መልካሚቱ አረኛ - ስለ አንዲቱ ግልገል ...
ገጽ 16

እንደ ንስር አሞራ ሕይወትን መቀየር !
ገጽ 11

የበለፀገ ምግብ ለማኅበረሰብ ጤና
ገጽ 12




አንድ
# አዲስ ዘመን
83ኛ ዓመት ቁጥር 215 ሚያዝያ 5 ቀን 2016 ዓ.ም ዋጋ 10:00
ቅዳሜ
ብዕራችን ለኢትዮጵያ ህዳሴ ይተጋል!





ፎቶ: ዳኜ አበራ

# በኢሚግሬሽንና ዜግነት አገልግሎት
## የአገልግሎት አሰጣጥ መማረራቸውን ተገልጋዮች ገለጹ

- ቋሚ ኮሚቴው በበኩሉ ተቋሙ አገልግሎቱን እንዲያሻሽል አሳስቧል

**መዓዛ ማሞ**

አዲስ አበባ፡- የኢሚግሬሽንና ዜግነት አገልግሎት የሚሰጠው አገልግሎት የተንዛዛና ተገልጋዩን ያላከበረ በመሆኑ መማረራቸውን ተገል,ጋዮች ገለጹ፡፡ በሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት የሕግና ፍትህ ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ በበኩሉ አገልግሎት አሰጣጡ ያልዘመነና መሻሻል ያለበት መሆኑን በምልከታው ወቅት አስታውቋል፡፡ የኢሚግሬሽንና ዜግነት አገልግሎት ዋና ዳይሬክተር ወይዘሮ ሰላማዊት ዳዊት በበኩላቸው፤ በሪፎርም ሥራ ›› አጀንዳዎችን ቀርጾ እየሠራ መሆኑንና ችግሮችን ከመቅረፍ አኳያም የባለድርሻ አካላት

በኢሚግሬሽንና ዜግነት ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል


ፎቶ: በሃዱሽ አብርሃ

## "የኢኮኖሚ ነፃነታችንን ለማረጋገጥ ወጣቶች ለሥራ የተከፈቱ በሮችን ሁሉ ሊጠቀሙ ይገባል"

- ሙፈሪሃት ካሚል
የሥራና ክህሎት ሚኒስትር

**ጌትነት ተስፋማርያም**

አዲስ አበባ፡- የኢኮኖሚ ነፃነታችንን ለማረጋገጥ ወጣቶች ለሥራ የተከፈቱ በሮችን ሁሉ ሊጠቀሙ ይገባል ሲሉ የሥራና ክህሎት ሚኒስትሯ ሙፈሪሃት ካሚል ተናገሩ።

"የኢኮኖሚ ነፃነታችንን ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል


መንገሻ ፈንታው(ዶ/ር)

# ከሰሞኑ በክልሉ በተካሄዱ ሰልፎች ሕዝቡ
## ስተመዘገቡ ውጤቶች እውቅና ሰጥቷል

- ጽንፈኞችንም በይፋ አውግዟል

**ፋንታነሽ ክንዴ**

አዲስ አበባ፡- ከሰሞኑ በአማራ ክልል በተካሄዱ ሰልፎች ሕዝቡ ባለፉት ስድስት የለውጥ ዓመታት በሁሉም መስክ ለተመዘገቡ ውጤቶች እውቅና መስጠቱን የአማራ ክልል ኮሙኒኬሽን ቢሮ አስታወቀ። የክልሉን ሰላም እያደፈረሱ ያሉ ጽፈኞችን በይፋ ማውገዙንም ጠቁሟል።

የአማራ ክልል ኮሙኒኬሽን ቢሮ ኃላፊ መንገሻ ፈንታው(ዶ/ር) ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ በክልሉ እየተከናወነ ባለው የሕግ ማስከበር ሥራ በተፈጠረው አንጻራዊ ሰላም ምክንያት የተለያዩ ሁነቶች ያለምንም ችግር ተከናውነዋል። በክልሉ የተለያዩ አካባቢዎች በተካሄዱ ሰልፎች ሕዝቡ ባለፉት ስድስት የለውጥ ዓመታት በሁሉም መስክ ለተመዘገቡ ውጤቶች እውቅና ሰጥቷል፤ ጽንፈኞችንም በይፋ አውግዟል።

ሰልፉ ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ(ዶ/ር) ባለፉት ስድስት የለውጥ ዓመታት ያሳኳቸውን ተግባራትና በሥራቸው ያለው አመራር በሁሉም ዘርፍ ላከናወናቸው ተግባራት እውቅናና ድጋፍ የተሰጠበት ነው ያሉት ቢሮ ኃላፊው፤ ያሉ

ከሰሞኑ በክልሉ ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል

## በአስቸጋሪ ሁኔታ የሚገኙ 70 ሺህ የሚጠጉ ዜጎችን ወደ ሀገራቸው የመመለስ ሥራ ተጀመረ

- 842 ኢትዮጵያውያን ትናንት ወደ ሀገራቸው ተመልሰዋል

ገጽ 4





አቶ ጫኔ አደፍርስ

# መስፈርቱን የሚያሟሉ ዩኒቨርሲቲዎች ራስ ገዝ መሆን ይችላሉ

**ልጅዓለም ፍቅሬ**

አዲስ አበባ፡- ትምህርት ሚኒስቴር በሥሩ ያሉት ሁሉም ዩኒቨርሲቲዎች የራስ ገዝነት መስፈርትና መመሪያ ካሟሉ ራስ ገዝ መሆን እንደሚችሉ አስታወቀ፡፡ ከዚህ በፊት ራስ ገዝ እንዲሆኑ የተመረጡ ዩኒቨርሲቲዎች በተያዘላቸው ጊዜ ወደ ትግበራ እንዲገቡ ድጋፍና ክትትል እያደረገ መሆኑን ሚኒስቴር መሥሪያ ቤቱ ጨምሮ ገልጿል፡፡

በትምህርት ሚኒስቴር የተቋማት አደረጃጀትና አመራር ዴስክ ኃላፊ አቶ ጫኔ አደፍርስ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንዳስታወቁት፤ መስፈርቱን የሚያሟሉ ሁሉም ዩኒቨርሲቲዎች ራስ ገዝ መሆን ይችላሉ፡፡

አቶ ጫኔ አክለውም፤ ራስ ገዝ ይሆናሉ ተብለው የተለዩ ዩኒቨርሲቲዎች በሚቀጥሉት አምስት ዓመታት ውስጥ ወደ ተግባር እንዲገቡ የድጋፍና ክትትል ሥራዎች እያደረገ ይገኛል ብለዋል፡፡

በትምህርት ሚኒስቴር ከሚከናወኑ የሪፎርም ሥራዎች ውስጥ የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ራስ ገዝ አደረጃጀት እንዲፈጠርላቸው ማድረግ አንዱ ነው ያሉት አቶ ጫኔ፤ ዩኒቨርሲቲዎቹ የወጣውን መስፈርትና መመሪያ ሲያሟሉ ራስ ገዝ የሚሆኑበት ሁኔታ እየተመቻቸ መሆኑን አመላክተዋል፡፡

ከተመረጡ ስምንት የምርምርና ሁለት የቴክኖሎጂ ዩኒቨርሲቲዎች በተጨማሪ ትምህርት ሚኒስቴር ያዘጋጀውን መስፈርት ለሚያሟሉ የትምህርት ተቋማት ራስ ገዝ ለማድረግ እየተሠራ ነው፡፡

የሰው ሀብት አደረጃጀት፣ የፋይናንስ አቅም፣ የትምህርት ፕሮግራም፣ የትምህርት ጥራትና ያላቸው ዓለም አቀፋዊ ግንኙነት ከመስፈርቶቹ መካከል ተጠቃሽ እንደሆኑ አቶ ጫኔ ተናግረዋል፡፡

ራስ ገዝነት ዩኒቨርሲቲዎቹ መንግሥት እያመቻቸ ያለው የሪፎርም ሥራ ተግባራዊ ማድረግ ከቻሉ በአጭር ጊዜ ውጤታማ መሆን የሚችሉበት መንገድ መሆኑን አስታውቀዋል፡፡

ከዚህ በፊት የተመረጡ ዩኒቨርሲቲዎች ያሉበት ደረጃ ለማጣራት ሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ የውይይትና የግምገማ መድረክ በማዘጋጀት ሲሠራ መቆየቱን ያነሱት አቶ ጫኔ፤ በተደረገው ግምገማ ዩኒቨርሲቲዎቹ በተያዘላቸው ጊዜ መግባት የሚያስችላቸው ጅማሮ ላይ እንደሚገኙ ጠቁመዋል፡፡

በተጨማሪም የውስጥ የፋይናንስ አቅም፣ መሠረተ ልማት፣ ከሰው ሀብት አደረጃጀት አንጻር ጥሩ ጅማሮ ላይ እንደሚገኙ አስረድተዋል፡፡

እንደ አቶ ጫኔ ገለጻ፤ የዩኒቨርሲቲዎች ራስ ገዝ መሆን በተለይ የትምህርት ጥራት ለማረጋገጥና በተሰጣቸው ተልዕኮና የትኩረት አቅጣጫ ተግባራዊ ለማድረግ ጠቀሜታ አለው፡፡ በተጨማሪም ተደራሽነት ፍትሐዊነት እንዲሁም ቀልጣፋ የአሰራር ሥርዓት መዘርጋት የሚያስችል መሆኑን አስረድተዋል፡፡

ዩኒቨርሲቲዎች በዓለም አቀፍ ደረጃ ተወዳዳሪና ተጽዕኖ ፈጣሪ ዜጋ ለማፍራት ተቋማት የሪፎርም ሥራዎች ማከናወን ይኖርባቸዋል፤ ከዚህ አንጻር የተለያዩ ሪፎርሞችን በማምጣት ራስ ገዝ ማድረግ አስፈላጊ ነው ብለዋል፡፡

# "የንግድ ቤቶች በማህበሩ ደንብ ስለማይገዙ የድምጽ ብክለትን ለማስቆም አልቻልንም"

## - የጎተራ ሳይት የጋራ መኖሪያ ቤቶች የቦርድ አመራሮች

# "የቦርድ አመራሩ ከተጠያቂነት ለመሸሽ እንጂ የንግድ ቤቶች በማህበሩ ደንብ ይገዛሉ"

## - በቂርቆስ ክፍለ ከተማ የወረዳ 04 አስተዳደር

**ሞገስ ተስፋ እና ሙሉቀን ታደገ**



አዲስ አበባ፡- ማህበሩ የንግድ ፈቃድ ስለማይሰጥ የንግድ ቤቶችን የድምጽ ብክለት በማህበሩ ደንብ ማስቆም እንደማይቻል የጎተራ ሳይት የጋራ መኖሪያ ቤቶች የቦርድ አመራሮች ገለጹ። የቂርቆስ ክፍለ ከተማ ወረዳ 04 አስተዳደር በበኩሉ የቦርድ አመራሩ ንግድ ቤቶቹ በማህበሩ መተዳደሪያ ደንብ አይገዙም የሚለው ተጠያቂነት ሲመጣ የመሸሻ መንገድ እንጂ በሁሉም ዘርፍ ያለውን ሁኔታ የማስተዳደርና የመቆጣጠር ኃላፊነት እንዳለባቸው አመላክቷል።

የጎተራ የጋራ መኖሪያ ቤት የቦርድ አመራሮች ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ በግቢው ውስጥ ከሚገኙ የንግድ ቤቶች የሚወጣ የድምጽ ብክለትና ሌሎች አዋኪ ድርጊቶች የነዋሪውን ደህንነት ለማስከበር በሚደረገው እንቅስቃሴ እንቅፋት ፈጥረዋል። ከፀጥታው ችግር በተጨማሪ በግቢው ውስጥ የድምጽ ብክለት አለ። ይህ ችግር በወረዳ እና በበላይ አመራሮች የሚፈታ ነው። ምክንያቱም ማህበሩ ተው ከማለት ባለፈ እርምጃ መውሰድ አይችልም፤ ከንግድ ቤቶች ጋር በተያያዘ ቁጥጥር የሚያደርገው የንግድ ፍቃድ የሰጠው አካል ነው።

ለነጋዴዎች ቦርዱ ፈቃድ እንደማይሰጥ የገለጹት የማህበሩ የቦርድ ኃላፊዎች፤ ይህም የንግድ ቤቶችን ለመቆጣጠር የሚደረገውን ጥረት አስቸጋሪ አድርጎታል ብለዋል። በማህበሩ የመተዳደሪያ ደንብ ከድምጽ ጋር በተገናኘ ከምሽት አራት ሰዓት በኋላ ማንም ሰው ታኮ (ሂል) ጫማ አድርጎ መረበሽ ክልክል ነው። በተጨማሪም ማንም ሰው በምሽት ሙዚቃ መክፈት አይችልም። ከፍቶ ማዳመጥ ቢፈልግ በኤርፎን ብቻ ነው የሚል ሕግ ቢኖርም በግቢው ውስጥ ባሉ ንግድ ቤቶች ያሉ ባርና ሬስቶራንቶች የሚወጣው ድምጽ ግን ነዋሪውን እረፍት እየነሳ ነው። ቦርዱ ችግሩን በተደጋጋሚ ለወረዳ እና ለከተማ አስተዳደሩ ቢያሳውቅም ምላሽ የሚሰጥ አካል ማግኘት አልተቻለም ብለዋል።

በቂርቆስ ክፍለ ከተማ የወረዳ 04 ዋና ሥራ አስፈጻሚ አቶ ናሆም መንግስቱ በበኩላቸው፤በጎተራ ኮንዶምንየም ውስጥ በርካታ ሕገ ወጥ ድርጊቶች የሚፈጸምባቸው ብዙ ተቋማት ነበሩ። በዚህም ከ19 በላይ በሚሆኑ ተቋማት በተወሰደ እርምጃ ከድምጽ ብክለት ጋር ተያይዞ የነበረውን ችግር መቀነስ ተችሏል።

በጋራ መኖሪያ ቤቶች ጭፈራ ቤቶች አሉ። ነገር ግን ለጭፈራ ቤት የንግድ ፈቃድ አይሰጥም። ፈቃድ የሚወስዱት ባርና ሬስቶራንት በሚል ነው። ባርና ሬስቶራንት የሚለውን ንግድ ፈቃድ በመጠቀም ወደ ጭፈራ ቤት የሚገቡ ይኖራሉ። 251 የሚባል ቤትና ብሎክ 28፤ 27፤ 26 ያሉ ቤቶች ፈቃድ ሲወስዱ ባርና ሬስቶራንት ብለው ነበር። ነገር ግን ከተሰጣቸው ፈቃድ ውጪ ሲሰሩ ተገኝተው እርምጃ የተወሰደባቸው መሆኑን አመላክተዋል።

ባርና ሬስቶራንት ተብሎ ፈቃድ የሚሰጥበት አሰራር እና መመሪያ መኖሩን የጠቆሙት አቶ ናሆም፤ ጭፈራ ቤት የሚል ፈቃድ ግን የለም ብለዋል። የድምጽ ብክለትን ለመቀነስ በማህበሩ መተዳደሪያ ደንብ አይገዙም የሚለው ተጠያቂነት ሲመጣ የመሸሻ መንገድ እንጂ በሁሉም ዘርፍ ያለውን ሁኔታ ቦርዱ የማስተዳደርና የመቆጣጠር ኃላፊነት እንዳለበት ገልጸዋል።

# ኦቲዝም፤ ትኩረት የሚሻው የጤና እክል

**ቃልኪዳን አሳዬ**

ሃሳባቸውን በንግግርም ሆነ በተለመዱ መንገዶች ለመግለፅ ይቸገራሉ። ይልቁንም የሚፈልጉትን ነገር በዙሪያቸው ያሉ ሰዎችን እጅ በመጎተት ለማስረዳት ይሞክራሉ። ከሰዎች ጋር ማህበራዊ ግንኙነቶችን አለማድረግ፤ ዓይን ለዓይን መተያየትን መሸሽ እና በአካባቢያቸው ለሚደረጉ ነገሮች ትኩረት አለመስጠት መለያ ባህሪያቸው ነው። አንድን ነገር ባልተለመደ መልኩ ደጋግመው ሲያደርጉ እንዲሁም በቀላሉ ሲያለቅሱና ሲረበሹም ይስተዋላሉ።

በኢትዮጵያ ዛሬም ድረስ ኦቲዝምን በኃጢያትና በእርግማን የመጣ አድርጎ የማየት የግንዛቤ ችግር መኖሩ ብዙ ልጆች ተገለለው ቤት ተዘግቶባቸው እንዲቀመጡ አድርጓል፡፡

በዲላ ዩኒቨርሲቲ የልዩ ፍላጎትና የአካቶ ትምህርት ረዳት ፕሮፌሰር አሊ ሳኒ ሰይድ እንደሚናገሩት፤ በኦቲዝም ጥላ ሥር ለሚኖሩ ልጆች ተከታታይነት ያላቸው ክህሎትን ለማሻሻልና ባህሪን ለማረቅ የሚያስችሉ ስልጠናዎችን በመስጠት ራሳቸውን የቻሉ፣ አምራችና በሀገራቸው እድገት ላይ የበኩላቸውን አስተዋጽኦ የሚያበረክቱ ዜጎች እንዲሆኑ ማድረግ ይቻላል፡፡

ልጆቻቸው ኦቲዝም ያለባቸው ወላጆች የከፈቷቸው ማዕከላት የሌሎችንም ወላጆች ችግር ለመፍታት አገልግሎቶችን እየሰጡ መሆናቸውን ያነሱት ረዳት ፕሮፌሰሩ፤ ዜጎቹ ከአመጋገባቸውና ከኑሯቸው አንጻር የሚያገኙት ድጋፍ አነስተኛ ቢሆንም እንደማንኛውም ሰው የአካል፣ የአስተሳሰብና የስሜት እድገት እንደሚያሳዩ ይጠቅሳሉ፡፡

እንደ እሳቸው ገለጻ፤ ኦቲዝም ባለባቸው ልጆች ላይ የሚታይባቸው ችግር የስነ ተግባቦትና የማህበራዊነት ሲሆን፤ ይህም የሚሰጣቸው ድጋፍ ውስን እንዲሆን በማድረግ ለመደፈርና ለተለያዩ አደጋዎች እንዲጋለጡ ያደርጋቸዋል፡፡

ችግሩን ለመፍታት ከወላጆች ጋር መወያየት አስፈላጊ መሆኑን ጠቁመው፣ ወላጆችም ልጆቻቸው ለስነ ተዋልዶ ከበቁበት ጊዜ ጀምሮ ስለ ጾታዊ ግንኙነት በአግባቡ በማስረዳት ሊደርስ የሚችለውን ጉዳት መቀነስ እንደሚችሉ ይገልጻሉ፡፡

የሦስተኛ ዲግሪ ማሟያ ጥናታቸውን ኦቲዝም ያለባቸው ልጆች ያሏቸው ወላጆች ጫና ላይ መስራታቸውን በመጥቀስ፤ ሁኔታው የወላጆችን አኗኗር የሚፈትን በመሆኑ ወላጆች በጉዳዩ ዙሪያ ማንበብና መሰልጠን እንዲሁም ተመሳሳይ ልጆች ካሏቸው ወላጆች ልምድ በመቀያየር ጉዳዩ ተስፋ የሚያስቆርጥ ሳይሆን የሚሻሻል በመሆኑ ሳይታክቱ ልጆቻቸው በራሳቸው እስኪቆሙ ድረስ ድጋፍ ማድረግ እንዳለባቸው ይመክራሉ፡፡

ሁሉም ዜጋ የመማርና የመኖር መብት ያለው በመሆኑ መንግሥት ችግሩን በመረዳት ድጋፍ ሊያደርጉ የሚችሉ አካላትን በማስተባበር በየትምህርት ቤቶች ኦቲዝም ላለባቸው ልጆች የሚያስፈልጉ የመማሪያ ቁሶችን በማሟላትና መምህራንን በመመደብ እንዲማሩ ማመቻቸት እንዳለበትም ይጠቅሳሉ፡፡

ወላጆች ከመቸገራቸው የተነሳ ልጆቻቸውን በሰንሰለት አስረው የእለት ስራቸውን እንደሚሰሩ የሚናገሩት ደግሞ የኒያ ፋውንዴሽንና ጆይ ኦቲዝም ማዕከል ሥራ አስኪያጅ ኢሌኒ ዳምጠው ናቸው፤ እሳቸው እንደሚሉት ተቋማቸው በወላጆች ላይ የሚደርሰውን ጫና ለመቀነስ ላለፉት 22 ዓመታት በየቤቱ ተደብቀው የተቀመጡ ኦቲዝም ያለባቸውን ልጆች አውጥቶ በማሰልጠንና እራስን በማስቻል ሲደግፍ ቆይቷል፡፡

እንደ ወይዘሮ ኢሌኒ ገለጻ፤ ልጆቹ መማር፣ ስዕል መሳል፣ መዝፈንና የተለያዩ ስራዎችን መስራት ስለሚችሉ ተሰጥኦአቸውን ለይቶ በማውጣት ወደ ሥራ በማስገባት ከኅብረተሰቡ ጋር አብረው እንዲኖሩ ማድረግ ያስፈልጋል፡፡ ተቋማቸው በአጫጭርና ረጃጅም ስልጠናዎች በርካታ ኦቲዝም ያለባቸውን ልጆች መቀየር የቻለ ሲሆን፤ በመስተንግዶ፣ በጽዳትና በሌሎችም ሞያዎች አስተምሮ በማስመረቅ ሥራ ሰጥቷቸዋል፡፡

በርካቶች ወደተቋሙ ለመግባት በመጠባበቅ ላይ እንደሚገኙና የኒያ ፋውንዴሽንም በ4ሺህ 622 ካሬ ሜትር ላይ የጆይ ኦቲዝም ማዕከል በማስገንባት ላይ እንደሚገኝ የሚጠቅሱት ወይዘሮ ኢሌኒ፤ ከ16 ዓመታት በፊት የተጀመረው የማዕከሉ ግንባታ ሲጠናቀቅ ኦቲዝም ላለባቸው 500 ዜጎች አገልግሎት መስጠት እንደሚችል ይገልፃሉ፡፡

ማዕከሉ በውስጡ የማቆያ፣ የማሰልጠኛ፣ የጥናትና ምርምር ማከናወኛ፣ ሲኒማ ቤትና ሌሎችንም አገልግሎቶች ይይዛል፤ የእደ ጥበብ ሥራዎችንም በማስፋት ወደ ፋብሪካ ለማሳደግ አስተዋጽኦ ያደርጋል የሚሉት ሥራ አስኪያጇ፣ ግንባታው ተጠናቆ በሙሉ አቅሙ አገልግሎት መስጠት እንዲችል ሁሉም የበኩሉን አስተዋጽኦ እንዲያደርግ ይጠይቃሉ፡፡

የሚያዚያ ወር የዓለም አቀፍ የኦቲዝም ግንዛቤ ወር መሆኑን በመገንዘብ የኒያ ፋውንዴሽንም በግንባታ ላይ የሚገኘውን ጆይ ኦቲዝም ማዕከል በከፊል በማስመረቅ የግንዛቤ ማስጨበጫ ሥራው እንደሚሠራ አመላክተው፤ ከሚያዝያ 5 እስከ 19 ባሉ ቀናት በመቀሌ፣ በጅማ፣ በወላይታ ሶዶና በድሬዳዋ ከተሞች የግንዛቤ ማስጨበጫ ሥራዎቹን አጠናክሮ ይቀጥላል ይላሉ፡፡

ዮናታን ዘሪሁን ከኦቲዝም ጋር የሚኖር የ16 ዓመት ታዳጊ ሲሆን፤ የአቶ ዘሪሁን ተከስተ የመጀመሪያ ልጅ ነው፡፡ ዮናታን ከአምስት ዓመቱ ጀምሮ በኒያ ፋውንዴሽን ውስጥ በመሆን ተገቢውን ክብካቤና የባለሙያ ምክር ማግኘቱ በብዙ መንገድ እንዲሻሻል አድርጎታል፡፡ በልጃቸው ላይ የሚታየው ለውጥ ለቤተሰቡ የስነ ልቦና እረፍት መስጠቱን ወላጅ አባቱ ይናገራሉ፡፡

ከዚህ ቀደም ማህበረሰቡ ከኦቲዝም ጋር በተያያዘ ግንዛቤው አናሳ በመሆኑ ኦቲዝም ያለባቸው ልጆች ወላጆች መገለል ይደርስብናል የሚል ስጋት አለባቸው የሚሉት አቶ ዘሪሁን፤ አሁን ላይ ከፍተኛ መሻሻሎች መጥተዋል። ልጄን ጨምሮ በተመሳሳይ ሁኔታ ውስጥ ያሉ ልጆች እንደማንኛውም ዜጋ ተሳክቶላቸው ማየት እመኛለሁ ይላሉ፡፡

# ስምክትል አንባ ጠባቂና ስሌሎች ዘርፎች የእጩ አንባ ጠባቂዎች የሕዝብ ጥቆማ ዛሬ ይጀመራል

**ዳግማዊት አበበ**

አዲስ አበባ፡- ለኢትዮጵያ እንባ ጠባቂ ተቋም በተጓደሉት እጩ ምክትል እንባ ጠባቂና ለሌሎች ሁለት ዘርፎች እጩ እንባ ጠባቂዎች ምትክ ለመምረጥ የሕዝብ ጥቆማ በዛሬው እለት ተጀምሯል፡፡

በሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት የኢትዮጵያ እንባ ጠባቂ ተቋም እጩ አቅራቢ ኮሚቴ ፀሐፊ አቶ እውነቱ አለነ በትናንትናው እለት በሰጡት ጋዜጣዊ መግለጫ እንዳስታወቁት፤ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት በአዋጅ ቁጥር 1142/2011 እና በተሻሻለው አዋጅ ቁጥር 1307/2016 አንቀጽ 10 የኢትዮጵያ እንባ ጠባቂ ተቋም እንዲቋቋም አድርጓል፡፡

የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት መጋቢት አምስት ቀን 2016 ዓ.ም ባካሄደው 17ኛ መደበኛ ስብሰባው የእጩ አቅራቢ ኮሚቴ ማቋቋሙን የገለጹት ፀሐፊው፤ ኮሚቴውም በይፋ ሥራ መጀመሩን አስታውቀዋል፡፡

ተቋሙን የሚመሩ ዋና እንባ ጠባቂና ምክትል እንባ ጠባቂ በምክር ቤቱ ተሹመው እንቅስቃሴ ሲያደርጉ መቆየታቸውን ያነሱት አቶ እውነቱ፤ ይሁን እንጂ በልዩ ልዩ ምክንያቶች ምክትል እንባ ጠባቂ ፣ ሴቶችና ሕፃናት ፣አረጋውያንና አካል ጉዳተኞች እንባ ጠባቂ እንዲሁም



አቶ እውነቱ አለነ

በግል ዘርፍ የሚደርሱ በደሎችን የሚመረምር የዘርፉ እንባ ጠባቂ መጓደላቸውን ገልጸዋል፡፡

በተጓደሉት ምክትል እንባ ጠባቂ ፣ ሴቶችና ሕፃናት፣ አረጋውያንና አካል ጉዳተኞች እንባ ጠባቂ እንዲሁም በግል ዘርፍ የሚደርሱ በደሎችን የሚመረምር የዘርፉ እንባ ጠባቂ ምትክ ሕዝቡ ከሚያዝያ አምስት እስከ ሚያዚያ 20 ቀን 2016 ዓ.ም ድረስ ባሉት 15 ተከታታይ ቀናት እጩዎችን መጠቆም ይችላል ብለዋል፡፡

እጩዎቹን በአካል ፣ በጽሑፍ ፣ ለዚሁ ዓላማ በተዘጋጁ ሳጥኖች እንዲሁም በኦንላይን መጠቆም እንደሚቻልም አስረድተዋል፡፡

በዚህም መሠረት እጩዎች ፣ዜግነት ኢትዮጵያዊ የሆነ/የሆነች፣ በሥራ ላይ ላለው ሕገ-መንግሥት ተገዢ የሆነ/የሆነች ፣በሕግ አልያም በተዛማጅ የትምህርት መስክ ቢያንስ የመጀመሪያ ዲግሪ እንዲሁም በቂ የሥራ ልምድ ፣ከማንኛውም የፖለቲካ ፓርቲ ገለልተኛ የሆነ/የሆነች ፣በታታሪነት ፣ በታማኝነትና በሥነ ምግባር መልካም ስም ያለው/ያላት ከደንብ መተላለፍ ውጪ በሌላ ወንጀል ያልተፈረደበት/ያልተፈረደባት፣ ሥራውን ለመሥራት የሚያስችል ሙሉ ጤንነት ያለው/ያላት ፣እድሜ ከ35 በላይ የሆነ/የሆነች የሚሉ መስፈርቶችን ማሟላት ይኖርበታል ተብሏል፡፡

ጽህፈት ቤቱም ከዛሬ ጀምሮ ባሉት አምስት ተከታታይ ቀናት ተደማጭነትና ተነባቢነት ባላቸው የመገናኛ ብዙኃን መስፈርቶቹን የማስተዋወቅ ሥራ የሚሠራ ይሆናል ሲሉም ገልጸዋል፡፡



ዶክተር ኢንጂነር ሱልጣን ዋሊ

# ኢትዮጵያ ካላት የኢነርጂ አቅም ያለማችው ከአራት በመቶ በታች ነው

## - ዘላቂ የኢነርጂ ልማት ስትራቴጂ ይፋ ሆኗል

**ሄለን ወንድምነው**

አዲስ አበባ፡- ኢትዮጵያ 150 ጊጋ ዋት ኢነርጂ የማመንጨት አቅም ያላት ቢሆንም እስካሁን አምስት ነጥብ አራት ጊጋ ዋት ማለትም ከአራት በመቶ በታች ብቻ ማመንጨትና መጠቀም መቻሏን የውሃና ኢነርጂ ሚኒስቴር ገለጸ፡፡

ሚኒስቴሩ ዘላቂ የኢነርጂ ልማት ስትራቴጂ በትናንትናው ዕለት ይፋ አድርጓል፡፡

የውሃና ኢነርጂ ሚኒስትር ዴኤታ ዶክተር ኢንጂነር ሱልጣን ዋሊ በመርሀ ግብሩ እንደገለጹት፤ ኢትዮጵያ እምቅ የኢነርጂ ሀብት ያላት ቢሆንም ከዚህ ቀደም የነበረው ፖሊሲና ስትራቴጂ የግሉን ሴክተር የሚያሳትፍ ባለመሆኑ በሚፈለገው ደረጃ ተጠቃሚና ተደራሽ ማድረግ አልተቻለም፡፡

በዚህም ኢትዮጵያ 150 ጊጋ ዋት የኢነርጂ አቅም እያላት እስካሁን ድረስ በመንግሥት አቅም አምስት ነጥብ አራት ጊጋ ዋት ብቻ ማለትም ከአራት በመቶ በታች ማመንጨትና መጠቀም ችላለች ብለዋል፡፡

አሁን ላይ ሀገሪቱ እያሳየች ያለውን የኢኮኖሚ እድገት መንግሥት በሚያመነጨው የኃይል አቅርቦት ብቻ ተደራሽ ማድረግ የማይቻል በመሆኑ የግሉ ሴክተር ኃይል በማመንጨት፣ በማስተላለፍና በማሰራጨት ሊሳተፍ ይገባል ብለዋል፡፡

የኢነርጂ አማራጮችን በሚፈለገው ደረጃ ማልማት ከቻልን ከሀገር አልፈን በቀጣናው ያለውን የኢነርጂ ችግር በመፍታት ሁለንተናዊ ብልጽግናን ማረጋገጥ እንችላለን ሲሉ ተናግረዋል ሚኒስትር ዴኤታው፡፡

እኤአ ከ2024 እስከ 2030 የሚተገበር የኢነርጂ ልማት ስትራቴጂ ይፋ መሆኑን ገልጸው፤ ስትራቴጂው የኢነርጂ ተደራሽነትን፣ አቅርቦትን፣ አማራጭንና ስብጥርን ለማሳደግ፣ የኢነርጂ ብክነትን ለመቀነስ እና ዘላቂነት ያለው የኢነርጂ አስተዳደርን አቅም ለማጎልበት እንደሚረዳም አስታውቀዋል።

ኢትዮጵያ ለነዳጅ የምታወጣውን የነዳጅ ወጪ ለመቀነስና በሀገሪቱ ታዳሽ ኢነርጂን ለማስፋፋት እንዲሁም የግሉ ሴክተር በኃይል ማመንጨትና በኃይል አቅርቦት እንዲሳተፍ በማድረግ በቀጣናው የተረጋጋ የኢነርጂ ልማት እንዲኖር የማድረግ ዓላማ እንዳለው ጨምረው ገልጸዋል።

ስትራቴጂው መንግሥት ያስቀመጠውን የኢኮኖሚ ማሻሻያ፣ ሁሉንም የልማት ዘርፎች፣ የ10 ዓመቱን እቅድ፣ የአረንጓዴ ልማት ኢኮኖሚውን እና የተባበሩት መንግሥታት ድርጅት ዘላቂ የልማት ግቦችን ታሳቢ ያደረገ ነው ብለዋል።

በውሃና ኢነርጂ ሚኒስቴር የኢነርጂ ሀብት ጥናት መሪ ሥራ አስፈጻሚ አቶ ካሌብ ታደሰ በበኩላቸው፤ በሀገሪቱ የኤሌክትሪክ ኃይል እያገኙ ያሉት ዜጎች 52 በመቶ ብቻ ሲሆኑ፤ ስትራቴጂው ሲተገበር ተደራሽነቱ ወደ 72 በመቶ ከፍ እንደሚልም አስታውቀዋል፡፡

የውሃና ኢነርጂ ሚኒስቴርና የተለያዩ ተቋማትን ያቀፈው የባለሙያዎች ቡድን ስትራቴጂውን ለማዘጋጀት አንድ ዓመት ከ6 ወር እንደወሰደበት እንዲሁም ለስትራቴጂው የግብዓት ማሰባሰቢያ ስድስት አውደ ጥናቶች መካሄዳቸውን ገልጸዋል፡፡

የጀርመን ዓለም አቀፍ የልማት ትብብር ድርጅት(ጂ አይ ዜድ) ለስትራቴጂው ዝግጅት የፋይናንስና የቴክኒክ ድጋፍ ማድረጉን አንስተው፤ በቀጣይ ከግሉ ሴክተር፣ ከአጋር የልማት ድርጅቶች እንዲሁም ከትራንስፖርት፣ ከግብርና፣ ከማዕድንና ኢነርጂ ዘርፎች ጋር በትብብር እንደሚሠራ አስታውቀዋል።

ስትራቴጂው የዘርፉ ተቋማትና ባለድርሻ አካላት ያላቸውን ቅንጅት ከማጠናከሩም ባለፈ የኢነርጂ አቅምን በአግባቡ ለመጠቀም ያስችላል ነው ያሉት፡፡



አምባሳደር ጃቬር ኒኖ ፔሬዝ
አምባሳደር ሮላንድ ኮቢያ

# ኅብረቱ ከኢትዮጵያ ጋር ያለውን ስትራቴጂካዊ አጋርነት አጠናክሮ እንደሚቀጥል አስታወቀ

**ቃልኪዳን አሳዬ**

አዲስ አበባ፡- የአውሮፓ ኅብረት ከመሠረታቸው ጥቂት ስትራቴጂካዊ አጋር ሀገራት መካከል አንዷ ከሆነችው ኢትዮጵያ ጋር ያለውን ግንኙነት አጠናክሮ እንደሚቀጥል አስታወቀ፡፡

በኢትዮጵያ የአውሮፓ ኅብረት አምባሳደር ሮላንድ ኮቢያ እና በአፍሪካ ኅብረት የአውሮፓ ኅብረት አምባሳደር ጃቬር ኒኖ ፔሬዝ በፈረንጆቹ ግንቦት ዘጠኝ የሚከበረውን የአውሮፓ ቀን አስመልክቶ ትናንት ከመገናኛ ብዙኃን ጋር ቆይታ አድርገዋል።

በዚሁ ወቅት አምባሳደር ሮላንድ ኮቢያ እንደገለጹት፤ ኅብረቱ ስትራቴጂካዊ አጋሩ ከሆነችው ኢትዮጵያ ጋር በፖለቲካና ኢኮኖሚ መስኮች ጠንካራ ትብብር መስርቷል። በተፈጠረው ኢኮኖሚያዊ ግንኙነትም ኢትዮጵያ ምርቶቿን ያለምንም ግብር በአውሮፓ ገበያ ላይ እያቀረበች ነው። በዚህም አውሮፓ 20 በመቶ የኢትዮጵያ ወጪ ንግድ መዳረሻ ሆኗል።

ኅብረቱ በኢትዮጵያ የግሉን ዘርፍ ለማጎልበት የሚያስችሉ በርካታ ስምምነቶች በማድረግ ተግባራዊ ስለማድረጉም አንስተዋል።

የአውሮፓ ኅብረት ነፃነት፣ ዴሞክራሲ፣ እኩልነትና ሰላም የማስፈን ተግባራት ተቀዳሚ መርሆዎቹ እንደሆኑ የጠቆሙት አምባሳደሩ፤ ኢትዮጵያን ጨምሮ ከተለያዩ ሀገራት ጋር በዘላቂና መርህ መር አግባብ የትብብር ግንኙነት እያደረገ እንደሚገኝ ተናግረዋል።

ኢትዮጵያ ግጭት ውስጥ በገባችበት ወቅት ኅብረቱ የሰብዓዊና ቁሳዊ ድጋፍ እያደረገ እንደነበር የገለጹት አምባሳደር ሮላንድ ኮቢያ፤ በትምህርት፣ በጤና፣ በኢንቨስትመንት፣በሰብዓዊ መብት ጥበቃ፣ በንግድና በሌሎችም ዘርፎች ያለውን ግንኙነት አጠናክሮ እንደሚቀጥል አረጋግጠዋል።

በአማራ፣ በኦሮሚያ፣ በትግራይና በሌሎች አካባቢዎች በተከሰቱ ግጭቶች ንፁሐን ዜጎች ጉዳት እየደረሰባቸው መሆኑን ጠቅሰው፤ ኅብረቱ ለችግሩ ፖለቲካዊ መፍትሔ እንዲሰጠው በሚደረገው ጥረት የራሱን ሚና ለመወጣት ዝግጁ እንደሆነ አመላክተዋል።

በአፍሪካ ኅብረት የአውሮፓ ኅብረት አምባሳደር ጃቬር ኒኖ ፔሬዝ በበኩላቸው፤ የአውሮፓ ኅብረትና አፍሪካ በኢኮኖሚ፣ በሰላምና መረጋጋት እንዲሁም በሰው ተኮር የልማት ሥራዎች በትብብር እየሠሩ መሆኑን ጠቁመው፤ ኅብረቱ በአፍሪካ እያከናወናቸው ያሉ ተግባራት የሕዝብ ለሕዝብ ትስስሩን ለማጠናከር የሚያግዙ መሆናቸውን ገልጸዋል፡፡

አፍሪካ እምቅ የማደግ አቅም ያላት በመሆኑ ያንን በአግባቡ በመጠቀም አፍሪካውያን እንዲጠቀሙ ማድረግ እንደሚገባ የገለጹት አምባሳደር ጃቪየር ኒኖ ፔሬዝ፤ በንግድና ኢንቨስትመንት ረገድ የአውሮፓ ኅብረት አባል ሀገራት ኩባንያዎች በአፍሪካ ከ241 ቢሊዮን ዩሮ በላይ ኢንቨስትመንት እንዳላቸው ጠቅሰዋል።

“የአውሮፓ ኅብረት ከአፍሪካ ኅብረት ጋር በሰላምና መረጋጋት፣ በስደት እና በሌሎች የባለብዙ ወገን ትብብር መስኮችም በጋራ እየሠራ ነው፡፡ አፍሪካ በዲጂታላይዜሽን፣በነፃ የንግድ ልውውጥ፣ በግብርና ልማትና በተለያዩ መስኮች ለውጥ እንድታመጣ ኅብረቱ አብዝቶ ይሻል” ሲሉም አክለዋል።

ከ74 ዓመታት በፊት በስድስት ሀገራት ጥምረት የተመሰረተው የአውሮፓ ኅብረት የአባል ሀገራቱን ቁጥር 27 በማድረስ፣ በፖለቲካዊና ኢኮኖሚያዊ ጉዳዮች እንዲሁም በትብብር ለመልማትና ሰላምን ለማረጋገጥ የጋራ መርህ አንግቦ እየተንቀሳቀሰ እንደሚገኝ በመድረኩ ተገልጿል።

# በአስቸጋሪ ሁኔታ የሚገኙ 70 ሺህ የሚጠጉ ዜጎችን ወደ ሀገራቸው የመመለስ ሥራ ተጀመረ

## - 842 ኢትዮጵያውያን ትናንት ወደ ሀገራቸው ተመልሰዋል

**አዲሱ ገረመው**

አዲስ አበባ፡- በሳዑዲ ዓረቢያ በአስቸጋሪ ሁኔታ ውስጥ የሚገኙ 70 ሺህ የሚጠጉ ዜጎችን ወደ ሀገራቸው የመመለስ ሥራ ተጀምሯል። በትናንትናው ዕለት በነበረው ሁለት በረራ ብቻ 842 ኢትዮጵያውያን ወደ ሀገራቸው ተመልሰዋል።

መንግሥት በሦስተኛው ምዕራፍ ዜጋ ተኮር ዲፕሎማሲ በሳዑዲ አረቢያ በአስቸጋሪ ሁኔታ ውስጥ የሚገኙ 70 ሺህ ኢትዮጵያውያንን ወደ ሀገራቸው ለመመለስ ሥራ መጀመሩን ተከትሎ በትናንትናው ዕለት በነበሩ ሁለት በረራዎች ሴቶችና ሕፃናትን ጨምሮ 842 ዜጎች ወደ ሀገር ቤት መመለስ ችለዋል። ተመላሾቹን ቦሌ ዓለም አቀፍ አውሮፕላን ማረፊያ ሲደርሱም የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር ቃል አቀባይ ነብዩ ተድላ እና ሌሎች የመንግሥት የሥራ ኃላፊዎች አቀባበል አድርገውላቸዋል።

የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር ቃል አቀባይ ነብዩ ተድላ በወቅቱ እንደተናገሩት፤ ዜጎችን ወደ ሀገራቸው የመመለስ ስራውን ለማስጀመር 16 የመንግሥት ተቋማትን በአባልነት ያቀፈ ብሔራዊ ኮሚቴ ተዋቅሮ ካለፈው ሳምንት ጀምሮ ወደ ሳዑዲ ዓረቢያ በማቅናት ከሀገሪቱ ከፍተኛ የመንግሥት የሥራ ኃላፊዎች ጋር ምክክር ተደርጓል።

በሳዑዲ አረቢያ እስር ቤት የሚገኙ ሰነድ አልባ ዜጎችን ወደ ሀገራቸው ለመመለስ ለተከታታይ አራት ወራት በሳምንት 12 የአውሮፕላን በረራ እንደሚደረግ ቃል



አቀባዩ ገልጸዋል።

ቃል አቀባዩ፤ በሳኡዲ ዓረቢያ እስር ቤቶችና ማቆያ ማዕከላት የነበሩ 842 ኢትዮጵያውያንን ትናንት በተደረጉ ሁለት ዙር በረራዎች ወደ ሀገር ቤት መመለስ መቻላቸውንም ጠቅሰዋል።

ለተመላሽ ዜጎች ጊዜያዊ የማረፊያ ቦታ እንደተዘጋጀላቸውና ተገቢውን ድጋፍና እንክብካቤ በማድረግ ከቤተሰብ ጋር የመቀላቀል እንዲሁም በየክልሎች የሥራ እድል ተፈጥሮላቸው ህይወታቸውን በተሻለ ሁኔታ ለመምራት እንዲችሉ ይደረጋል ተብሏል።

በሳኡዲ ዓረቢያ በአስቸጋሪ ሁኔታ ውስጥ የነበሩና በትናንትናው ዕለት ወደ ሀገራቸው የተመለሱ ወጣቶች በበኩላቸው፤ የተሻለውን ህይወት ለመምራት በሚል ሕገ ወጥ በሆነ ሁኔታ ከሀገራቸው ቢወጡም ለበርካታ ወራት አስቸጋሪ ሁኔታ ውስጥ እንደነበሩ ገልጸዋል። በቀጣይ ከስህተታቸው ታርመው በሀገራቸው ሠርተው መለወጥ እንደሚፈልጉና ለዚህም መንግሥት የሥራ እድል እንዲያመቻችላቸው ጠይቀዋል። ወጣቶች ስደትን ከመምረጥ ሀገራቸው ውስጥ ሠርተው መለወጥ እንዳለባቸው ከገጠማቸው ፈተና ተነስተው መክረዋል።

በቅርቡ በውጭ ጉዳይ ሚኒስትር ዴኤታ አምባሳደር ብርቱካን አያኖ የተመራ ከፍተኛ የመንግሥት የሥራ ኃላፊዎችን ያካተተ የኢትዮጵያ የልዑክ ቡድን በሪያድ በመገኘት ከሳዑዲ አረቢያ አቻው ጋር በሳዑዲ ውስጥ የሚገኙ ሕገወጥ ፍልሰተኛ ኢትዮጵያውያን ዜጎችን ወደ ሀገር ቤት መመለስ በሚቻልባቸው ሁኔታዎች ላይ መምከራቸው ይታወሳል።

# ከሰሞኑ በክልሉ...

ከ1ናው ገጽ የዞረ

ክፍተቶችን በመጠቆም በአጭር ጊዜ እንዲስተካከሉም መልእክት አስተላልፏል።

በሁሉም መስክ እየተከናወኑ ያሉ የለውጥ ሥራዎችን ለማደናቀፍ የሚፈልጉት የውጭና የውስጥ ጠላቶችን በማውገዝ ለመታገል ያለውን ቁርጠኝነትም አሳይቷል ብለዋል።

በተጨማሪም የዓባይ ግድብ ብዙ ፈተናዎችን አልፎ በተወሰዱ የሪፎርም ሥራዎች ወደመጨረሻው ምዕራፍ በመድረሱ የተሰማውን ደስታና ድጋፍ ለማሳደግ ያለውን ቁርጠኝነት መግለጹንም አመላክተዋል።

ከሰሞኑ ከተከበረው የኢድ አልፈጥር በዓል ቀደም ብሎ ጽንፈኛ ኃይሉ ግድያን ጨምሮ የተለያዩ ችግሮችን በመፍጠር በዓሉን ለማወክ ጥረት አድርጎ እንደነበር ጠቅሰው፤ ሕዝቡና የፀጥታ አካላት በሠሩት የቅንጅት ሥራ ሕዝበ ሙስሊሙ በነቂስ ወጥቶ በዓሉን በሰላም ማክበር ችሏል። ድርጊቱንም በይፋ ተቃውሟል ብለዋል።

ይህም በክልሉ እየተከናወነ ያለው የሕግ ማስከበር ሥራ በጥሩ ሁኔታ እየተከናወነ መሆኑን የሚያመላክት ነው ብለዋል።

እንደ ቢሮ ኃላፊው ገለጻ፤ መከላከያ ሠራዊት ከክልሉ የጸጥታ ኃይል ጋር በመተባበር የጽንፈኛ ኃይሉ ማሰልጠኛና መደበቂያ የሆኑ ቦታዎች ላይ ሁሉ አስፈላጊው ሥራ እየተሠራ ነው። በዚህም በቁጥጥር ስር አድርጓቸው የነበሩ ወረዳና ቀበሌዎችን ለቆ በየጫካው እየተሹለከለከ የሽፍትነት ተግባራትን እያከናወነ ነው።

ሕዝቡ መረጃዎችን በመስጠትና ጽፈኞችን አሳልፎ በመስጠት የሕግ ማስከበር ሥራውን እያገዘ ነው ያሉት ዶክተር መንገሻ፤ በሚሠሩ ኦፕሬሽኖችም የቡድኑ አመራሮችን ጨምሮ ቀንደኛ ጽንፈኞች ላይ እርምጃ እየተወሰደ ነው። ይህን ተከትሎም በአብዛኛው የክልሉ አካባቢዎች ሰላም ማስፈን ተችሏል።

ከሕግ ማስከበር ሥራው ጎን ለጎን የልማት ሥራዎች በአግባቡ እየተከናወኑ መሆኑን ጠቅሰው፤ ለግብርና ሥራው አስፈላጊ የሆኑ ግብዓቶችም በበቂ ሁኔታ ወደ ክልሉ እየገቡ ነው ሲሉም ተናግረዋል።

በቀጣይነትም ሕዝቡን በማወያየትና ግንዛቤ የመፍጠር ከፀጥታ አካላት ጋር በትብብር የሚሠራውን ሥራ አጠናክሮ እንዲቀጥል ማድረግ ላይ ትኩረት ተደርጎ ይሠራል ብለዋል።

ክልሉን ከአንጻራዊ ሰላም ወደ ፍጹም ሰላም ለመለወጥም ሕዝቡ እንደከዚህ ቀደሙ ከጎናችን ተሰልፎ የሚያደርገውን ድጋፍ አጠናክሮ መቀጠል ይኖርበታል ብለዋል።

# "የኢኮኖሚ ነፃነታችንን ለማረጋገጥ ወጣቶች ለሥራ የተከፈቱ...

ከ1ኛው ገጽ የዞረ

በሳይንስ ሙዚየም እየተካሄደ ከሚገኘው የኢትዮጵያ ስታርት አፕ አውደ ርዕይ ጎን ለጎን በፈጠራ ሃሳቦች ላይ ትኩረት ያደረገ ጉባኤ ትናንት ተከናውኗል።

ሚኒስትሯ ወይዘሮ ሙፈሪሃት ካሚል፤ ያሉንን ሀብቶች በስፋት እስካልተጠቀምን ድረስ የኢኮኖሚ ነጻነታችንን ማረጋገጥ አንችልም ሲሉ በመድረኩ ገልጸዋል።

ኢትዮጵያ ደሃ ናት ብለው ለሚያስቡ በርካታ ዕምቅ አቅምና የፈጠራ ሃሳብ ያላቸው ወጣቶች መኖራቸውን ማሳየት ይገባል ያሉት ሚኒስትሯ፤ ወጣቶቹ ካለው ሰፊ የኢኮኖሚ ሀብት ጋር እንዲጣጣሙ በማድረግ የተሻለ ውጤት ማስመዝገብ እንደሚገባ አመላክተዋል።

ያሉን ጸጋዎች ላይ ማተኮር ይገባል ሲሉ የተናገሩት ወይዘሮ ሙፈሪሃት፤ በቴክኖሎጂ ፈጠራ ላይ በተመረኮዘ መንገድ ያልተገደቡ የኢኮኖሚ ሀብቶችን ማልማት ይገባል ብለዋል።

ማንኛውም ሀብታችንን ለመጠቀም የሚደረግ ጥረትና የሥራ ዕድል ፈጠራን ለመደገፍ መንግሥት ዝግጁ መሆኑን ተናግረዋል።

በዚህ ረገድ ወደሥራ የሚተረጎም አዲስ ሃሳብ ያላቸው ወጣቶች ሃሳባችን በኢትዮጵያ የሕግ ማዕቀፍ ስላልወጣለት ተግባራዊ አይሆንም ብለው እንዳያስቡ መንግሥት መፍትሔ አዘጋጅቷል ብለዋል።

አዲስ የፈጠራ ሃሳብ ያላቸው ወጣቶች ስለ ውጤታማነቱና ስለትርፋማነቱ ሳይጨነቁ በሙከራ ደረጃ ሃሳባቸውን ተግባራዊ የሚያደርጉበትን አሰራር መዘርጋቱን አመላክተዋል።

ኢትዮጵያ ያላትን ሰፊ የሰው ኃይል፣ ዕውቀትና ዘርፈ ብዙ ሀብት እንዴት አያይዘን እንጠቀም የሚለው ላይ ማተኮር ወሳኝ ነው፤ በዚህ ረገድ ውጤታማ ሥራ ለማከናወን መንግሥት በሕግ፣ በፖሊሲ፣ በፋይናንስ ፣ በአሰራርና በተለያዩ ጉዳዮች ላይ ጉልህ ማሻሻያ አድርጓል ብለዋል።

የገንዘብ ሚኒስትር ዴኤታ እዮብ ተካልኝ (ዶ/ር) በበኩላቸው እንዳመላከቱት፤ እንደሀገር ኢኮኖሚን ለማሳደግ ቴክኖሎጂ ላይ ትኩረት ተደርጓል፤ በዘርፉ ትልልቅ ሃሳብ ያላቸው ወጣቶች ላይ ኢንቨስት ማድረግ ከተቻለ ሰፊ ውጤት ይገኛል።

አዲስ የፈጠራ ሃሳብ ይዘው የሚመጡ ዜጎች የሙከራ ደረጃ ትግበራ ሂደትን የሚያሳልፉበትን መደላድል መፈጠሩን ጠቁመው፤ ማንኛውም አዋጭ የሆነ የፈጠራ ሃሳብ እንዲጎለብት የሚደረገው ጥረት ተጠናክሮ ይቀጥላል ሲሉ ለስታርት አፖች መልዕክት አስተላልፈዋል።

በመድረኩ በቴክኖሎጂ መስክ የፈጠራ ሃሳብ ባለቤቶች፣ ለስታርት አፖች የፋይናንስ ድጋፍ አቅራቢ ድርጅቶችና የተለያዩ የመንግሥት ሥራ አመራሮች ተገኝተዋል።

በሳይንስ ሙዚየም እየተካሄደ የሚገኘው የኢትዮጵያ ስታርት አፕ አውደርዕይ እስከ ሚያዚያ 20 ቀን 2016 ዓ.ም ድረስ ይቆያል።

# በኢሚግሬሽንና ዜግነት አገልግሎት...

ከ1ኛው ገጽ የዞረ

ድጋፍ አስፈላጊ መሆኑን ተናግረዋል።

የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት የሕግና ፍትሕ ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ ከትናንት በስቲያ በተቋሙ በመገኘት ድንገተኛ የመስክ ምልከታ ባደረገበት ወቅት የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት ሪፖርተሮችም በቦታው በመገኘት የተገልጋዮችን አስተያየት ጠይቀዋል።

በዕለቱ በፓስፖርት እድሳት ክፍል አገልግሎት ለማግኘት ከመቀሌ ከተማ የመጡት አቶ ጣዕመ ኃይሉ ከለሊቱ 11 ሰዓት በተቋሙ ተገኝተው ቢሰለፉም እስከ ረፋዱ 5 ሰዓት ድረስ አገልግሎት ማግኘት እንዳልቻሉ ይገልጻሉ። አገልግሎት ፈላጊውና አገልግሎት አሰጣጡ የተጣጣመ እንዳልሆነ የሚናገሩት ተገልጋዩ፤ አገልግሎት የሚሰጡት ሠራተኞች ጥቂት በመሆናቸው ለአላስፈላጊ እንግልት እየተዳረግን ነው ይላሉ።

የዚሁ ክፍል ሌላኛው ተገልጋይ የሆኑት አቶ አበበ በበኩላቸው፤ ፓስፖርት ለማደስ ከሁለት ቀን በፊት በቀጠሯቸው ቢገኙም ወረፋ ሳይደርሳቸው ቀርቶ በድጋሚ በዕለቱ ከለሊቱ 10 ሰዓት መምጣታቸውን ይናገራሉ። በርካታ ተገልጋዮች ለሰዓታት ወረፋ ቢጠብቁም አገልግሎት አሰጣጡ አዝጋሚ በመሆኑ አገልግሎት ማግኘት አለመቻላቸውን ይናገራሉ።

በተቋሙ ትክክለኛ መረጃ የሚሰጥ ያለመኖር፣መጸዳጃ ቤቱ ለበሽታ የሚዳርግ መሆኑ፣ጥሩ መቀመጫ እና ማረፊያ ያለመኖሩ በተቋሙ የተመለከቷቸው ችግሮች መሆናቸውን የሚገልጹት አቶ አበበ፤ ከዚህም በላይ ደግሞ በሰልፍ አስከባሪዎች ተገልጋዮች የሚደበደቡበት ሁኔታ በተቋሙ ያለውን የሥነ ምግባር ችግር ምን ላይ እንደደረሰ ማሳያ መሆኑን በምሬት ይናገራሉ።

በአሻራ ክፍል አገልግሎት ለማግኘት እየተጠባበቁ የነበሩት ስማቸው እንዳይጠቀስ የፈለጉ ተገልጋይ እንደሚሉት ደግሞ፤ በተቋሙ አገልግሎት ፈልጎ የመጣ ሰው ክብሩን ያልጠበቀ መስተንግዶ እየተሰጠው ነው። ተገልጋይ ዜጋ በመሆኑ አላስፈላጊ "መመነጫጨቅ" ሊደርስበት አይገባምም ይላሉ።

አገልግሎት የሚሰጡት ሠራተኞች ባጅ ባለማድረጋቸው መብት ለመጠየቅም አይመችም የሚሉት እኚሁ ተገልጋይ፤ ባለጉዳይ ተራ የሚጠብቅበት ዲጂታል መሳሪያ የማይሠራ በመሆኑ ተቋሙ ተገልጋይን ወረፋ የሚያስጠብቅበት መንገድ ኋላቀር መሆኑን ይናገራሉ።

የቋሚ ኮሚቴው ሰብሳቢ ወይዘሮ እፀገነት መንግስቱ በምልከታቸው አገልግሎቱ ከዚህ በፊት ይሰጥ ከነበረበት መንገድ አሁን መሻሻሎች መኖራቸውንና ተቋሙን ለማዘመን ጥረቶች መደረጋቸውን ገልጸው፤ አሁንም አገልግሎት አሰጣጡ ያልዘመነና መሻሻል ያለበት ነው ይላሉ።

አሁን ተቋሙ ያለበት ቦታ በጣም የቆየ በመሆኑ ቴክኖሎጂ በተገቢው ጥቅም ላይ ለማዋል አስቸጋሪ በመሆኑ ተገልጋዩን የሚመጥን ሰፊ ቦታ ተፈልጎ አገልግሎት መስጠት እንዳለበትም የገለጹት ወይዘሮ እጸገነት፤ ተቋሙ እጅግ በርካታ አገልግሎት ፈላጊ ያለበት እንደመሆኑ ተገልጋዮችን በአግባቡ የሚያስተናግድበት የቦታ ጥበት ችግር እንዳለበት መመልከታቸውንም ይገልጻሉ።

በተቋሙ ከፍተኛ ሰልፍ፣ ግፊያ እና መጨናነቅ መኖሩን መመልከታቸውን የሚገልጹት ወይዘሮ እጸገነት፤ ይህንን ማስተካከል የሚቻለው በአዲስ አበባ እና በክልሎች በርካታ ቅርንጫፎችን በመክፈት አገልግሎቱን በማስፋት እንደሆነ ይናገራሉ።

ትክክለኛ ፓስፖርት ማግኘት የሚቻለው በአዲስ አበባ ብቻ እንደሆነ ተደርጎ በአንዳንድ አካላት የሚሰራጨውን መረጃም ተጋግዞ ማረም እንደሚያስፈልግ ይገልጻሉ። ደላሎች ተገልጋዮችን መግቢያ በር አካባቢ " ፓስፖርት ቶሎ ይደርስላችኋል" በማለት ኅብረተሰቡን እንደሚበዘብዙ በምልከታው መረዳታቸውን የሚገልጹት ሰብሳቢዋ፤ ኅብረተሰቡ ከሕገወጥ ደላሎች እራሱን እንዲጠብቅም ይመክራሉ።

ግንዛቤ ለመፍጠር ተቋሙ ብቻ ሳይሆን የሁሉም ባለድርሻ አካላት ሚና አስፈላጊ ነው ያሉት ሰብሳቢዋ፤ 90ሺ ፓስፖርት ታትሞ ሳይወሰድ መቀመጡንም መመልከታቸውን ገልጸዋል፤ ኅብረተሰቡ በትክክል መረጃ አግኝቶ ፓስፖርቱ የሚወሰድበት ሁኔታ መፈጠር እንዳለበትም ጠቁመዋል። በተቋሙ የሠራተኛ ቁጥር መጨመር እንዳለበትና ችግሮችን ለማረምም ተቋሙን ዲጂታላይዝ በማድረግ ማዘመን አስፈላጊ መሆኑን አመላክተዋል።

ቋሚ ኮሚቴው በተቋሙ የተመለከታቸውና በፍጥነት መፈታት ያለባቸው ችግሮች ብሎ ያስቀመጣቸው ተገልጋይን በክብርና በአግባቡ ያለማስተናገድ እና የፓስፖርት ዕድሳት ክፍል ላይ ያሉ ሰልፎች ናቸው። እነዚህም አስቸኳይ መፍትሔ እንዲሰጥ አሳስቧል። በተጨማሪም የተገልጋዮች የመጸዳጃ ቤት ጽዳት በአግባቡ እንዲጠበቅ አስተያየቱን ሰጥቷል።

የኢሚግሬሽንና ዜግነት አገልግሎት ዋና ዳይሬክተር ወይዘሮ ሰላማዊት ዳዊት ቋሚ ኮሚቴው የሰጠውን አስተያየት እንደሚመለከቱት ገልጸው፤ ተቋሙ ያለበት ችግር በጣም ጥልቅ በመሆኑ የተሠሩና ቀሪ የቤት ሥራዎችን በደንብ በጋራ መመልከት እንደሚገባ ይጠቁማሉ።

ተቋሙ የቆዩ ችግሮች እንዳሉበት የሚገልጹት ዋና ዳይሬክተሯ፤ አንድ ዓመት ተኩል ተቋርጦ የነበረውን የፓስፖርት አገልግሎት ማስቀጠል የተቻለው በበርካታ ባለድርሻ አካላት ድጋፍ መሆኑን ያመለክታሉ። ተቋሙ በሪፎርም ሥራ 11 አጀንዳዎችን ቀርጾ እየሠራ መሆኑንና ችግሮችን ከመቅረፍ አኳያም የባለድርሻ አካላት ድጋፍ አስፈላጊ መሆኑን ያስረዳሉ። ቋሚ ኮሚቴው ቀሪ የተመለከታቸው ጉዳዮችን ከዘጠኝ ወር አፈጻጸም ጋር በምክር ቤቱ ለመገምገምም ቀጠሮ ይዟል።

የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት ተቋሙ የሚሰጣቸውን አገልግሎቶች በተመለከተ ከአንድ ወር በፊት ተገልጋዮችን በማነጋገር እና የተቋሙን ዋና ዳይሬክተር ምላሽ በማካተት ዘገባዎችን መሥራቱ ይታወሳል።

ወቅታዊ እና ቃለ ምልልሶች

# የዘመን እንግዳ

# “የራሳችንን የምግብ ፍላጎት ከማሟላት አልፈን ለውጪ ገበያ ማቅረብ የሚያስችል አቅም አለን”

## ፕሮፌሰር ዘሪሁን ወልዱ (ዶ/ር) የእጽዋት ስነ ምህዳር ተመራማሪ

**አስቴር ኤልያስ**

ቡልቂ፣ ተወልደው ፊደል የቆጠሩባት ትንሽዬ ከተማ ናት። ትምህርታቸውን የጀመሩት ቄስ ትምህርት ቤት ነው፣ እዛ እንዲገቡ የተደረገበት ዋናው ዓላማ ደግሞ ወደ ድቁናው እና ቅስናው እንዲመጡ ታስቦ ነው። ይሁንና ቄስ ትምህርት ቤት ጥቂት እንደቆዩ ወደመንግስት ትምህርት ቤት እንዲገቡ ተደረገ - የዛሬው የዘመን እንግዳችን ፕሮፌሰር ዘሪሁን ወልዱ (ዶ/ር)። እኚህ እንግዳችን፣ የትውልድ ስፍራቸው በቀድሞው አጠራሩ ጋሞ ጎፋ ጠቅላይ ግዛት፣ ጎፋ አውራጃ፣ ልዩ ስሟ ቡልቂ ተብላ በምትጠራ ከተማ ውስጥ ነው።

ትምህርታቸውን መማር የጀመሩት ገና በለጋ እድሜያቸው ነው። በቡልቂ ከተማ ውስጥ በወቅቱ የቄስ ትምህርት ቤትም ሆነ የመንግስት ትምህርት ቤት አገልግሎት የሚሰጡት በእኩልነት ነው። ሁለቱም ዘንድ የሚማሩ የተማሪዎች ቁጥር የሚተናነስ አይደለምና አስቀድመው በገቡበት የቄስ ትምህርት ቤት ፊደልን አሳምረው ከማወቃቸውም በላይ ማንበቡንም መጻፉን ተክነው መውጣት ቻሉ።

ጥቂት ጊዜ ከቆዩበት ከቄስ ትምህርት ቤት ወጥተው ከአንደኛ እስከ ስድስተኛ ክፍል ያለውን ትምህርታቸውን በቡልቂ አንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ተማሩ። ቀደም ብለው በቄስ ትምህርት ቤት ፊደል ቆጥረው ማንበብና መጻፉን በአግባቡ ተምረው ወደመንግስት ትምህርት በመግባታቸው ሁኔታዎች በጣም ቀለዋቸው እንደነበር እንግዳችን ይናገራሉ። ከዚህም የተነሳ ስድስት ዓመት ይፈጅ የነበረውን ከአንደኛ እስከ ስድስተኛ ክፍል ያለውን ትምህርታቸውን ያጠናቀቁት በአራት ዓመት ውስጥ ነው። ሰባተኛ እና ስምንተኛን ሳውላ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ተማሩ።

በተለይ የስምንተኛ ክፍል ውጤታቸው አመርቂ የሚባል ነበረ። በመሆኑም በወቅቱ ከስምንት ወደዘጠኝ ያለፉ ተማሪዎች ጥሩ ውጤት ያላቸው ከሆነ ተወዳድረው በዊንጌት ትምህርት ቤት መቀጠል የሚያስችላቸው እድል ነበርና እርሳቸውም ተወዳደሩ። በወቅቱ ቃለ መጠይቅ የተደረገላቸው በፈረንጆች አማካይነት ነበር። ይሁንና የእንግሊዝኛውን ቋንቋ ከፈረንጅ አፍ መስማቱ ለእርሳቸው እንግዳ ነገር ስለነበር በቅጡ ሊረዷቸው አልቻሉም። በዚሁ ምክንያት ሊሳካላቸው ባለመቻሉ ወደመጡበት ተመለሱ።

በወቅቱ በአንድ ጠቅላይ ግዛት ውስጥ የሚኖረው ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት /ሃይስኩል/ አንድ አሊያም ሁለት ቢሆን ነው። ስለዚህም የበጋሞ ጎፋ ጠቅላይ ግዛት የነበረው ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት አንድ ሲሆን፣ እርሱም የሚገኘው አርባ ምንጭ ስለነበር፤ ከዘጠነኛ ጀምሮ ያለውን ትምህርታቸውን ለመማር ወዲዚያው አቀኑ። የመጡትም ከሌላ ከተማ በመሆኑ በአርባምንጭ ከተማ ቤት መከራየት ግድ ሆነባቸው።

ቤት የተከራዩት በእድሜ ከእርሳቸው ከሚበልጡ ተማሪዎች ጋር በመሆኑ ተጽዕኖ የሚያደርሱባቸው ከመሆኑም በተጨማሪ ከእድሜያቸው ትንሽነት የተነሳ የራሳቸውንም ምግብ በቅጡ አብስለው መመገብ ያቅታቸው ነበር። ከዚህም በተጨማሪ ሙቀቱና ወባው ተደራርቦ የአርባ ምንጭ ቆይታቸውን በእጅጉ ፈታኝ እንዳደረገባቸው ይናገራሉ። የዚያን ጊዜ ቆይታቸው በሕይወታቸው ካጋጠማቸው ዋነኛው ፈታኝ ጊዜ እንደሆነም ያስታውሳሉ።

12ኛ ክፍል ሲደርሱ ሌላ እድል አጋጠማቸው። በወቅቱ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ስር የሚገኘው የበዕደማሪያም ትምህርት ቤት ተማሪዎችን ከ11ኛ ክፍል ይወስድና አንድ ዓመት አሰልጥኖ የ12ኛ ክፍል መልቀቂያ ፈተና ሳይፈትን በቀጥታ ወደዩኒቨርሲቲው እንዲቀላቀሉ የሚደረግበት ስርዓት ነበር። እንግዳችን ፕሮፌሰር ዘሪሁን፣ በወቅቱ ወደበዕደማርያም ሊያስገባ የሚችለውን ፈተና በአስደናቂ ሁኔታ አልፈው ትምህርት ቤቱን ተቀላቀሉ።

12ኛ ክፍልን በጥሩ ሁኔታ የተማሩት እንግዳችን፣ ምንም እንኳ የ12ኛን ክፍል መልቀቂያ ፈተና ሳይፈተኑ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲን መቀላቀል ቢቻልም እርሳቸው ግን ብቃታቸውን መፈተሽ ስለፈለጉ መልቀቂያ ፈተናውን ለመፈተን ቆረጡ። በወቅቱ ይፈተኑ የነበረው አምስት የትምህርት አይነት ሲሆን፣ ለዚህም ክፍያ ነበረውና ለእያንዳንዱ የትምህርት አይነት አምስት አምስት ብር በድምሩ 25 ብር ከፍለው ተፈተኑ፤ ባገኙትም ውጤት ለዩኒቨርሲቲም ብቁ መሆናቸውን አረጋገጡ።

በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ የአራት ኪሎውን የሳይንስ ፋኩልቲ ከተቀላቀሉ በኋላ ያጠኑት ምርጫቸው የሆነውን ባዮሎጂ ነው። በዩኒቨርሲቲው ሶስት ዓመት ከተማሩ በኋላ ለአንድ ዓመት ከዩኒቨርሲቲ ውጪ ኅብረተሰቡን ማስተማርና ማገልገል የሚያስገድድ የኢትዮጵያ ዩኒቨርሲቲ አገልግሎት (EUS) የሚባል መርሃግብር ስለነበር ለዚያ ተዘጋጁ።

ግዳጁም፣ ሕብረተሰብን ማገልገል ነበርና የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት መምህር ለመሆን ወደ ወለጋ ጠቅላይ ግዛት ጊምቢ ከተማ አቀኑ። ግዴታ የሆነውን ይህን አገልግሎት እንዳጠናቀቁም ወደዩኒቨርሲቲው ተመልሰው መማር እንደጀመሩ አብዮቱ ፈነዳ።

በወቅቱ እድገት በኅብረት የሚባለውን ዘመቻ በመቀላቀላቸው ምክንያት ዲግሪያቸውን ተምረው ያጠናቀቁት ከእነዚህ አገልግሎቶች በኋላ ነበር። እንዳጠናቀቁ ግን ጎበዝ ተማሪ ስለነበሩ እዛው ዩኒቨርሲቲ እንዲቀሩ ተደረገና መምህር መሆን ቻሉ።

ፕሮፌሰር ዘሪሁን፣ ሁለተኛ ዲግሪያቸውን የተማሩት በሚያስተምሩበት አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ሲሆን፣ ሶስተኛ ዲግሪያቸውን ያገኙት ደግሞ በሲውድን ኡፕሳላ ዩኒቨርሲቲ በእጽዋት ስነ ምህዳር ላይ ሰርተው ነው።

አዲስ ዘመንም ከእኚህ ከ90 በላይ የምርምር ጽሑፎችን ብቻቸውንና ከሌሎች ጋር በመሆን በዓለም አቀፍ ጆርናሎች ላይ ካሳተሙ አንጋፋ ምሁር ጋር ቆይታ አድርጓል። የዛሬው የዘመን እንግዳችን ፕሮፌሰር ዘሪሁን ወልዱ (ዶ/ር) ከ40 ዓመት በላይ የካበተ ልምድና ተሞክሮ ያላቸው፣ ተመራማሪና መምህርም ናቸው። ከእርሳቸው ጋር ያደረግነውን ቆይታ እንደሚከተለው አጠናቅረን አቅርበነዋል።



ፎቶ ፡ ዳኜ አበራ

**አዲስ ዘመን፡- በዕደማሪያም ተምሮ ዩኒቨርሲቲን ያጠናቀቀ ተማሪ ለተወሰነ ጊዜ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት የማስተማር ግዴታ እንዳለበት ይታወቃልና እርስዎ ዩኒቨርሲቲ ሲቀሩ ያንን ባለማድረግዎ ያጋጠመዎ ነገር የለም?**

**ፕሮፌሰር ዘሪሁን (ዶ/ር)፡-** እርግጥ ነው፤ በዕደማርያም የተማሩ ሁሉ ከዩኒቨርሲቲ ወጥተው የተማሩበትን ለማካካስ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ማስተማር ግዴታ አለባቸው። እኔ ደግሞ ለማስተማር የቀረሁት ዩኒቨርሲቲ ውስጥ ነው። ቆይታዬን ዩኒቨርሲቲ ውስጥ ካደረግሁ የተማርኩበትን ወጪ 550 ብር መክፈል ግዴታዬ ነበር። በመሆኑም ከዚህ ማምለጥ ስለማልችል ብሩን ከተለያየ ቦታ አሰባስቤ በመክፈሌ ከዕዳ ነጻ መሆን ቻልኩ።

ይህ ጊዜ 1969 ዓ.ም ነው፣ ከዚያን ጊዜ ጀምሮ እስካሁን ድረስ የቢሮ ለውጥ ሳላደርግ በአራት ኪሎ ዩኒቨርሲቲ አሁን ባየሻት ቢሮ ውስጥ እገኛለሁ። ምናልባት ከቢሮዋ የተለየሁበት ዘመን ቢኖር ለሶስተኛ ዲግሪ ወደስዊድን በሔድኩበት ጊዜ እና ለማጠናከሪያ ኮርሶች ወደጣሊያን ባቀናሁባቸው ጊዜ ብቻ ነው ማለት ይቻላል።

ሶስተኛ ዲግሪዬን የተማርኩበት የስዊድኑ ኡፕሳላ ዩኒቨርሲቲ፣ በእጽዋት ስነ ምህዳርና በአጠቃላይ ስለእጽዋት ትምህርት በዓለም አቀፍ ደረጃ የታወቀ በመሆኑ ታላላቅ ሰዎች የተመራመሩበትና የሰሩበት ነው። ልክ ሌሎች ተማሪዎች እንደሚያደርጉት ሁሉ በዚያው መቅረትን አማራጭ አላደረግኩም። ወደ አገሬ ተመልሼ ማስተማሬን ቀጠልኩ። ይሁንና በወቅቱ አገራችን የነበረችበትን ወከባ ሳጤነው በእርግጥ በመመለሴ “ስህተት ሰራሁ እንዴ?!” የሚል ሐሳብ ሰቅዞ ይዞኝ እንደነበር አልዘነጋም።

ይሁንና አገሬን ማገልገል እንዳለብኝ ስላመንኩ ማስተማሬን በችግር ውስጥም ቢሆን ቀጠልኩ። ሶስተኛ ዲግሪ አንድ ሰው ከሰራ በኋላ አንድ ዓመት ደግሞ ማጠናከሪያ በሚል መማር ስለሚቻል ለዚሁ ማጠናከሪያ ወደጣሊያን አቀናሁ። ይህን እድል ያገኘሁት ደግሞ ስዊድን ኡፕሳላ ዩኒቨርሲቲ በመማር ላይ ሳለሁ አብሮኝ በነበረ ጣሊያናዊ አማካኝነት ነው።

በጣሊያን የሚገኘው ትሬይስቴ ዩኒቨርሲቲ የሚያስተምረው ይህ ሰው፣ ባመቻቸልኝ እድል ማቲማቲካል ኢኮሎጂን ለመሰልጠን በቃሁ፤ ኡፕሳላ እንደሚታወቀው የስበት ማዕከል ነው። ተማራማሪዎች እየመጡ የሚያስተምሩበት ዩኒቨርሲቲ ነው፡። የጣሊያኑን አስተማሪ ያገኘሁትም በዚህ ምክንያት ነው።

**አዲስ ዘመን፡-እርስዎ በእጽዋዕትም ሆነ በተፈጥሮ ሀብት ጥበቃና እንክብካቤ ዙሪያ ብዙ አጥንተዋል፤ ተመራምረዋልም። ምን የተገኘ ውጤት አለ?**

**ፕሮፌሰር ዘሪሁን (ዶ/ር)፡-** የኢትዮጵያ ስነ ምህዳር መራቆት የጀመረው ከብዙ ሺ ዓመት በፊት ነው። አንድ ምሁር ዋናውና ትልቁ ተግባሩ የምርምር ውጤቶችን ማውጣት ነው። የሚተገብረው ደግሞ ሌላ አካል ነው። በእኔ በኩል ያለብኝን ግዴታ የተወጣሁ ይመስለኛል። ምክንያቱም የምርምር ጽሑፎችን ማውጣትና የሰው ኃይል መፍጠር ነው። እኔ ባጠናሁት ዘርፍ በኢትዮጵያ ባሉ ዩኒቨርሲቲዎች ዙሪያ የእኔ አሻራ አለ። በዩኒቨርሲቲዎች ብቻ ሳይሆን በተለያዩ ተቋማትም ጭምር ይህ አሻራ አለ። በትግበራ ውስጥም የእኔ ኃላፊነት መኖሩ እንደተጠበቀ ሆኖ ማለት ነው።

**አዲስ ዘመን፡- እንደ አገር በርከት ያሉ የምርምር ማዕከላት መኖራቸው ይታወቃል። ከአገሪቱ ፍላጎት አኳያ ሲታይ ግን ውጤታማ ናቸው ማለት አያስደፍርም። ምክንያቱ ምንድን ነው ይላሉ?**

**ፕሮፌሰር ዘሪሁን (ዶ/ር)፡-** በተወሰነ ሁኔታ ውጤታማነት አለ፤ ውጤታማነት ሙሉ ለሙሉ የለም ብሎ መደምደም አይቻልም። የተፈለገውን ያህል ውጤት ተገኝቷል ከተባለ ግን አነጋጋሪ ነው። ለምን የተፈለገው ውጤት መምጣት አቃተው? ከተባለ ኢትዮጵያን በተለያየ ዘመን ያስተዳደሩ መሪዎች የተለያየ ፍልስፍና ያላቸው ከመሆናቸው በተጨማሪ የፖለቲካ ዓላማቸውም የተለያየ በመሆኑ ነው። ከዚህ የተነሳ በአገራችን የተረጋጋ ዘመን ነበር ለማለት ይቸግራል።

የመንግስት ትኩረትና አስተሳሰብ እንዲሁም የሰው ኃይል ይቀያየራል። እስካሁን የመንግስት መስሪያ ቤት አንድ ወጥ ሆኖ ሊዘልቅ አልቻለም፤ ይለዋወጣል። አንድ የሆነ የትኩረት አቅጣጫ እና የተረጋጋ ነገር ኖሮ ቢሆን የተሻለ ውጤት ማስመዝገብ ይቻል ነበር። የሰከነ ፖሊሲ የወጣበት ዘመንም አለ ብዬ አላምንም። ስለዚህ ውጤቱ ሊቀንስ የቻለው በጥቅሉ የተረጋጋ ጊዜ ባለመኖሩ ነው ባይ ነኝ።

እንደሚታቀው የኢትዮጵያ ስነ ምህዳር የተጎሳቆለ ነው፤ ቢሆንም አቅሙ ግን ከፍተኛ ነው። ዛሬም ቢሆን ምግብ ለማምረት የሚያስችል አቅም አለው። ስነ ምህዳሩ እንዲያገግም በተቀናጀ መልኩ ቢሰራ ወደተፈለገው ውጤት እና ደረጃ መድረስ ይቻላል።

**አዲስ ዘመን፡- በኢትዮጵያ በተለይ ከቅርብ ዓመታት በኋላ በርካታ ዩኒቨርሲቲዎች ተቋቁመዋል፤ ግብርና ላይ ማዕከል ያደረገ ግን ጥቂት ብቻ ነው፤ የጀርባ አጥንቱ ግብርና ለሆነ አገር ይህን ማድረጉ ተጽዕኖ አይኖረውም? በዚህ ላይ ትኩረት ተደርጎ ያልተሰራበት ምክንያት ምንድን ነው ብለው ያስባሉ?**

**ፕሮፌሰር ዘሪሁን (ዶ/ር)፡-** ከዚህ በፊት አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ዋና ሆኖ በየጠቅላይ ግዛቱ ለምሳሌ የጎንደር ዩኒቨርሲቲ በጤና ኮሌጅ፣ በዓለማያ ግብርና ኮሌጅ፣ በሐዋሳ ሳተላይት ኮሌጅ፣ ቀረብ ባሉ ዓመታት ደግሞ አርባ ምንጭ ዩኒቨርሲቲ በውሃ እንዲሁም ሌሎችም በየዘርፋቸው በትኩረት የሚያስተምሩ ነበር። በመሃከሉ ዩኒቨርሲቲዎችን ለማስፋፋት ተብሎ በታሰበበት ጊዜ ትንሽ ስህተት የተፈጠረ ይመስለኛል።

ችግሩ ሁሉም የተቋቋሙ ዩኒቨርሲቲዎች የሚያስተምሩት ተመሳሳይ ትምህርት (Harmonization Principle) መሆኑ ነው። የሚማሩትም ስርዓተ ትምህርት አንድ አይነት ነው። አዳዲሶቹ ዩኒቨርሲቲዎች ብዙውን ነገር የቀዱት ከአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ነው። ስለዚህ ስርዓተ ትምህርቱ ሁሉ የአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ድግግሞሽና ቅጂ ነው። ትኩረት አድርገው በግብርናው በጤናው በውሃውና በሌላውም ይሰሩ የነበሩ ዩኒቨርሲቲዎች አሁን እንደ

ወደ ገጽ 7 ዞሯል

ወቅታዊ እና ቃለ ምልልሶች

## የዘመን እንግዳ

# "የራሳችንን የምግብ ፍላጎት ከማሟላት...



ከ6ኛው ገጽ የዞረ

አዳዲሶቹ ሁሉ ተመሳሳይ ትምህርት ማስተማር ውስጥ ገቡ።

ይህ ሃርሞናይዜሽን (Harmonization) የሚባለው ፖሊሲ ነው የትኩረት አቅጣጫን ያጠፋው። የማስተማሪያ ጽሑፎች ሁሉ የተቀዱት ከአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ነው። በአሁኑ ወቅት ግብርና የሚባለው ነገር ተመናምኖ በእያንዳንዱ ኮሌጅ እንደ አንድ አነስተኛ ዲፓርትመንት እየተሰጠ ነው። የሚደረገው የትምህርት ትኩረት በጣም የተመናመነ ነው። በግብርና ዘርፍ የሚያስተምረው የሰው ኃይል ሁሉ ተበታተነ። በአንጻሩ በጤና አካባቢ ያለው ደግሞ ደህና የሚባል ነው።

ወደነበረበት መምጣት የሚቻለው የተጀመረውን ተመሳሳይነት ያለው የትምህርት አሰጣጥን ሙሉ በሙሉ እርግፍ አድርጎ በመተው ነው። አለማያን ወደነበረበት የግብርና መመለስና ሌሎቹም ለምሳሌ በግብርናው ዘርፍ ልምድ ያላቸው እንደ ሐዋሳ፣ ጅማ ዩኒቨርሲቲዎችን እንዲሁ ማድረግ ነው። በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲም የደብረዘይቱ ኮሌጅ በራሱ የግብርና ነው። የእንስሳት ሕክምና ኮሌጁ ከዓለማያ ጋር ጎን ለጎን ይሰራ የነበረ ነው።

ተመሳሳይነት ያለውን ትምህርት ማስተማር ካልቀረ ሁሉም አንድ አይነት ስለሚሆን የሚጠቅም ዜጋ ለማፍራት አስቸጋሪ ይሆናል። ሙሉ በሙሉ ጥቅም ላይ መዋል የማይችል፤ ነገር ግን የምሩቃንን ቁጥር ብቻ ዳጎስ የማድረግ አካሔድ ይሆናል። ስለዚህ አንድ አይነት ሰው መፍጠር አስፈላጊ አይደለም። ለምሳሌ የሰመራ እና የጅግጅጋ ዩኒቨርሲቲዎች በመስኖ ዘርፍና በአርብቶ አደር ዙሪያ ስለሚካሔዱ እንቅስቃሴዎች ላይ ቢያስተምሩ መልካም ነው። ሌላውን አይማር ማለት አይደለም እነዚህ ላይ ቢያተኩር ለማለት ነው። የአካባቢውን ትኩረት ያማከለ ስልጠና መስጠት ለአገርም ለአካባቢም የተሻለ ነው።

**አዲስ ዘመን፡- በአሁኑ ወቅት ኢትዮጵያ በምግብ ራሷን ለመቻል እያደረገች ያለውን ጥረት እንዴት ያዩታል?**

**ፕሮፌሰር ዘሪሁን (ዶ/ር)፡-** ጥረቱ የሚደነቅ ነው። በኢትዮጵያ ላይ ስላለው የምግብ እጥረት በሰፊው የተነገረው በ1966 ዓ.ም ንጉሱ በወደቁበት ዘመን ነው። ከዛ በፊት ኢትዮጵያ ውስጥ የምግብ እጥረት አለ የሚባል ዜና አልነበረም። በእርግጥ ሊኖር ይችላል፤ አይነገርም እንጂ።

እኔ በዩኒቨርሲቲ የአንደኛ ዓመት ተማሪ በነበርኩበት ጊዜ ጂኦግራፊ ስንማር የኢትዮጵያ ሕዝብ ቁጥር 25 ሚሊዮን ብቻ ነበር። በአሁኑ ወቅት ከ120 ሚሊዮን የዘለለ ነውና ቁጥሩ በጣም እያሻቀበ መጥቷል። ከሕዝብ ቁጥር ማደግ ጎን ለጎን የምግብ ፍላጎትን የሚያሟላ ነገር መፈጠር አለበት። በ25 ሚሊዮንም ጊዜ ሆነ አሁን ረሃብ አለ።

የምግብ ፍላጎታችንን ማሟላት አለብን በሚል በመንግስት ደረጃ በፖሊሲ ተይዞ መነሳቱ እንዲያውም ቀደም ሲል መሆን የነበረበት ሲሆን፣ አሁን መሆኑም ቢሆን አትራፊ ነው።

በምግብ ራሳችንን መቻል እንችላለን። ምክንያቱም ብዙ ሊታረሱና ሊለሙ የሚችሉ ቦታዎች አሉን። ይህን ስናደርግ ደግሞ ያለውን ስነ ምህዳር ጠብቀን መሆን አለበት። የራሳችንን የምግብ ፍላጎት ካማሟላት አልፈን ለውጪ ገበያ ማቅረብ የሚያስችል አቅም አለን። ስለዚህ ይህ እንቅስቀቃሴ መጀመሩ በጣም የሚያበረታታ ነው፡።

እዚህ ላይ ግን ጥንቃቄ ማድረግ ያለብን ልማታችን በአንድ የሰብል አይነት ብቻ እንዳይሆን ነው። በአሁኑ ወቅት በስፋት እየተሰራበት ያለው ስንዴ ላይ ነው። ጤፍ፣ ገብስ፣ አተር እና ሌሎችም ላይ መስራት አለብን። የአንዱን ማሳ ለስንዴ ስናደርግ ያኛው የሰብል አይነት ሊወደድ ይችላል። ጤፍና አተሩ ለኢትዮጵያውያኑ ምግብ የሚያስፈልጉ ናቸው። ስለዚህ ለስንዴ የሚሰጠውን ያህል ትኩረት ለአተሩም ለባቄላውም ሆነ ለጤፉና ለሌሎችም ቢሰጥ አስተማማኝ ይሆናል።

ስንዴ የዓለም የምግብ ትኩረት ሊሆን ይችላል። ነገር ግን የምግብ ሉዓላዊነት የሚባል ነገር ደግሞ አለ። ሉዓላዊ ሕዝብ እንደመሆናቸው የምግብ ሉዓላዊነታችንንም በማስጠበቁ ረገድ ልንሰራ ይገባል። ይህ የምግብ ሉዓላዊነት በማዕከላዊ ኢትዮጵያ በእንጀራ፣ በሽሮ፣ በጎመን፣ በቅመማቅመም የሚገለጽ ነው፤ ወደደቡብ ሲመጣ ደግሞ እንሰትና ስራስር የምግብ ሉዓላዊነት የሚገለጽበት ነው።

ለምሳሌ አንድ ሶስተኛ የኢትዮጵያ ኅብረተሰብ ቢያንስ በቀን አንዴ የእንሰት ውጤት ይመገባል። ስለዚህ እንሰት ሊዘነጋ አይገባም። እንሰትን አላስተዋወቅንም፤ ገና ከኢትዮጵያ አልወጣም። ስለሆነም አሁን ራስን በምግብ ለመቻል የሚደረገው ጥረት ጥሩ ነው፤ ሚዛናዊነትን መጠበቅ ደግሞ አስፈላጊ ነው።

**አዲስ ዘመን፡- መንግስት እንደ አገር ኢንቨስት ያደረገባቸው ልምድ ያላቸው የዘርፉ ተመራማሪዎች በአገር ደረጃ ችግር ሲመጣ እንኳን ከልምዳቸው ተነስተው አያማክሩም። ይህ ከምን የመነጨ ይመስልዎታል?**

**ፕሮፌሰር ዘሪሁን (ዶ/ር)፡-** እንደ እኔ አተያይ ከሆነ ይህ ጉዳይ ከሁለት ምክንያት የመነጬ ነው። አንደኛው የመንግስት ባለስልጣናት የመቀያየርና አገር ውስጥ ያለውን እምቅ እውቀት መኖሩንም ያለመገንዘብ ሊሆን ይችላል። ሌላው ደግሞ ምሁሩ ራሱ ተሰባስቦ "አለን፤ እናማክር" ሊል ይገባል። አለመቀራረቡ የመጣው ከአንድ አቅጣጫ ብቻ ሳይሆን ከሁለቱም ወገን የጎደለ ይመስለኛል። መንግስትም ረጋ ብሎ አስቦ "በሰው ኃይል መቀያየር ምክንያት ያለኝን አቅም ዘንግቼው ይሆን?" ብሎ ሊያጤን ይገባል።

ምናልባትም "መንግስት አርቆኛል፤ ብዙም አላቀረበኝም" የሚለውን ቁዘማ ትቶ ደፍሮ መቅረብ የሚያስፈልገግ ይመስለኛል። ያንን ደግሞ የሚያሰባስብ ኃይል ቢኖር ጥሩ ነው። በዚህ መልኩ ከሁለት ወገን ለመቀራረብ ጥረት ማድረግ ነው እንጂ ዝም ብሎ በጉዳዩ ብቻ እየተቆጩ መኖር ለሕዝብም ለመንግስትም ሆነ ለወደፊቱ ትውልድ አይጠቅምም። በተለይ ትውልዱ ከአንጋፋ ምሁራን መጠቀም የሚችልበት ሁኔታ አሁን ነው። ምክንያቱም አንድ ሰው ዘላለማዊ አይደለም። ስለዚህ ውስን የሆነው ምሁር ልምዱን ሊያካፍል ይገባል።

**አዲስ ዘመን፡- ኢትዮጵያ በዓለም አቀፍ ደረጃ ከምትታወቅባቸው ምርቶች ዋነኛው ጤፍ ነው፤ አሁን አሁን ምርቱ ባህር ተሻግሮ በመሄዱ €€ምርቱ የእኛ ነው‹‹ የሚሉ ሀገራት ተፈጥረዋል። ከዚህ አኳያ ምን ይላሉ?**

**ፕሮፌሰር ዘሪሁን (ዶ/ር)፡-** የዓለም ሕግጋት አሉ። ጥቅም ማግኘት ለሚችሉ አካላት ጉዳዩ ክፍት መሆን አለበት። የራስን ብዝሃ ሕይወት ደብቆ አልሰጥም ማለት ግን አይቻልም። ያለውን ሕግ ጥሶ ደግሞ መኖር አይቻልም። እናም ከሌላው አገር እንወስዳለን። እነርሱም ከእኛ ይወስዳሉ።

በአገራችን የምንመገባቸው ብዙዎቹ ምግቦች ከሌላ አገር ያገኘናቸው ናቸው። ለምሳሌ ፓፓያ፣ ብርቱካን፣ ሙዝ፣ ድንች፣ ስኳር ድንች፣ ሽንኩርት፣ ቃሪያ የእኛ አይደሉም። ከሰጠናቸው ይልቅ የወሰድናቸው ይበልጣሉ። አሁንም የምናገኛቸው ሊኖሩ ይችላሉ።

በእርግጥ ስንዴም ሆነ ገብስ ከሌላ ቦታ የመጣ ይሁን እንጂ እዚህ ኢትዮጵያ ውስጥ የዳበረ ነው። እንዲያውም በአንድ ወቅት ከኢትዮጵያ የተወሰደ ገብስ የዓለምን ቢራ ከመጥፋት የታደገ ነው ይባላል። እንደሚታወቀው ገብስ በዋግ ይመታል። የአውሮፓንና የአሜሪካንን የቢራ ፋብሪካ ከመጥፋት ያደነው የዋግን በሽታ መከላከል የሚችል ገብስ ከኢትዮጵያ ተወስዶ ነው።

እሱ ሕጉ ከመውጣቱ በፊት ስለተወሰደ አሁን ልንጠይቅበት አንችልም። ሌሎች ብዙ ትኩረት ያልተሰጠባቸው የቅመማቅመም ዝርያዎችና እጽዋት አሉ። ነገር ግን እንሰትን ጨምሮ እነርሱን ማስተዋወቅ ይኖርብናል። ይህን ስናደርግ ከጥቅሙ ተካፋይ የምንሆንበትን ሁኔታ በማመቻቸት ነው።

ስለዚህ "ጤፍ የእኛ ነውና አንሰጥም፣ አናስነካም" ማለት አንችልም። ከጤፍ የሚገኘውን ጥቅም ግን መጋራት አለብን። ጤፍን የወሰደ አካልም ከእኛ ጋር የመጋራት ግዴታ አለበት። እንዲያውም ጤፍ አምራቾቹ ኢትዮጵያና ኤርትራ ናቸው ወደሚልም ተመጥቷል።

ይህ የመጋራት ጉዳይ ግን በእርግጥ አሁን የወጣ ሕግ ነው፤ ከዚህ በፊት ቃሪያ፣ ድንች፣ ሽኩርትና ሌላ ሌላውን ያገኘነው ከሕጉ በፊት በመሆኑ ነው። ይሁንና ከዚህ በኋላ ለሚሆነው እንጂ ወደኋላ ተመልሶ የሚጠይቀን የለም። እኛም ከዚህ በፊት ለወጣው ሳይሆን በቀጣይ ለሚወጣው እንዲሁ ተጠቃሚ የምንሆንበት አሰራር አለ።

ጤፍና ቡና እንዴት እንደተወሰሰዱ አይታወቅም፤ ከዚህ በኋላ ግን ሌሎች ለምሳሌ በቅመማቅመም እና በእንሰት ደረጃ ብዙ ብዝሃ ሕይወት ስላሉን ከእኛ የተወሰዱ ስለመሆናቸው ተረጋግጦ የዚያ ጥቅም ተካፋይ መሆን ያስችለናል ማለት ነው።

**አዲስ ዘመን፡- የዓባይ ግድብ አካባቢ የምንጣሮ ስራ ጥናት ላይ ተሳትፈዋል፤ ጥናቱ ምን ይመስል ነበር ?**

**ፕሮፌሰር ዘሪሁን (ዶ/ር)፡-** የዓባይ ግድብ በሚሰራ ጊዜ የደን ምንጣሮን በተመለከተ ሊደርስ የሚችለው ተጽዕኖ ምን ሊሆን ይችላል? በሚለው ጥናት ተካሄዷል። በወቅቱ የኢትዮጵያ ፓናል ኦፍ ኤክስፐርት የሚባል የግድቡ አማካሪም የጥናቱ አካል ነበር። በወቅቱ የደን ምንጣሮ ሊያድረስ የሚችለውን ተጽዕኖ አጥንቼ በስራ ላይ ውሏል።

ደኑ ባይመነጠር ሐይቁ ላይ ሊደርስ የሚችለው ተጽዕኖ ምን አይነት ነው? የሚለውን ነገር ስናጤን መመንጠሩና መነሳቱ ግዴታ መሆኑ ታውቆ ነው የተመነጠረው። መመንጠሩ ወሳኝ እና የግድ የሆነ ተግባር ነው።

በጉዳዩ ላይ ምርምርና ጥቆማ አድርጌያለሁ። ምን ያህል ደን እንደሚመነጠርም ጭምር። ከዚያ ከሚመነጠረው ደን ምን ያህል ክብደት ያለው የእጽዋት ስብስብ ነው የሚነሳው? ያ መነሳት ያለበት የእጽዋዕት ስብስብ እዛው ቢቀር ምን የሚያመጣው ጉዳትስ አለው? የሚለውንም ጭምር ለማየት እና ለማጥናት ሞክሬለሁ።

የደኑ መመንጠር ለሐይቁ ዘላቂነት ችግር እንዳይፈጥር ትልቅ ሚና ያለው ነው። ከእኛ አልፎ ደግሞ በሱዳን፣ በግብጽ በተለይም ደግሞ በዓባይ ውሃ ላይ ደኑ ባይመነጠር ኖሮ ትልቅ ጉዳት የሚያደርስ ይሆናል። ስለዚህ በእኛም በጎረቤቶቻችንን ላይም የሚያደርሰውን ጥፋት ደኑ በመመመንጠር መዳን አለበት። ደግሞም ግዴታም አለብን።

ደኑ ሳይመነጠር ውሃው ቢተኛ የሚያመጣው ከባድ ችግር አለ። ብስባሹ እዚያ ውሃ ውስጥ ያሉትን እንደዓሳ አይነት እንስሳትን ሊገድል ይችላል። ብስባሹ 'ሚቴይን' የተባለ አደገኛ ጋዝ ስለሚፈጥር የአየር ንብረት ለውጥ ሊያመጣ ይችላል። ሚቴይን የካርቦን ዳይ ኦክሳይድ ሃያ ጊዜ የአየር ንብረት ለውጥ የማምጣት ኃይል አለው። ከዚህ የተነሳ ውሃ ራሱ የባዮ ጋዝ ክምችት ሆነ ማለት ነው።

**አዲስ ዘመን፡- ለ47 ዓመታት ያህል በማገልገል ላይ ይገኛሉና አሁን ያሉበት ሁኔታ እንዴት ይገለጻል?**

**ፕሮፌሰር ዘሪሁን (ዶ/ር)፡-** በአሁኑ ወቅት እየሰራሁ ያለው በማስተማር እና በምርምር ስራ ላይ ነው። የማስተምረው የሁለተኛ እና የሶስተኛ ዲግሪ ተማሪዎችን ነው። ማስተማር ብቻም ሳይሆን የሚሰሯቸውን ምርምሮች መከታተልም ሌላው ስራዬ ነው፤ አማክራለሁም።

አሁን እያስተማርኩ ያለሁት ምንም እንኳ የእጽዋት ስነ ምህዳር ቢሆንም፤ በጣሊያኑ ትሬይስቴ ዩኒቨርሲቲ በሰለጠንኩበት ሒሳብ ነክ የሆነ በእጽዋት ቀመር ላይ ነው። ትሬይስቴ ዩኒቨርሲቲ በሕይወቴ ላይ ያመጣው ተጽዕኖ ቀላል አይደለም። ወደጣሊያን እንዳቀና እና እንድሰለጥን ካደረገኝ ከፕሮፌሰር ኢንሪኮ ፌዎሊ ጋር በርካታ ጽሑፎችን በዓለማቀፍ ጆርናሎች ላይ ለማሳተም በቅቻለሁ።

እነዚያ ጽሑፎችም በብዙዎቹ ተማሪዎች ዘንድ የሚጠቀሱ ናቸው። ለ12 ዓመታት በተከታታይ ለሁለት ለሁለት ወር ወደ ትሬይስቴ ዩኒቨርሲቲ አቀና ነበር። እኔ በስዊድን ከቆየሁበት ትምህርት ጥልቀት ይልቅ በጣሊያኑ ዩኒቨርሲቲ ያደረግኳቸው ጥናትና ምርምሮች ትልቅ ስፍራ የሚሰጣቸው ናቸው።

ከዚያ በኋላ ከፕሮፌሰር ኢኒሪኮ ጋር በመሆን ከአውሮፓ ሕብረት ለአራት ዓመት በብዙ ሺ ዩሮ የሚቆጠር እርዳታ ለምርምር ስራው ማምጣት ችለናል። ዋናው ስራችን በትግራይ፣ በወሎ ከአገራችን አልፎ ደግሞ በምስራቅ አፍሪካ በታንዛኒያ፣ በኬንያ የተራቆተ ስነ ምሕዳር የሚያገግምበት መንገድ ለመመራመር የሚያግዝ ድጋፍ መሰብሰብ ያስቻለ ነው። ይህም ስራ የዘለቀው ለአራት ዓመት ነው። እኔ ብቻዬንም ሆነ ከሌሎች ጋር በመሆን ሳሳትማቸው የነበሩ የምርምር ጽሑፎች ሁሉም የሚያጠነጥኑት ስለ ስነ ምህዳር ማገገም ላይ ነው።

**አዲስ ዘመን፡- ማስተላለፍ የሚፈልጉት መልእክት ካለ?**

**ፕሮፌሰር ዘሪሁን (ዶ/ር)፡-** ማስተላለፍ የምፈልገው መልዕክት፤ አንድ ምሁር ከመመራመርና ከማጥናት ጎን ለጎን ቁጭት ሊኖረው ይገባል። እኔ በመጀመሪያ ከውጭ አገር ትምህርቴን ጨርሼ ስመጣ የነበረኝን ቁጭት ሙሉ በሙሉ የማሟላት አጋጣሚውን አላገኘሁም፡። ነገር ግን እያንዳንዱ ሰው የተፈጠረበትንና የተማረበትን ዓላማ ለማሟላት በቁጭት ውስጥ መሆን አለበት።

እኔ ለምሳሌ ሕይወቴን ወደኋላ መለስ ብዬ የተቆጨሁትን በሙሉ አሟልቻለሁ ወይ ስል የዩኒቨርሲቲውን የመማር ማስተማር ሒደትና የሰው ኃይል ለመጨመር ያሰብኩትን ቁጭት ከሞላ ጎደል ያሟላሁ ይመስለኛል።

ከስነ ምህዳር ማገገም ጋር ያለኝን ቁጭት በተለያዩ አጋጣሚዎች ተሳክተዋል የሚል እምነት የለኝም። በእርግጥ አንድ ሰው ብቻውን በራሱ ምንም ነገር ማድረግ አይችልም። በማስተማሩ ዓለም የፈጠርኩት የሰው ኃይልም በዚህ ቁጭት ውስጥ ገብቶ የተቻለውን ማድረግ ይጠበቅበታል።

**አዲስ ዘመን፡- ፈቃደኛ ሆነው ከሕይወት ተሞክሮዎ ስላካፈሉን ከልብ እመሰግናለሁ።**

**ፕሮፌሰር ዘሪሁን (ዶ/ር)፡-** እኔም አመሰግናለሁ።

# የኢትዮጵያዊነት የትውልድ አደራ

**ቴልጌልቴልፌልሶር (የኩሽ አሸክታብ)**

የትውልድ አደራ በኢትዮጵያዊነት በትላንት በዛሬና በነገ የሚመነዘር የታሪክ ውርርስ ነው። ውርርሱ ከአንድ ወገን ብቻ የሆነ ሳይሆን ከእርስ በርስ መሰጣጣት፣ ከእርስ በርስ መተሳሰብ፣ ከእርስ በርስ መከባበር፣ ከእርስ በርስ መደማመጥ እና ከብዙሀነት ውስጥ የሚመዘዝ ሀገር ሰሪ፣ ትውልድ መሪ ቡዳኔ ነው። ይሄ ቡዳኔ በኢትዮጵያ ላይ በሶስት ትውልድ በኩል ተንጸባርቆ እናገኘዋለን። የመጀመሪያ የአድዋ ትውልድ ነው። አባቶቻችን የነበሩበት ትላንት ብለን የምንጠራው የአብሮነት ቡዳኔ።

ይሄ ቡዳኔ የዛሬውን ትውልድ ባለክብር ያደረገ፣ የነጻነትን ዘውድ ያስደፋ ከብዙዎች ብርሀንን የተፋ ቡዳኔ ነው። እኔን ከሌላው ሌላውን ከእኔ ያስተሳሰረ ፍቅር የዘነበበት፣ ኢትዮጵያዊነት ያበበበት ነበር። በሀሳባችን በኩል፣ በተግባራችን በኩል እያንዳንዳችን ስለሀገራችን አደራ አለብን። አደራው ሁሉም ለማንም የሚሰጠው የፍቅርና የመተሳሰብ አደራ ነው። ከአባቶቻችን በተቀበልን የእውነት እና የአብሮነት አደራ ወደዛሬ እንደመጣን ወደነገ የምንሄድበትንም በጎ መንገድ መጥረግ ግዴታችን ይሆናል።

የትዝታ ገሳ ለብሰን፣ በወፍ በረር አድዋን ስንቃኘው ..የካቲት 23 1888 የዛሬ መቶ ሀያ ስምንት ዓመት የተከሰተን የጥቁር አንበሶችን የጀግንነት ድል እናገኛለን። አግኝተንም አንቆምም ለምን? እንዴት? የሚሉ መጠይቆችን እንጠይቃለን። ጠይቀንም መዳረሻውን እኔና እናተን ያደረገ መልስ እናገኛለን። ሁለት በታሪክ፣ በባህል፣ በስልጣኔ፣ በአይዶሎጂ የተራራቁ ሀገራት ኢትዮጵያና ጣሊያን አንዱ በራስ ወዳድነት አንዱ ደግሞ ለነጻነቱ በጦርነት አውድማ ተገናኝተዋል።

ከመዲናችን አዲስ አበባ በስተ ሰሜን አቅጣጫ በ1065 ኪሎ ሜትር ርቀት ላይ በምትገኘው አድዋ ላይ የነጻነት ሰንደቃችንን ሰቀልን። ስለሀገርና ርስት፣ ስለነጻነትና እኩልነት፣ ስለሰውነትና ፍትህ የተከፈለ ይሄ ተቧድኖ በዛኛው ዘመን ለእኛ የተከፈለ የፍቅር ቡዳኔ ነው። ትላንት ብለን ዛሬን ስንቃኝ፣ ዛሬ ብለን ወደነገ ስናገድም አድዋ ፋና ወጊያችን ነው። አድዋ መቼት የለውም..መቼና የት የለውም። ጦርነቱ አድዋ ላይ ተጀምሮ ቢያበቃም የመላው ሕዝብ ጉዳይ ነበር። መቼ የሌለው..ከየት እስከየት የማይከነዳ፣ ሸንጠረጅም እንኸርርግ ብቸኛ ታሪካችን ነው ።

ቀጣዩ ቡዳኔአችን የአባይ ግድባችንን ይዘክራል። ከአድዋ ተነስተን ያረፍንበት የትስስብና የውዳዴ የብዙሀነትም አሻራችን ነው። ቁጭት ያበቃበት የተስፋ ብርሀን የፈነጠቀበት የድል አድራጊነት አርማችን ሆኖ በእያንዳንዳችን ልብ ውስጥ ተሰቅሏል። የዛሬ አስራ ሶስት ዓመት በጉባ ምድር መልህቁን ሲጥል እኛን አምኖ፣ በእኛ ታብዮ እንደሆነ ይታወቃል። እኛም ሳናሳፍረው እንሆ ማብቂያው ላይ አደረስነው።

በአሁኑ ሰዓት አጠቃላይ ሂደቱም 95 ከመቶ የደረሰ ሲሆን ሰባት ወራትን በሚሸፍን ሂደት ተጠናቆ ለአገልግሎት እንደሚውል ይጠበቃል። የግድቡ የሲቪል ስራ 99% የተጠናቀቀ ሲሆን የኤሌክትሮ ሜካኒካል የተርባይንና ጄኔሬተር ተከላ 78%፣ የግድቡ የውሀ ማስተላለፊያ አሸንዳ ከ85 ከመቶ በላይ መድረሳቸው አጠቃላይ ሂደቱን 95 ከመቶ አድርሰውታል። ግድቡ ሲጠናቀቅ በቀን እስከ 6 ሺህ ሜጋ ዋት፣ በዓመት ደግሞ 15 ሺህ 130 ጊጋ ዋት ኃይል እንደሚያመነጭ የሚታወቅ ሲሆን ይሄ የኃይል አሀዝ እንደሀገር፣ እንደሕዝብ፣ እንደትውልድ የኢኮኖሚ ሀይላችንንና የተሰሚነት ሚናችንን እንደሚጨምረው ሳይታለም የተፈታ ነው።

አፍንጫችን ስር በቅሎ በእልህ አክ እንትፍ ስንልበት፣ ጥርሳችንን ነክሰን ስናጉረመርምበት የነበረው ዘመን፣ 86 ከመቶ ያህሉን እያዋጣን ለባዕድ ሀገራት ጺጋ መሆናችን አብቅቶ በሕዝብ በሚሰጡ እጆች ለወግ ማዕረግ በቅተናል። እርግማንና ወቀሳችን ወደ ውዳሴ ተቀይሮ አባይ ክብራችን ነህ ወደ ማለት ተመልሰናል። ይሄ ታሪካዊ አሻራ በዚህ ትውልድ ላይ ሲደገም መነሻው አብሮነት ነው። አድዋን በፈጠሩ ሕብረብሄራዊ ልቦች አሻራችንን ስናስቀምጥ በምንም ሳይሆን በጋራ በርትተን ነው። ተሳስበንና ተጋግዘን፣ መክረንና ተወያይተን፣ አዋጥተንና ከመቀነታችን ላይ ፈትተን ያቆምነው የብዙሀነት ምስላችን ነው።

በዚህ ረድፍ ስር የሚነሳው ሌላኛው የተስፋችን ሰንደቅ የወደብ ባለቤትነት ጉዟችን ነው። ተፈጥሮና ታሪክ ካወራረሱን፣ ካዋሃዱንና ካቆራኙን ለስልጣኔአችን መሰረት ከሆነ ወደባችን ተቆራርጠን በተፈጥሮአችን ላይ ባይተዋር ሆነን ኖረናል። የሰው የማይነካ የራሱንም የማያስነካው ትውልድ ወደመነሻው ሊሄድ የወደብ አጋሩን ጥያቄን ይዞ ተነስቷል። ይሄኛው የትውልድ አሻራ ለጀመርናቸውና ልንጀምራቸው ላሰብናቸው የስልጣኔ ርምጃዎቻችን መንገድ የሚጠርግ፣ ያለንን ሰጥተን የሌለንን የምንቀበልበት፣ ፖለቲካዊና ኢኮኖሚያዊ ማህበራዊ ቁርኝትም የምንፈጥርበት ነው።

ሀገራችን በዓለም ላይ ካሉ 44 ወደብ አልባ ሀገራት መሀል አንዷን ነች። በአፍሪካም በ16 ከሚቆጠሩ የባህር በር ከሌላቸው ሀገራት ውስጥ ትመደባለች። ከመቶ ሚሊዮን የዘለለ የሕዝብ ቁጥር ኖሮት ወደብ አልባ የሆነ ሀገር በታሪክ የለም። ሀገራችን ብቻዋን የጠቅላላውን የወደብ አልባ ሀገር 1 ሶስተኛ የምትሸፍን ናት። የሕዝብ ቁጥር ፍሰቱ፣ የፍላጎት መናሩ፣ የኢኮኖሚ ግስጋሴው የባሕር በር ጥያቄው ተገቢ መሆኑን ከማመላከቱም በላይ ተቀባይነት እንዲኖረው የሚያስገድድም ጭምር ነው።

የባህር በር በአጭር ቋንቋ ቢገለጽ ‹የእድገት መሰረት› የሚል ይሆናል። ኢኮኖሚያዊና ፖለቲካዊ ዲፕሎማሲያዊም ፋይዳው እንዳለ ሆኖ እያደገ ለመጣው የሕዝብ ፍላጎትና ኢኮኖሚ እንደማስተንፈሻ ቦይነትም የሚያገለግል ነው። የባሕር በር ማጣት በአንድ ሀገር ላይ በኃይል መጥቶ መሄጃ እንደአጣ ጎርፍ ነው። ኢኮኖሚያችን፣ የሕዝብ ቁጥራችን፣ ፍላጎቶቻችን በኃይል መጥተዋል ከሌላው ዓለም ጋር በነጻነት የምንነካካበት የራስ መተላለፊያ ያስፈልገናል።

ከቀይ ባህር ጋር የነበረንን ታሪካዊና ተፈጥሮአዊ ቁርኝት እንድንበጥስ መንገድ ከጠረጉ ውሎች ውስጥ ዋነኞቹ የ1900፣ የ1902 እና የ1908ቱን የቀኝ ገዢዎች ውልን ማስታወስ እንችላለን። እነዚያ ውሎች በኃይልና በአስገዳጅነት የተፈጸሙ የአንድ ወገን የበላይነት የተንጸባረቀባቸው ውሎች ስለመሆናቸው ብዙዎች ምስክርነታቸውን ከመስጠት ባለፈ በሉአላዊ ሀገር ላይ የተፈጸመ ታሪካዊ ውንብድናም እንደሆነ የሚናገሩ ናቸው።

ያለ ቅኝ ተገዢዎች ፍቃድና ይሁንታ በመፈጸማቸው ውሎቹ በተባበሩት መንግስታት ማቋቋሚያ ቻርተር ላይ ተግባራዊነት እንደማይኖራቸው በግልጽ ሰፍሯል። ዓለም አቀፉ ሕግ ከፍትህና ከሚዛናዊነት አንጻር የሁለት ወገኖችን ፍቃድና ይሁንታ በማጤን መልስ የሚሰጥ እንደሆነ ይታወቃል። ኢትዮጵያና ጣሊያን የተፈራረሙት ውል እንዲሁም ደግሞ ኤርትራን ወክላ ጣሊያን የፈረመችው ስምምነት የወቅቱን የኢትዮጵያ ትክክለኛ ፍላጎት ያላማከለ፣ እንደ እንግሊዝና ፈረንሳይ ባሉ ሀገራት ጣልቃ ገብነት የተፈረመ እንደነበር ማስታወስ አስፈላጊም ጭምር ነው።

ዓለም አቀፉ ሕግ የባህር በር የማግኘትም ሆነ የመጠቀምን ነጻ መብት በሀገራት መካከል ይፈቅዳል። ከዚህ አኳያ ያነሳነው ጥያቄ ስህተት እንዳልሆነ እንገነዘባለን። ሌላ መጥቀስ ካስፈለገ ደግሞ በአንድ ዘመን ላይ ያለ የታሪክና የስልጣኔ ፈር ቀዳጅ የሆነን ይዞታ ነው እየጠየቅን ያለነው። በአንድም ሆነ በሌላ መልኩ የባህር በር ጉዳይ የትውልዱ ቀጣይ የቤት ስራው እንደሚሆን ሳይታለም የተፈታ ነው። ታሪክ መስራት የለመደው ትውልድ በአድዋ ጀምሮ በአባይ ደግሞ በቀይ ባህር ላይ ሊሰልስ አሀዱ ብሏል።

የባህር በር የአንድ ሀገርን 20 ከመቶ የኢኮኖሚ አሀዝ ይይዛል። ላለፉት ሰላሳና ከዛ በላይ ዓመታት እንደሀገር ይሄን እድል ሳንጠቀም ቀርተናል። የባህር በር ማግኘት የሕዝብን ጥያቄ፣ የኢኮኖሚ ግስጋሴውን፣ የደህንነት ጉዳይን፣ የዲፕሎማሲ ግንኙነትን ማሳለጥ ነው። አሁን ባለው ሀገራዊ ንቃት የባህር በር ማግኘት በኢኮኖሚ ግንባታ ላይ የላቀ ዋጋ ያለው ነው። የባህር መተላለፊያ በሁሉም ዘርፍ ላይ አሉታዊና አዎንታዊ

**ያለ ቅኝ ተገዢዎች ፍቃድና ይሁንታ በመፈጸማቸው ውሉቹ በተባበሩት መንግስታት ማቋቋሚያ ቻርተር ላይ ተግባራዊነት እንደማይኖራቸው በግልጽ ሰፍሯል። ዓለም አቀፉ ሕግ ከፍትህና ከሚዛናዊነት አንጻር የሁለት ወገኖችን ፍቃድና ይሁንታ በማጤን መልስ የሚሰጥ እንደሆነ ይታወቃል**

ተጽዕኖ ያለው መሆኑ እዚህ ጋ ሊነሳ የሚገባው ሌላው ጉዳይ ነው። የባህር በር ተጠቃሚ የሆኑ ሀገራት ፖለቲካዊና ኢኮኖሚያዊ አቅማቸውን ከማዳበር ባለፈ የደህንነት ዋስትናቸውንም ያረጋገጡ በተጽዕኖ ፈጣሪነትም ከፊት የሚሰለፉ ሀገራት ናቸው።

በተቃራኒው የባህር በር የሌላቸው ሀገራት በኢኮኖሚና በፖለቲካቸው ላይ ስጋትና ጣልቃ ገብነትን ከመፍጠሩም በላይ የሉአላዊነት ጉዳይን ጥያቄ ውስጥ የሚያስገባ ነገር ነው። ሉአላዊነት ለአንድ ሀገር፣ ለአንድ ሕዝብ፣ ለአንድ መንግስት የምንም ነገር መሰረት ነው። ይሄ ትልቅ ነገር ከወደብ ተጠቃሚ ሀገራት ይልቅ ወደብ በሌላቸው ሀገራት ላይ ስጋቱ ጎልቶ የሚታይ ነው። እኚህን ከመሳሰሉት ምክንያቶች በመነሳት የባህር በር ጥያቄአችን ተገቢና ወቅቱን ያማከለ እንዲሁም ደግሞ የማደግና የመለወጥ መሻታችንን ያማከለ ጉዳይ ነው።

ማጠቃለያ...

ኢትዮጵያ ትላንት ዛሬና ነገ በሚል በሶስት ትውልዶች ላይ ተንጠራርቼ ያስቃኘኋችሁ የጋራ አሻራዎቻችን በኢትዮጵያ አሁናዊ ሁናቴ ላይ ደማቅ ብርሀንን የፈነጠቁ ስለመሆናቸው ተጠራጣሪ አይኖርም። በአድዋ የነጻነት፣ የእኩልነት፣ የፍትሀዊነት እና የሰውነት ሚዛኖች ተብለናል። ይሄ ስም ከእኛ ውጪ በየትም የለም። ይሄ ክብር ከኢትዮጵያዊነት ጉያ ውስጥ ካልሆነ በየትም አልታቀፈም። ዛሬም ድረስ ስለዚህ ስምና ስለዚህ ክብር ፊተኞች ነን።

በአባይ ግድብ በኩል ሌላ ታላቅ ድልን እየተጎናጸፍን እንገኛለን። በአይችሉም ውስጥ ችለን፣ በአይሳካላቸውም ውስጥ አሳክተን፣ በአይሆንላቸውም ውስጥ ተያይዘን ማንነታችንን ያሳየንበት የዚህ ትውልድ የላብ አሻራ ነው። ትውል በጋራ አስቦ በጋራ የሚጽፈው የብዙሀነት ታሪክ እንዳለው ሰነዶች ይናገራሉ። ..ልክ እንደአድዋ ሁሉ የሕዳሴ ግድባችንም የብዙሀነታችን ማሳያ ምልክት ነው።

ሌላው የከፍታዎቻችንን ማማ ካረጋገጡልን ሁነቶች ውስጥ አንዱ የባሕር በር ጉዳይ ነው። ኢትዮጵያ ወደመነሻዋ እየተንደረደረች እንደሆነች በማመን ውስጥ እንድንቆም ካጸኑን ውስጥም ነው። ታሪክና ስልጣኔ፣ ዘመናዊነትና ኢትዮጵያዊነት ያበቡበት ጥንተ ጠዋታችን በከሰዓት እና በአመሻሻችን ላይ መጥቶ ዳግም ታሪክ እንድንሰራ፣ ዳግም እንድንዋሃድ፣ ዳግም እንድንበረታ ኃይል እያበጁልን ነው።

ስንነሳ ከማንም ቀድመን፣ ከማንም በፊት ነበር። በእኛ ፊተኝነት ውስጥ ሀገርና ሕዝብ የሆኑ ብዙ ናቸው። አሁን ላይ ኋላ ቀርተን ኋላ ቀር የሚል ስምን ከመጎናጸፋችን በላይ የድህነትና የአለመርባት ማሳያዎች ሆነናል። ለምን የሚሉ በርካታ ጥያቄዎች ቢኖሩም ወደመነሻችን እየወሰዱን ባሉ የጋራ አሻራዎቻችን ግን ተስፋ ወደማድረግ ተመልሰናል።

አድዋና ታላቁ የሕዳሴ ግድብ ከቀይ ባሕር እሳቤ ጋር ተጣምረው የለውጥና የተሀድሶ ተራማጅ አስተሳሰቦቻችን ወደ ሕዝባዊነት ቀይረው መድረሻዎቻችንን እያመላከቱን ይገኛሉ። በተስፋና በብርታትም እየሞሉን ይገኛሉ። መነሻችን ሰውነት መድረሻችን ኢትዮጵያዊነት ነው። ከዚህ አውድ ሳንወጣ ልዩነቶቻችንን በመሻራ በጋራ ታሪኮቻችን ፊት ነገን መልካም ለማድረግ እንቅስቃሴ ላይ ነን።

እንደ እኔነት ያሉ የተለማመድናቸውን አጉል ልምዶች ያለንን ከመቀማት ባለፈ እንዳልጠቀሙንና ከድህነት እንዳላወጡን ከገባን ሰንብቷል። ያጣነው መውጫ ቀዳዳ ነው። የራቀን ወደብዙሀነት የሚወስድ ፖለቲካና ፖለቲከኛ ነው። የጋራ ታሪኮቻችን ይሄን መንገድ በመክፈት የአንበሳውን ድርሻ በመውሰድ ወንድማማችነታችንን እያስመሰከሩልን ይገኛሉ።

በጀመርነው የብዙሀነት መንገድ ተጉዘን ጥንተ ጠዋታችን ላይ መድረስ፣ ብሔርተኝነትን ሽረን ኢትዮጵያዊነትን ማጠንከር፣ በጋራና በአብሮነት ድህነትን ከስሬ መንግሎ መጣል፣ ትውልድ በዘር ሳይሆን በሰውነት፣ በእኔነት ሳይሆን በብዙሀነት፣ በጥላቻ ሳይሆን በፍቅር ወደነገ እንዲሄድ ማበረታት የእኔ የእናንተ የሁላችን ግዴታ መሆኑን በማሳሰብ ላብቃ።

ፖለቲካና ወቅታዊ

# ተናጋሪው ዶሴ

## ድንበርተኞቹ

አስመረት ብስራት



እኛ ኢትዮጵያውያን የመሬትና የድንበር ጉዳይን የሕልውና ጥያቄ አድርገን እንወስደዋለን። ለነገሩ አያት ቅድመ አያቶቻችን እፍኝ አፈር ተዘግና ከሀገራችን እንዳትወጣ ሲሉ አይደል ከፍተኛ ተጋድሎ ያደረጉት። ይህ ጉዳይ ወደ ግለሰቦችም ወርዶ ደም አቃብቷል፡፡

ጎረቤታሞቹ በፍቅር ሲኖሩባት ከነበረች ሰፈራቸው አንዱ በሞት አንዱ በእስር እስኪለዩ ድረስ፤ ያጋጫቸው ከላይ ያነሳሁት የመሬት ጉዳይ እስኪነሳ ድረስ፤ በሠላም ይኖሩ ነበር፡፡ የኋላ ኋላ ግን ድንበርተኞች ድንበሬን ገፋህ አልገፋህ በሚል የከፋ ፀብ ውስጥ ገብተዋል። ይህ የድንበር ይገባኛል ጥያቄ ምክንያት የተነሳው ፀብ ስር ሰዶ ነፍስ እስከመጥፋት አድርሷል የሚለን ከአዲስ አበባ ፖሊስ የተዘጋ መዝገብ ያገኘነው መረጃ ነው።

እርቅን ያልወደደ ከሰይጣን የተዋደደ እንዲሉ አበው እርቅን ጠልተው ቂምን ሰንቀው የሰነበቱት፤ ለሽማግሌ ለያዥ ለገናዥ ያቃቱትን የእነዚህን ሁለት ሰዎች ታሪክ አነሆ ብለናል። መልካም ቆይታ።

### የዋሁ ቂመኛ

ጨዋታ የሚወድ ፈገግታ ከፊቱ የማይጠፋ ሰው ነበረ። ነገሮችን ቀለል አድርጎ የመመልከት ተሰጥዖ ያለው ከሁሉ ጋር በሰላም የመኖርን መርሕ የሚከተል አይነት ሰው ነው። ሩህሩህና ለጋስ የሆነው ይህ ሰው ደግነት መለያውም ነበር። ደግነት ሳያንሰው፤ የአንደበቱ ልስላሴ የበርካቶችን ልብ የሚገዛው ይህ ሰው በፀብ ከመጡበት ግን ሰይጣን ራሱ የሚቀናበት እልኸኛ ነበር። አንዴ ነገር ከጀመረ ዳር ሳያደርስ ማቆም የማይወድ ሁለት መልክ ያለው ይህ ግለሰብ የዋህነቱን የሚፈታተን ጉዳይ ገጥሞታል።

ከእንግዳ ተቀባይ ጎረቤቱ ጋር በሠላም፤ በመከባበር ሲኖር የቆየው ይህ ሰው አጥር በጋራ ለማጠር ከተነሱበት ቀን አንስቶ ነገር ሆዱ ገብታል። መሬቷ ከስልሳ ሳንቲ ሜትር ባትበልጥም መደፈሩ መናቁ አያንገበግበው የሚወደውን ጎረቤቱን በክፉ መመለከት ከጀመረ ሰነባብቷል።

ቀን ቀንን ሲጨምር ጥላቻው እየባሰበት ሲሄድ የቅርቡ ሰዎች ነገሩን ትተው በሠላማዊ መንገድ ችግራቸውን እንዲፈቱ ቢለምኗቸውም ፈቃደኛ ሳይሆኑ ቀርተው የማይበርድ ጠብ ውስጥ ገብቷል። ይህ ፀብ ስር ሰዶ የሕይወት ዋጋን እስከሚያስከፈል ድረስ ይህ ቂመኛው ሰው ሲወጣና ሲገባ ባላንጣውን በአይነቁራኛ ሲመለከት ቆየቷል።

### ባለ ከዘራው

ተግባቢ ነው፤ እንኳን ሰው ወፍ ያለምዳል የሚባል አይነት ሰው። በእድሩም በማኅበራዊ ሕይወትም ዋነኛ ተሳታፊ በሰፈሩ የታወቀ ግለሰብ ነበረ። አንድ ሰው ጎረቤቱ አዲስ ገዝቶ ሲገባ በተለመደው እንግዳ ተቀባይነቱ ተቀብሎ አካባቢውን አላምዶታል።

ቤቱን ሠርቶ እስኪያጠናቅቅ ያለውን የግንባታ መርጃ እቃ ከማበደር አንስቶ በሀሳብም በጉልበትም ሲያግዝ ቆይቷል። ሰው መጋበዝ ማብላት የሚወደው ይህ ሰው ጎረቤቱ ቤቱን ሠርቶ እስኪያጠናቅቅ ድረስ በተመቸው ቀን ሁሉ ምሳ እያሠራ ቡና እያስፈላ ከነሠራተኞቹ ሲንከባከብ ቆይቷል።

ቤቱ ተሠርቶ አልቆ ዙሪያው መታጠር እስኪጀምር ድረስ በጥሩ የወዳጅነት ሰሜት ሁለት ዓመታትን አሳልፈዋል። ልክ አጥሩ መታጠር ሲጀምርና የጋራ ድንበራቸው ላይ ሲደርስ ያለመግባባት ይፈጠራል። ሁለቱም የየራሳቸው ትክክልን ይዘው ቢነሱም እልኻቸው በትክክል ተነጋግረው እንዲግባቡ አላደረጋቸውም ነበር።

በቀላሉ ሊፈቱት የሚችሉትን ችግር በሁለቱም እልኸኝነት የተነሳ መቋጫው መጠፋፋት ሊሆን በቅተዋል። ተነጋገረው ቢስማሙ ለሁለት ተካፍለው ሊጠቀሙበት የሚችሉት መሬት ቢሆንም መነጋገር ባለመፈለጋቸው ምክንያት አንዱን ለሞት አንዱን ለአስር ያበቃ ፀብ አድርገውት አልፈዋል።

### ድንበርተኞቹ

በየካ ክፍለ ከተማ ወረዳ 10 አንቆርጫ ዳንሴ ሰፈር ተብሎ ከሚጠራው ሰፈር ቀድሞ የገባው ያሬድ ሰለሞን የተባለው ሰው ነበር። ቦታ ገዝቶ ቤት ሠርቶ መኖር ከጀመረ ከሁለት ዓመታት በኋላ ጉታ ከበደ የተባለ ሰው በቀኝ በኩል ቦታ ገዝቶ ይገባል። በወቅቱ ያሬድ የተባለው ሰው ማከፋያ አጥር ሳይሠራ በመቆየቱና የተነሳ አዲስ የገባውም ሰው ብዙም ሳይጨነቅ የገዛው ቦታ ላይ ግንባታውን ማከናወን ይጀምራል።

ቀድሞ የገባው ጎረቤቱን በጥሩ ሁኔታ ተቀብሎ ቤቱን ሠርቶ ቤተሰቡን እስኪያስገባ ድረስ በፍቅርና በመተጋገዝ ቆዩ። ግንባታው ተጠናቆ ዙሪያው ታጠሮ ከአቶ ያሬድ ጋር የሚያዋስነው አጥር ለማጠር ተነጋገሩ። የጋራ አጥራቸው በመሆኑም ሁለቱም በጋራ መሠረት አውጥተው የየራሳቸውን ብሎኬት ሊደረድሩ ተስማምተው ለሥራ የሚያስፈልገውን ቁሳቁስ በሙሉ አቀረቡ።

ቦታው ተለክቶ ሲባነ ሊዘረጋ ሲል ግን ቀድሞ የገዛው ሰው "የኔ ቦታ እዛ ድረስ ነው" ሲል። ይሄኛው ደግሞ "እኔ የገዛሁት ቦታው እዚህ ድረስ ነው" በማለት ክርክር ይገጠሙና ሽማግሌ መካከላቸው ገብቶ እንዲዳኛቸው በማለት የሆዳቸውን በሆዳቸው ይዘው ሥራውን ያስቆማሉ።

በሽማግሌም ሆነ በተለያዩ መንገዶች ተስማምተው መልካም ጉርብትናቸው እንዲቀጥል በርካታ ጥረቶች ቢደረጉም ተስማምተው ጉዳያቸውን በሠላም ከመጨረስ ይልቅ ፀብን ምርጫቸው አድርገው ሁለቱም በየፊናቸው ይዛዛቱ ጀመር።

የነበረው መከባበርና ፍቅር ጠፍቶ አንዱ ሌላውን ሊያጠፋ የሚዝት ከመዛትም አልፎ አሳቻ ቦታና ጊዜን የሚጠብቅ ሆነ። አጥሩም እንደ ነገሩ በመወታተፉ የተነሳ በወጡ በገቡ ቁጥር ንዴታቸው እየጨመረ በክፉ በመተያየት ለመጠፋፋት መፈላለግ ጀመሩ።

ቀን ደርሶ ተነጋግረው ችግራቸውን ከመፍታት ይልቅ ዱላ መሰናዘርን የመረጠው ያሬድ የተባለው ሰው ሌላውን ድንበረተኛውን ለመግደል አስቦ ሰኔ 19 ቀን 2014 ዓ.ም በግምት ከቀኑ 7፡00 ሰዓት ሲሆን በየካ ክፍለ ከተማ ወረዳ 10 አንቆርጫ ዳንሴ ሰፈር ተብሎ ከሚጠራው አካባቢ ጉታ ከበደን በነበራቸው ጸብ ምክንያት ቂም በመያዝ ለፀብ ይጋበዛል።

አንድ አንድ ሲባባሉ የቆዩት ሰዎች የያሬድ ንዴት ከፍ በማለቱ የተነሳ በያዘው ከዘራ ዱላ ከኋላ ጭንቅላቱን ደጋግሞ በመምታት ኮብልስቶን ንጣፍ ላይ እንዲወድቅ በማድረግ የራስ ቅሉ አጥንት እንዲሰበር በማድረጉ ጎረቤትዬው ሕይወቱን እንዲያጣ ያደረገው ሲሆን እሱም ማረፊያው እስር ቤት እንዲሆን አድርጎታል።

ተነጋግሮ መፍታት ያልተቻው የመሬት ጉዳይ አንዱን አፈር ውስጥ ሲያስገባ ሌላው ከአፈር በላይ በፀፀት ከቤተሰቡ ተለይቶ እንዲኖር አደረገው።

አካባቢው የደረሱና የሆነውን የተመለከቱ ሰዎች ጉዳዩን ለፖሊስ በማመልከታቸው የተነሳ ፖሊስ በአካባቢው ደረሰ። ሟች ወድቆ ገዳይም በሰዎች ተይዞ ያዙኝ ልቀቁኝ ሲል ይደርሳሉ። አስከሬኑን ለምርመራ ወደ ዳግማዊ ምኒሊክ ሆስፒታል ልከው ገዳዩን በቁጥጥር ስር በማዋል ምርመራቸውን ጀመሩ።

### የፖሊስ ምርመራ

ፖሊስ ጉዳዩን ከስር መሠረቱ ሲያጣራ መነሻቸው የድንበር ክርክር መሆኑን፤ ወዳጅ ዘመድ ጎረቤት በጉዳዩ ጣልቃ ሊገባ ቢሞክር እንኳን አሻፈረኝ ማለታቸውን፤ ከአንድ ዓመት በላይ በመጠላላት ሲተያዩ መቆየታቸውን ይረዳል። በእለቱም ገዳይ አልሞና አስቦ ሊያጠቃ የሚችልበትን ከዘራ ይዞ መውጣቱን የዓይን አማኞች ለፖሊስ አብራርተዋል።

እለቱ ጭቅጭቅ ያለ ዝናብ የሚዘንበበት ፀሐይ ያልታየበት ቀን ነበር። ሰኔ 19 ቀን 2014 ዓ.ም። ያን እለት ቤቱ ተኝቶ የዋለው ሟች ዝናቡ አረፍ ሲል እግሬን ላፍታታ ብሎ ይወጣል። በግምት ከቀኑ 7፡00 አካባቢ ነበር። የሟችን ከቤት መውጣት የተመለከተው ያሬድ ሰለሞን የተባለው ተከሳሽ ሟችን ለመግደል አስቦ ነበር ከቤቱ ተዘጋጅቶ የወጣው። ቦታው አንቆርጫ ዳንሴ ሰፈር ተብሎ ከሚጠራው አካባቢ ነበር።

ፖሊስ እንደሚለው ቀደም ሲል ከሟች ጉታ ከበደ ጋር በመሬት ጉዳይ በነበራቸው ፀብ ምክንያት ቂም በመያዝ በከዘራ ዱላ ከኋላ ጭንቅላቱን ደጋግሞ በመምታት ኮብልስቶን ንጣፍ ላይ እንዲወድቅ በማድረግ የራስ ቅሉ አጥንት እንዲሰበር በማድረጉ በሕክምና ሲረዳ ቆይቶ ሕይወቱ ያለፈ መሆኑን በመረጃዬ ደርሼበታለሁ ብሏል።

በምርመራውም መሠረት ገዳይ ሆን ብሎ አስቦ የሰው ነፍስ በማጥፋቱ የተነሳ በፍትሕ ሚኒስቴር የጠቅላይ ዐቃቤ ሕግ ዘርፍ የልዩ ልዩ ወንጀል ጉዳዮች ዳይሬክቶሬት ዐቃቤ ሕግ በ1996 ዓ.ም በወጣው የወንጀል ሕግ አንቀጽ 539/1/ሀ/ መሠረት በፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ልደታ ምድብ 2ኛ ግድያና ከባድ ውንብድና ወንጀል ችሎት በከባድ ሰው መግደል ወንጀል ክስ እንዲቀርብበት ይደረጋል።

ፖሊስ የፎረንሲክ ምረመራውን፤ የተከሳሽን የእምነት ክህደት ቃል፤ የአይን እማኞችን ቃል በመቀበል ጉዳዩ በሕግ ፊት ትልቅ ቦታ እንዲሰጠው ያደርጋል ያለውን ማስረጃ በሙሉ አሟልቶ በፍትሕ ሚኒስቴር የጠቅላይ ዐቃቤ ሕግ ዘርፍ የልዩ ልዩ ወንጀል ጉዳዮች ዳይሬክቶሬት ዐቃቤ ሕግ ይልካል።

### የዐቃቤ ሕግ የክስ ዝርዝር

በፍትሕ ሚኒስቴር የጠቅላይ ዐቃቤ ሕግ ዘርፍ የልዩ ልዩ ወንጀል ጉዳዮች ዳይሬክቶሬት ዐቃቤ ሕግም የደረሰውን ማስረጃ በመመልከት በዚህ መልኩ የክስ ዝርዝሩን ያቀርባል።

ያሬድ ሰለሞን የተባለው ተከሳሽ ሰውን ለመግደል አስቦ ሰኔ 19 ቀን 2014 ዓ.ም በግምት ከቀኑ 7፡00 ሰዓት ሲሆን በየካ ክፍለ ከተማ ወረዳ 10 አንቆርጫ ዳንሴ ሰፈር ተብሎ ከሚጠራው አካባቢ ከሟች ጉታ ከበደ ጋር በመሬት ጉዳይ በነበራቸው ፀብ ምክንያት ቂም በመያዝ በከዘራ ዱላ ከኋላ ጭንቅላቱን ደጋግሞ በመምታት ኮብልስቶን ንጣፍ ላይ እንዲወድቅ በማድረግ የራስ ቅሉ አጥንት እንዲሰበር በማድረጉ በሕክምና ሲረዳ ቆይቶ ሕይወቱ ያለፈ በመሆኑ በፍትሕ ሚኒስቴር የጠቅላይ ዐቃቤ ሕግ ዘርፍ የልዩ ልዩ ወንጀል ጉዳዮች ዳይሬክቶሬት ዐቃቤ ሕግ በ1996 ዓ.ም በወጣው የወንጀል ሕግ አንቀጽ 539/1/ሀ/ መሠረት በፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ልደታ ምድብ 2ኛ ግድያና ከባድ ውንብድና ወንጀል ችሎት በከባድ ሰው መግደል ወንጀል ተከሶ ብይን ይሰጥልኝ ሲል የጠይቃል።

### ውሳኔ

በፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ልደታ ምድብ 2ኛ ግድያና ከባድ ውንብድና ወንጀል ችሎትም በክርክሩ ሂደትም የዐቃቤ ሕግ ማስረጃ ከተሰማ በኋላ ተከሳሽ እንዲከላከል ብይን ተሰጥቶት ነበር።

ተከሳሽ የመከላከያ ምስክር አቅርቦ ያሰማ ቢሆንም በዐቃቤ ሕግ የቀረበበትን ክስ መከላከል ባለመቻሉ ምክንያት ፍርድ ቤቱ በተከሳሽ ላይ የጥፋተኛነት ፍርድ በመስጠትና የቅጣት ውሳኔ ለማሳለፍ ቀን ቆርጧል።

በፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ልደታ ምድብ 2ኛ ግድያና ከባድ ውንብድና ወንጀል ችሎት በዋለው ችሎት ላይ ተከሳሹን ጥፋተኛ በማለት በ14 ዓመት ከ3 ወር ጽኑ እስራት እንዲቀጣ ሲል ወስኗል፡፡

ኢኮኖሚ

# ስኬት

# የወጣትነት አቅምን አሟጦ በመጠቀም የተገኘ ስኬት

**ፍሬሕይወት አወቀ**

ወጣትነት ብርታት፣ ጥንካሬ፣ ድፍረትና እምቅ አቅም አለው። ሞራልና ልበሙሉነትም በመስጠት በኩልም ይታወቃል። ይህን ዕምቅ አቅም አጭቆ የያዘን ወጣትነት ስንቶች በአግባቡ ተጠቅመውበት ይሆን?... መልሱን ለናንተው እያልኩ ይህን ለዛሬ ስለ አንድ ብርቱ ወጣት የስኬት መንገድ እንጨዋወት።

‹‹ወጣት የነብር ጣት›› እንዲሉ ጥቂት የማይባሉ ወጣቶች በእዚህ እድሜያቸው ከላይ ታች ብለው ሕይወታቸውን ለመለወጥና ለማሻሻል ሲማሩ፣ ዕውቀት ሲሸምቱ፣ ሙያዎችን ሲቀስሙና ሲለምዱ ከአንዱ ሥራ ወደ አንዱ፣ ከአንዱ አካባቢ ወደ ሌላው ሲሉ ይስተዋላሉ። በዚህም ራሳቸውን ከመቻል አልፈው ሃብት ንብረት አፍርተው ለሌሎች ሲተርፉ ይታያሉ።

የዕለቱ የስኬት እንግዳችንም ገና ከአፍላ የወጣትነት ዕድሜው ጀምሮ ‹‹ሕይወት ትግል ናት፤ ታገላት›› ከሚለው አባባልም ባለፈ በተግባር የመኖር ዕጣ ፈንታ ገጥሞታል። በመሆኑም ከዝቅታው ዝቅ ብሎ ለከፍታው እየተንደረደረ የወጣትነት ዕምቅ አቅሙን አሟጦ ተጠቅሟል። በአፍላነት ዕድሜው የገጠሙት ፈተናዎች ብርቱና ጠንካራ ሰው ሆኖ እንዲሠራ እንዳደረጉት ይናገራል።

በሕይወት ከባድ ትግል ውስጥ የገባው ገና በለጋነት ዕድሜው ወላጅ እናቱን በሞት በተነጠቀበት ወቅት ነው። በወቅቱ በልቶ ጠጥቶ ለማደር፣ መሠረታዊ ፍላጎቱን ለማሟላት ሥራ ማግኘት አማራጭ የሌለው ምርጫው ነበርና ራሱን ለሥራ አሳልፎ በመስጠት ያገኘውን ሁሉ መሥራቱን ተያያዘው።

ሥራን ገና በለጋነት ዕድሜው የጀመረው እንግዳችን የትውልድ አካባቢው ኢሉባቦር መቱ ቢሆንም፣ የትምህርት ጊዜውን ጨምሮ አብዛኛውን የልጅነት ዕድሜውን ያሳለፈው በደሴ ከተማ ነው። ነፍስ ካወቀበት ጊዜ ጀምሮ ደሴ ከተማ ላይ ብዙ ቢቆይም፣ እንጀራ ፍለጋ በተለያዩ የሀገሪቱ አካባቢዎች ተዘዋውሯል፤ ክፉና ደግ የለየባትን ደሴ ከተማን ጨምሮ ወልቂጤ፣ ድሬዳዋ፣ ባሕርዳርና አዲስ አበባ ከተማ ድረስ ማንም ሳይኖረው ተዘዋውሮ በመሥራት ራሱን ኑሮን ለማሸነፍ ተፍጨርጭሯል።

የ12ኛ ክፍል ትምህርቱን በደሴ ከተማ በወይዘሮ ስህን ትምህርት ቤት ባጠናቀቀ ማግስት የእንጨት ሥራ ሙያን ተዋውቋል። ይህ ብርቱ ሰው የዕለቱ እንግዳችን ወጣት ዐቢይ ወልደሐና ነው። የሶሊና ሾፒንግ ሴንተር መሥራችና ባለቤትም ነው። የእንጨት ሥራ ሙያን ለመልመድና ለመሥራት የወሰነው እንዲህ እንደዛሬው ታዋቂ እንጨት ቤት እከፍታለሁ በሚል ሃሳብ አልነበረም።

ለመኖር ባደረገው ብርቱ ጥረት በእንጨት ቤቶች ዙሪያ ያገኘውን ሥራ ሁሉ ሲሠራ ቆይቷል። ሌላ ሥራ የለም የተባለ ያህል የእንጨት ሥራውን የሙጥኝ ብሎ ከአንዱ ቤት ሌላኛው ቤት፤ ከአንድ አካባቢ ወደ ሌላ አካባቢ እየተዘዋወረ በእንጨት ሥራው ላይ ቆይቷል።

ዛሬ በተለይም በሶፋ ምርቶቹ ስመጥር ከሆኑ ሶፋ ቤቶች መካከል አንዱ የሆነው ሶሊና ሾፒንግ ሴንተርን ማቋቋም የቻለው ወጣት ዐቢይ፤ ትናንት በወጣትነት ሙቅ ልቡ ለሙያው ብዙ ዋጋ ከፍሏል። የገጠሙትን መሰናክሎች ሁሉ ግን በትዕግስት አልፏል። ከቦታ ቦታ እየተንቀሳቀሰ በሠራባቸው 19 ሶፋ ቤቶች በአንዳቸውም ትችላለህ አልተባለም። ‹‹አትችልም›› ተብሎ ተባረረ እንጂ፤ በእዚህ ሁሉ የተነሳ ግን ተስፋ አልቆረጠም፤ ተዘዋውሮ በሠራባቸው አካባቢዎች ሁሉ ሙያውን ለማሻሻል ከፍተኛ ጥረት ሲያደርግ ቆይቷል። ድካሙ፣ ልፋቱ፣ ትጋቱና መውተርተሩም ሌባ የማይሰርቀውን የእጅ ሙያ አስታጠቀው።

ከዕለት ዕለት በሙያው ይበልጥ እየተሳበና ሙያውን እያፈቀረ የሄደው ዐቢይ፤ በሥራው ተቀባይነትን ከማግኘት ባለፈ የእንጨት ሥራ በተለይም የሶፋ ሥራ የነብሱ ጥሪ መሆኑን ማረጋገጥ እየቻለ መጣ። በተለያዩ አካባቢዎችና ቤቶች ተዟዙሮ ቢሠራም፣ ሥራ ብሎ የሚፈልገው ያንኑ የእንጨት ሥራ እንደነበር ያስታውሳል። በተዘዋወረባቸው የተለያዩ ክልሎችና አካባቢዎች በአጫጭር የጊዜ ቆይታ 19 ቤት ተቀጥሮ ሠርቷል።

ተስፋ ያልቆረጠው ወጣቱ ዐቢይ፤ አዲስ አበባ



ወጣት ዐቢይ ወልደሐና

ሲመጣም ሌላ ሥራ አልተመኘም። እንጨት ቤቶችን እያሰሰ እንዲያሠሩት ተማጽኗል። በከተማዋ በሚገኙ ሶፋ ቤቶች በተለይም ፒያሳ አካባቢ የመሥራት አጋጣሚ ሲያገኝ እንደተለመደው ‹‹አትችልም›› ተብሏል።

እሱ ግን ‹‹ትዕግስት ፍሬዋ ጣፋጭ ነው›› እንዲሉ ሁሉንም በትዕግስትና በብዙ ጥረት አልፎ መቻሉን አስመስክሯል። ‹‹አትችልም›› ተብሎ ከተባረረበት ሶፋ ቤት መቻሉን በተግባር አረጋግጦ በድጋሚ ተቀጥሮ የመሥራት ዕድሉን ያገኘበት አጋጣሚም ነበር። ይህን አጋጣሚ ሲያስታውስ ‹‹ወቅቱ በሕይወት ጉዞዬ ማርሽ ቀያሪ ክስተት የተፈጠረበት ነበር›› በማለት ነው።

በወቅቱ የተለያዩ የሙያ ጓደኞችን ያፈራው ወጣት ዐቢይ፤ እሱን ጨምሮ አራት ጓደኛሞች ሆነው የሶፋ ሥራ ለመሥራት የተቀጠሩት ከዚህ ቀደም ተቀጥሮ ሲሠራ አትችልም ተብሎ የተሰናበተበት ሶፋ ቤት ነበር። ያም ቢሆን በራስ መተማመን ያዳበረ በመሆኑ ስጋት አልገባውም፤ መቻሉን ለማስመስከር ከፍተኛ ጥረት አድርጓል። ከጥቂት ቆይታ በኋላ ጓደኞቹ ጥለው ሲሄዱ መቻሉን ያስመሰከረው ዐቢይ ግን፤ ቆይታውን አራዝሞ የተሰጠለትን ሙያ ዳር ለማድረስ ራዕይ ሰንቆ መሥራቱን ቀጠለ። ለራዕዩ መሳካትም በወቅቱ ሁለተኛ ዕድል ሰጥቶ ሲያሠራው የነበረው ሰው ትልቅ ድርሻ እንዳለው አጫውቶናል።

አሠሪው የሰጠውን ምክር መነሻ በማድረግ አንድ ሶፋ ሠርቶ ከሚያገኘው ገንዘብ ላይ የተወሰነውን በመቆጠብ ራዕዩን ለማሳካት ከፍተኛ ጉጉት ያሳየው ወጣት ዐቢይ፣ በሁለትና በሦስት መቶ ብር ቁጠባውን አጠናክሮ በመቀጠል ዓመት ባልሞላ ጊዜ ውስጥ ስምንት ሺ ብር መቆጠብ ቻለ፤ ተከራይቶ በሚኖርበት ግቢ ውስጥ በ15 ቀናት ውስጥ አንድ ሶፋ ሠርቶ 9500 ብር ሸጠ። እንዲህ እንዲህ እያለ ሥራውን ማሳደግ የቻለው ዐቢይ፤ ተቀጥሮ ከሚሠራበት ሶፋ ቤት ወጥቶ የግል ሥራውን ‹‹ሀ›› ብሎ በመጀመር ዛሬ በተለይም በሶፋ ምርቱ ዕውቅናን ማትረፍ ችሏል።

በ2002 ዓ.ም ፒያሳ አካባቢ 450 ብር በተከራየው ቤት ሶፋ ማምረት ሲጀምር ዛሬ ላይ ለመድረሱ እርግጠኛ ነበር። በወቅቱ ሁለት ሠራተኞችን ቀጥሮ ሥራውን ሌት ተቀን ሳይል በከፍተኛ ተነሳሽነት ሲሠራ ቆይቷል። ‹‹ቀስ በቀስ እንቁላል በእግሩ ይሄዳል›› እንዲሉ ሽሮ ሜዳ አካባቢ ሰፋ ያለ ቦታ ተከራይቶ ሥራውን በማስፋት የሠራተኞቹን ቁጥርም ከሁለት ወደ ሦስት፣ አራት አምስት እያለ ዛሬ ሶሊና ሆም ሾፒንግን በማቋቋም ከ380 ለሚልቁ ዜጎች ቋሚና ጊዜያዊ የሥራ ዕድል መፍጠር ችሏል።

በአሁኑ ወቅት ሙሉ የቤት ዕቃዎችን እያመረተ የሚገኘው ሶሊና ሆም ሾፒንግ፣ በዋናነት የሚታወቀው በሶፋ ምርቶቹ ነው። ከሶፋ በተጨማሪም ወንበሮች፣ የምግብ ጠረጴዛዎች፣ አልጋዎች፣ ቁምሳጥኖችና የቴሌቪዥን ማስቀመጫዎችን ያመርታል። ሌሎች ሲኒ፣ ብርጭቆ፣ ሹካ፣ ማንኪያ፣ መመገቢያ ሳህኖችን ጨምሮ የተለያዩ ደረጃቸውን የጠበቁ የቤት ዕቃዎችን እንዲሁም ኤሌክትሮኒክስ የሆኑ የቤት ውስጥ መገልገያዎችን ደግሞ ከአውሮፓ በማስመጣት ለገበያ ያቀርባል።

ሶሊና ሆም ሾፒንግ የተቋቋመበትን ዓላማ እያሳካ የመጣ ድርጅት ስለመሆኑ ያነሳው ዐቢይ፤ ድርጅቱ መጠነኛ በሆነ ትርፍ ብዙ ማምረትና በስፋት ገበያ ውስጥ መግባት የሚል ዓላማ ይዞ የተነሳ ስለመሆኑ ሲያስረዳ፤ ብዙ ሰዎች ሶፋ ይፈልጋሉ ነገር ግን ዋጋው ከአቅማቸው በላይ ሲሆን ይስተዋላል ይላል። ስለዚህ ሁሉም ሰው በአቅሙ መግዛት እንዲችል ተመጣጣኝ በሆነ ትርፍ ብዙ እያመረተ ገበያ ውስጥ በመግባት አብዛኛው ማኅበረሰብ ጋር መድረስ እንደቻለ ተናግሯል።

ሶፋ ለመሥራት አብዛኛው ጥሬ ዕቃ በሀገር ውስጥ የሚገኝ እንደመሆኑ ጨርቁን ጨምሮ ጥቃቅን የሆኑ ማስጌጫዎች ብቻ ከውጭ የሚመጡ መሆናቸውን የገለጸው ዐቢይ፤ ሶፋን ጨምሮ ቁምሳጥን፣ አልጋና ሌሎችም የቤት ውስጥ ቁሳቁሶችን ከውጭ አጓጉዞ ማምጣት በጣም አሳፋሪ እንደሆነ ነው የጠቀሰው። ሀገር ውስጥ በተሻለ ጥራትና ውበት በተመጣጣኝ ዋጋ መሥራት እየተቻለ ከውጭ ማስመጣቱ ተገቢ አይደለም የሚል ጽኑ ዕምነትም አለው። ሥራው ማንም ሰው ፍላጎት ካለው ሥልጠና ወስዶ መሥራት የሚችለው ቀላል ሥራ እንደሆነም አስረድቷል።

አሁን ላይ መንግሥት እየወሰደ ያለው እርምጃ አበረታች ነው። የሚለው ዐቢይ፤ በተለይም የሀገር ውስጥ አምራች ኢንዱስትሪዎችን በማበረታታት ተኪ ምርቶች በሀገር ውስጥ እንዲመረቱ እየተደረገ ያለው ጥረት አበረታች ነው ብሏል። ሀገር ውስጥ የማይገኙ በጣም ጥቃቅን የሆኑ ግብዓቶችን ብቻ ከውጭ በማምጣት ሁሉንም በሀገር ውስጥ ማምረት እንደሚቻል ያስረዳው ዐቢይ፤ ለዚህም መንግሥት የያዘው አቋም ተጠናክሮ ሊቀጥልና የሀገር ውስጥ አምራቾች ሊበረታቱ ይገባል ባይ ነው።

አንድ ሰው ሶፋ፣ አልጋና ቁምሳጥን ሲገዛ ለረጅም ጊዜ ሊጠቀምበት ነው የሚለው ዐቢይ፤ በሀገር ውስጥ የሚመረቱት ምርቶችም ጠንካራና ብዙ ጊዜ የሚያገለግሉ እንደሆኑ ጠቅሶ፤ በሶሊና ሆም ሾፒንግ የሚመረቱ ምርቶችም እጅግ ጠንካራ፣ ጥራትን ከውበት ያጣመሩ ከመሆናቸው ባሻገር ተመጣጣኝ ዋጋ ያላቸው እንደሆኑም ተናግሯል። እሱ እንደሚለው በሶሊና ሆም ሾፒንግ የሚመረት የሶፋ ዋጋ ትንሹ 40 ሺ ብር ሲሆን፤ ትልቁ 170 ሺ ብር ነው።

ቃሊቲ ላይ በሦስት ሺ ካሬ ሜትር ቦታ ምርቶቹን እያመረተ ያለው ሶሊና ሆም ሾፒንግ ለድርጅቱ ማስፋፊያ መናገሻ አካባቢ ከመንግሥት ባገኘው ተጨማሪ 10 ሺ ካሬ ሜትር ቦታ ላይ ግንባታ ጀምሯል። ይህም በቀጣይ ሥራውን እያስፋፋ በመሄድ በተለይም ጥራት ያላቸውንና ደረጃቸውን የጠበቁ ምርቶቹን ከሀገር ውስጥ ባለፈ ለአፍሪካ ሀገራት ኤክስፖርት ለማድረግ ያለመውን ዕቅድ ተግባራዊ ማድረግ የሚያስችለው መሆኑን ተናግሯል። ፋብሪካው ከአንድ ዓመት በኋላ ግንባታው ተጠናቅቆ ወደ ምርት ሲገባ ከፈርኒቸር ምርቶቹ በተጨማሪ ስፖንጅን ጨምሮ የተለያዩ ግብዓቶችን በማምረት ለገበያ ያቀርባል። ይህም ሰፊ የሥራ ዕድል የሚፈጥር እንደሆነ አመላክቷል።

ሙያውን በተመለከተ ማንም ፍላጎት ያለው ሰው መሥራት የሚችለው ሥራ እንደሆነ ዕምነት ያለው ወጣት ዐቢይ፤ ‹‹ማንም የማይችል ሰው የለም። እኔ አትችልም ተብዬ 19 ጊዜ እንደተባረርኩት ሰዎች ከሥራው እንዲርቁ አልፈልግም። ሙያው የሌለው ማንኛውም ሰው ጥሩ ሥነ-ምግባር፣ የሥራ ፍቅርና ፍላጎት ካለው መማር ማወቅና መሥራት ይችላል›› በማለት ሥራውን ፈልጎ ወደ ሶሊና ሶፋ ለሚመጣ ማንኛውም ሰው ሙያዊ ሥልጠና ከመስጠት ጀምሮ ቀጥሮ ለማሠራት በራቸው ክፍት እንደሆነ ገልጿል።

በእንጨት ሥራ ከልጅነት እስከ ዕውቀት ብዙ የደከመው ወጣት ዐቢይ፤ በትዕግስትና በበዛ ጥንካሬው አለመቻልን በመቻል ድል ነስቶ ዛሬ ስመ ጥር የቤት መገልገያ እቃዎች/ ፈርኒቸሮች/ ማምረቻ ባለቤት መሆን ችሏል። ያም ቢሆን ዐቢይ ዛሬም እረፍት የለውም። ለሥራው ካለው ጥልቅ ፍቅር የተነሳ በየጊዜው አዳዲስ ዲዛይኖችን በመፍጠር በተለይም የሶፋ ሥራን በተለየ መንገድ ለመሥራት ሲጠበብ ይታያል።

አዳዲስ ፈጠራዎች ያስደስቱኛል የሚለው ዐቢይ፤ ዓመታት ሲያስብ የነበረውን በዓይነቱ ልዩ የሆነ ትልቅ የሶፋ ቤት ከሙያ አጋሮቹ ጋር ሠርቷል። ይህ ትልቁ የሶፋ ቤትም በአፍሪካ ድንቃድንቅ ተመዝግቦ የዕውቅና ሰርተፊኬት አግኝቷል።

በትልቅ ሶፋ ቅርጽ የተሠራው ትልቁ የሶፋ ቤት ሶፋን ጨምሮ በውስጡ አንድ ቤት ማሟላት የሚገባቸውን ቁሳቁስ በሙሉ ጥንቅቅ አድርጎ ይዟል። የውሃና የኤሌክትሪክ መስመሮችም እንዲሁ ተዘርግተውለታል። ሶፋ ቤቱ ለአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር በስጦታ የተበረከተ ሲሆን፤ ከተማ አስተዳደሩም ትልቁ የሶፋ ቤት የሚቀመጥበትን ቦታ ፈቅዷል። ቦታው ፒያሳ ቸርቸር አካባቢ ሲሆን ድርጅቱ ቦታውን አፅድቶ ሙሉ መስታወት በመስታወት የሆነ ቤት ሠርቶ ትልቁን የሶፋ ቤት ለሕዝብ ዕይታ ክፍት ለማድረግ እየተዘጋጀ ይገኛል። በቅርቡ ለሕዝብ ዕይታ ክፍት የሚሆነው ትልቁ የሶፋ ቤት መስታወት ቤቱን ጨምሮ አምስት ሚሊዮን ብር ወጪ የተደረገበትና 150 ሠራተኞች የተሳተፉበት ድንቅ ሥራ ነው።

ማኅበራዊ ኃላፊነትን በመወጣት ረገድም ለአካባቢው ማኅበረሰብ የተለያዩ ድጋፎችን ያደርጋል። ድርጅቱ በሚገኝበት ጎተራ መስቀል ፍላወር አካባቢ ለመኖሪያ ምቹ ያልሆኑና የፈራረሱ የአራት አባወራዎችን ቤቶች አድሶና የቤት ዕቃ አሟልቶ አስረክቧል።

ከዚህ ባለፈም በበዓላት ወቅት ለአቅመ ደካሞች ማዕድ በማጋራት ድጋፍ ያደርጋል። መንግሥት ለሚያደርገው ማንኛውም ጥሪም እንዲሁ ምላሽ በመስጠት የአጋርነቱን እያረጋገጠ መሆኑን ገልጿል። በዚህ ተሳትፎውም ከከተማ አስተዳደሩ ዕውቅናን በማግኘት የዋንጫ ተሸላሚ መሆኑንም ነው ያመለከተው።

# እንደ ንስር አሞራ ሕይወትን መቀየር !

**አስናቀ ፀጋዬ**



ንስር አሞራ እስከ 70 ዓመት የሚኖር የእድሜ ባለፀጋ ነው። ነገር ግን 70 ዓመት ሙሉ በደስታ ከመኖሩ በፊት በእድሜው አጋማሽ ማለትም ከ35 - 40 ባለው እድሜው ላይ ከባድ ነገር ይገጥመዋል። የመጀመሪያው ምግቡን ለማደን የሚገለገልበት ጥፍሮቹ ከመጠን በላይ ስለሚያድጉ ምግቡን ከመሬት ላይ ማንሳት ያቅተዋል። ሁለተኛው አጥንትን ሳይቀር የመስበር አቅም ያለው አፉ (መንቁሩ) ስለሚታጠፍና ስለሚጣመም ምግቡን እንደወትሮው መመገብ ይሳነዋል። ሶስተኛው ክንፉና በአካሉ ላይ ያሉ ላባዎቹ ስለሚከብዱት ያ ሰማየ ሰማያትን እየሰነጠቀ ይበር የነበረው ኃይሉ ይከዳዋል።

እነዚህ ሶስት ከባድ ነገሮች ንስር አሞራ በእድሜው አጋማሽ የሚያጋጥሙት ከባድ ችግሮች ናቸው። አሁን ንስር አሞራ ያለው ምርጫ ሁለት ነው። ወይ ካረጀ አካሉ ጋር ዝም ብሎ ተቀምጦ ሞቱን መጠበቅ አልያም ደግሞ አምስት ወር የሚፈጅ ስቃይና መከራ ያለበት መስዋዕትነትን ከፍሎ ቀሪውን 35 ዓመት በደስታ ማሳለፍ። የመጀመሪያውን ከመረጠ በእድሜው አጋማሽ ይሞታልና ታሪኩ እዛ ጋር ያበቃል። ሁለተኛውን ምርጫ ከመረጠ ግን የሚቀጥሉት አምስት መስዋዕቶች ማለፍ ይጠበቅበታል።

በመጀመሪያ ከፍተኛ ተራራ ላይ በመውጣት የብቻውን ጎጆ ይቀልሳል። ቀጥሎ ጎጆ ከቀለሰ በኋላ የመጀመሪያ ስራው የአፉን መንቁር ከአለት ጋር በማጋጨት ነቅሎ ይጥላል። ይህን ካደረገ በኋላ አዲስ መንቁር ይወጣለታል። መንቁሩ እስኪያድግ ድረስ ታግሶ በጎጆው ምንም አይነት ምግብ ሳይመገብ መቆየት ግዴታው ይሆናል። አዲስ መንቁር ከበቀለለት በኋላ በአዲሱ መንቁሩ የገዛ እግሩን አሮጌ ጥፍር ነቃቅሎ ይጥለዋል።

አዲሱ የእግር ጥፍር ከበቀለለት በኋላ ደግሞ ይህንን አዲስ ጥፍር እንደ መሳሪያ በመጠቀም በሰውነቱ የተጣበቁትን፣ እንዳይበር እንቅፋት የሆኑትን፣ የገዘፉና ያረጁ ላባዎችን ነቃቅሎ ይጥላል። በምትኩ አዲስ ላባ ያበቅላል።

ይህን አምስት ወር በዚህ መልኩ በጀግንነት ከተወጣ በኋላ እንደገና ራሱን በራሱ ወልዶና ወጣት ሆኖ ወደ ንስሮች መንደር ብቅ ይላል። አንተም በተመሳሳይ መንገድ አልፈህ በአዲስ ሕይወት ከፍ ብለህ መብረር ትችል ዘንድ ከንስር አሞራው ሕይወት ትምህርት መውሰድ ይኖርብሃል።

አየህ በብዙ ችግሮች ተተብትበህ ሊሆን ይችላል። ግን ደግሞ ከችግሮችህ ተላቀህ አዲስ ሕይወት መምራት ትፈልጋለህ። አዲስ ሕይወት ለመምራት ደግሞ የውሳኔ ሰው መሆን ይጠበቅብሃል። ግን ደግሞ ለመወሰን ብዙ ታመነታ ይሆናል። ብዙ ሰበብ ትደረድር ይሆናል። ለውሳኔ ግዜው አሁን አይደለም፤ ትክክለኛ ግዜ ሲመጣ እወስናለሁ ልትልም ትችላለህ። በውሳኔ ደግሞ ግዜው አልደረሰም የሚል ነገር የለም። ሁሌም ቢሆን የውሳኔ ግዜው አሁን ነው፤ ዛሬ ነው።

ለመሆኑ ችግርህ ምን ኖራል? ከተቀጣሪነት ተላቆ የራስን ቢዝነስ መጀመር ነው?፣ ካለብህ ሱስ መላቀቅ ነው?፣ ትዳር መመስረት ነው?፣ ትምህርት መማር ነው? መንፈሳዊ ሕይወትህ ላይ መጠንከር ነው? ጤናህን መጠበቅ ነው? ወይስ ሌላ ችግር? ብቻ በሕይወትህ እስከመጨረሻው ድረስ መለወጥ የምትፈልገው አንድ ነገር ይኖራል፡ ፡ ጥያቄው ይህን ነገር እንዴት ታሳካዋለህ የሚለው ነው። ለዚህ ደግሞ ከላይ የተነሳው የንስር አሞራ ሕይወት ጥሩ ምሳሌ ይሆንሃል።

ልብ ብለህ ከሆነ ንስር አሞራው ሰባ ዓመት መኖር የሚችለው ሰላሳ አምስት ዓመቱ ላይ ሲደርስ ቆራጥ ውሳኔ ማሳለፍ የሚችል ከሆነ ብቻ ነው። አለበለዚያ ግን ሰባ ዓመት የመኖር እድል አያገኝም። ተፈጥሮ የሰጠችውን እድል ከዳር ማድረስ አይችልም። አንተም ቢሆን እስካሁን ድረስ በሕይወትህ ትርጉም

> **‹‹የንስር አሞራው ታሪክ ላይ ሁለት አይነት የተፈጥሮ ምርጫ ማለትም መኖር ወይም መሞት ያለ ቢሆንም በተፈጥሮ ሕግ መሰረት ማንም ፍጥረት እስከመጨረሻው ድረስ ይፍጨረጨራል እንጂ ራሱን ለሞት አጋልጦ የሚሰጥ የለም። እርግጥ ንስር አሞራዎች ሁለት አይነት ምርጫ ቢኖራቸውም ተስፋ ያልቆረጡት ካልሆኑ በስተቀር አብዛኛቹ የሚጠበቅባቸውን መስዋዕትነት ከፍለው ሕይወታቸውን እስከመጨረሻው ያስቀጥላሉ፡፡ ይህ ደግሞ የተፈጥሮ ግዴታም ጭምር ነው፡፡››**

ያለው ለውጥ አላመጣህ ይሆናል። በስራህና በገቢህ ደስተኛም ላትሆን ትችላለህ፣ የጤንነትህ ሁኔታም አደጋ ላይ ሊሆን ይችላል። ትምህርትህ፣ የፍቅር ግንኙነትህም ጥቁር ጥላ አጥልቶበት ሊሆን ይችላል።

እናም አሁንም አልረፈደምና ሕይወትህን እስከወዲያኛው ድረስ ለመቀየር ከፈለክ እንደ ንስር አሞራው አሁኑኑ መወሰን ይኖርብሃል። ይህ ሲባል መጥፎ ልማዶች ካሉብህ ማቆም፣ ጤናህ አደጋ ላይ ከሆነ ስፖርት መስራት፣ ተቀጣሪነት ከሰለቸህ በራስህ ቢዝነስ ለመፍጠር ዝግጁ መሆንና ወዘተ የመሳሰሉትን ለማድረግ ፍቃደኛ መሆን ይጠበቅብሃል። ይህን ለማድረግ ዝግጁ ከሆንክና ካደረከው ደግሞ ልክ እንደ ንስር አሞራው አሁን የገጠመህን ችግር ቀርፈህ በቀጣይ የተሻለ ሕይወት የመኖር እድል ይኖርሃል።

አይተህ ከሆነ ንስር አሞራው በእድሜው አጋማሽ ላይ የገጠመውን ችግር ለማለፍ ብርቱ መሰዋዕትነትን መክፈል አለበት። ስለዚህ አንተም የምትልግው የሕይወት ደረጃ ላይ እስከምትደርስ ድረስ ዋጋ መክፈል አለብህ። ውጣ ውረዶችን ማለፍ ይጠበቅበሃል። ለችግሮች እጅ መስጠት የለብህም። ያለበለዚያ ግን በተለመደው የሕይወት መንገድ ለመቀጠል ወስነሃልና በሕይወትህ አዲስ ነገር አይኖርም። ተመሳሳይ ሕይወት ነው የምትኖረው። የሚቀየር ነገር አይኖርም። ስለዚህ ምርጫው ያንተ ነው። ወይ ትንሽ ተሰቃይቶ በዘለቄታው ሕይወትህን መቀየር፤ አልያም ደግሞ አሁን ያለውን ሕይወትህን ተቀብለህ መኖርና ይችን ምድር ተሰናብቶ መሄድ!

የንስር አሞራውን የመጀመሪያ ውሳኔ ከመረጥክ የተሻለና ዘላቂ ሕይወት ለመኖር ወስነሃልና ልክ ንስር አሞራው ደረጃ በደረጃ ከባድ መስዋዕትነትን በሕይወትህ መክፈል ይጠበቅበሃል። ከራስህ ጋር ምከር። የሚጠቅምህንና የሚጎዳህን ላይ። በዙሪያህ ያሉና ተተብትበው የያዙህ ችግሮች ምን እንደሆኑ እወቅ። አለስራህ ያሉህ እንቅፋቶች የትኞቹ እንደሆኑም አንድ በአንድ ለያቸው። ከዛም ለውሳኔ ዝግጁ ሁንና ወደተግባር ግባ። አይተህ ከሆነ ንስር አሞራው 35 ዓመቱ ላይ ሲደርስ እንደልብ እደዳያድን ካደረጉት የሰውነት ክፍሎች ውስጥ አንዱ መንቁሩ ነው። ስለዚህ በልቶ ለመኖር መንቁሩ ወሳኝ ነውና አዲስ መንቁር እንዲበቅልለት መንቁሩን ከአለት ጋር እያጋጨ ነቅሎ ጥሎታል። በምትኩም አዲስ መንቁር በቅሎለታል።

አንተም ብትሆን ከዚህ በፊት አላሰራ ያለህን መጥፎ ልማድ ተውና በአዲስ ተካው። ትሰራለህ፣ ትደክማለህ ግን በስራህ ውጤት አይኖርህ ይሆናል። ስለዚህ መነቀል ያለባቸውና ያረጁና ያፈጁ አሰራሮችን የምትከተል ከሆነ እነርሱን ተዋቸውና አዲስ፣ ቀላልና ብልህነት የታከለባቸው አሰራሮችን ተከተል። ይህ በስራህ ብቻ ሳይሆን በግል ሕይወትህ ላይም ጭምር ሊሰራ ስለሚችል ተግባራዊ አድርገው። ያኔ ሕይወትህ እየተለወጠ እንደመጣ በግልፅ ይታይሃል።

ንስር አሞራው መንቁሩ ካደገለት በኋላ ለማደን ይገለገልባቸው የነበሩትንና አሁን ግን ያረጁትን ጥፍሮቹን ለመንቀያነት ይጠቀምባቸዋል። ጥፍሮቹ ሲያድጉ ደግሞ ለመብረር የከለከሉትን ክንፎቹን ነጭቶ ይጥልበታል። አየህ! አንተጋም ያሉት ችግሮች ተደራራቢ ሊሆኑ ይችላሉ። ለአፍታም አስቸጋሪ ሆነው ሊታዩህ ይችላሉ። ነገር ግን በሕይወትህ አዲስ ነገር ለማምጣት እስከፈለክና እስከወሰንክ ድረስ አንዱን ችግር ስትፈታ ሌላኛው ይቀረፋል። ብቻ አንዱን ችግር ለመፍታት አንተ ቁርጠኛ ሁን እንጂ የአንዱ ችግር መፍትሄ ለሌላውም መፍትሄ የማይሆንበት ምንም ምክንያት አይኖርም።

በሕይወትህ ሁለንተናዊ ለውጥ ለማምጣት የምታደርገው ሂደት በአንድ ጀምበር ውጤት አያመጣም። ልክ እንደ ንስር አሞራው የራሱ የሆነ ግዜ ይወስዳል። ንስር አሞራው ዳግም ወደ ወጣትነት ለመመለስ አምስት ወራት ፈጅቶበታል። ግን ደግሞ ለአምስት ወር የከፈለው መስዋዕትነት ተጨማሪ 35 ዓመታትን እንዲኖር እድል ሰጥቶታል። ሁሉም ነገር በአንድ ጀምበር አልሆነምና በሕህይወትህ ትርጉም ያለው ለውጥ ማምጣት ከፈለክ አንተም ወስደህ ሕይወትህን ለመለወጥ ስራ። ትእግስት ይኑርህ። ምክንያቱም ትግስትና የምትከፍለው መስዋዕትነት ኋላ ላይ መልሶ ይከፍልሃልና።

የንስር አሞራው ታሪክ ላይ ሁለት አይነት የተፈጥሮ ምርጫ ማለትም መኖር ወይም መሞት ያለ ቢሆንም በተፈጥሮ ሕግ መሰረት ማንም ፍጥረት እስከመጨረሻው ድረስ ይፍጨረጨራል እንጂ ራሱን ለሞት አጋልጦ የሚሰጥ የለም። እርግጥ ንስር አሞራዎች ሁለት አይነት ምርጫ ቢኖራቸውም ተስፋ ያልቆረጡት ካልሆኑ በስተቀር አብዛኞቹ የሚጠበቅባቸውን መስዋዕትነት ከፍለው ሕይወታቸውን እስከመጨረሻው ያስቀጥላሉ። ይህ ደግሞ የተፈጥሮ ግዴታም ጭምር ነው።

የሰው ልጅም ቢሆን እንዲህ ሳይፍጨረጨር በተስፋ መቁረጥ ብቻ ውድ ሕይወቱን አሳልፎ አይሰጥም። በዚህች ምድር እስካለ ድረስ ይፍጨረጨራል፣ ላይ ታች ይላል፣ በብዙ ይፈተናል። በመጨረሻም ይህችን ምድር ለቆ ወደማይቀረው ይሄዳል። ስለዚህ አንተም ብትሆን እርግጠኛ ነኝ በሕይወትህ ተስፋ አትቆርጥም። ጥቂት ነገሮች ይዘው ሊሆን ይችላል እንጂ ሕይወትህን እስከመጨረሻው መለወጥ ትፈልጋለህ።

ብዙ ሰዎች ከተስፋ መቁረጥ ወጥተው ሕይወታቸውን በብዙ መልኩ ቀይረዋል። በርካቶች አለቀላችሁ ሲባሉ ዳግም ተፈጥረው ዓለምን ጉድ አሰኝተዋል። አከተመላቸው የተባሉ ብዙ ሰዎች ወደሕይወት ዳግም ተመልሰዋል። ለዚህ ደግሞ የንስር አሞራው ታሪክ ለብዙዎች ትምህርት የሚሰጥ ነው። በተለይ በሕይወት መንገድ ሁለት አማራጭ ቀርበው የተሻለውን ነገር ግን ለጥቂት ግዜ ስቃይ ያለውን ውሳኔ መርጦ እንዴት ሕይወትን መቀየርና ተስፋ ሳይቆርጡ እስከመጨረሻው የሕይወት ፍፃሜ ድረስ መጓዝ እንደሚቻል ትልቅ ማሳያ ነው።

አንተም ቢሆን ቀሪ ሕይወትህ ያማረና የሰመረ ይሆን ዘንድ ከአሁኑ ወስነህ ሕይወትህን መቀየር ይኖርብሃል። በስራህ፣ በኑሮህ፣ በትዳርህ፣ በትምህርትህና በመሳሰሉት ለውጥ ማምጣት ከፈለክ ዛሬውኑ ወስነህ ማስተካከል የሚገቡህን ነገሮች ማስተካከል ይጠበቅብሃል። ከንስር አሞራው ትምህርት ወስደህ ሕይወትህን በዘለቄታው መቀየር ይጠበቅብሃል። አንተ ደግሞ ሰው ስለሆንክ ምን ከማድረግ ምንም እንደማያግድህ ማወቅ አለብህ። ይህን ስታደርግ የመኖር ትርጉሙ ይገባሃል። እንደንስር አሞራውም ከፍ ብለህ ትበራለህ።

# ማህደረ ጤና

# የበለፀገ ምግብ ለማኅበረሰብ ጤና

**አስናቀ ፀጋዬ**

ምግብ ከመሰረታዊ የሰው ልጅ ፍላጎቶች ውስጥ አንዱ ነው። ያለምግብ የሰው ልጅ ጥቂት ቀናት ሊሰነብት ይችላል እንጂ ሟች ነው። ምግብ ሲባል ግን እንደው በደፈናው የሚረባውንም የማይረባውንም ጨምሮ አይደለም። ከምግብም በላይ ምግብ አለ። የስነ ምግብ ባለሞያዎች እንደሚሉት ከሆነ ትክክለኛ ምግብ የሚባለው ለጤና ተስማሚ፣ ሰውነትን ሊገነባና በሽታ ሊከላከል የሚችል ብሎም በልዩ ልዩ ንጥረ ነገሮች የዳበረ ነው።

ምግብ ከምግብነት ባሻገር የሰው ልጅ ጤና ተጠብቆ እንዲዘልቅ የሚያስችል በመሆኑ ልዩ ትኩረት ተደርጎ ይሰራበታል። ይህ ማለት ሰዎች ለጤና ተስማሚ የሆኑ ምግቦችን እንዲመገቡ ቁጥጥር ከሚያደርገው የመንግስት አካል ጀምሮ ምግብን አምርተው ለተጠቃሚው እስከሚያደርሱት ድረስ ጠንካራ ስራ ይሰራበታል። እንዲህ በተናበበ መልኩ በምግብ ላይ ልዩ ትኩረት አድርገው የሚሰሩ ሀገራት ደግሞ የዜጎቻቸው ጤና ማስጠበቅ ችለዋል።

ኢትዮጵያን ጨምሮ ሌሎች ገና በማደግ ላይ ባሉ ሀገራት ለምግብ የሚሰጠው ትኩረት አናሳ ስለመሆኑ መረጃዎች ያሳያሉ። በነዚህ ሀገራት ዜጎች በአብዛኛው የሚመገቧቸው ምግቦች በንጥረ ነገር የዳበሩ አይደሉም። ይልቁንም በአብዛኛው በፋብሪካ የተቀነባበሩና የምግብ ይዘታቸው ያለቀለት ምግቦችን ነው የሚመገቡት። ተፈጥሯዊ ምግቦችን የመመገብ ዝንባሌ ቢኖራቸውም ለምግብ ግብአትነት የሚውሉ ምርቶች በውስጣቸው የያዙትን ጠቃሚ ንጥረ ነገር አስቀድመው ስለሚያወጧቸው የተሟላ ምግብ ተመገቡ ለማለት አይቻልም።

በኢትዮጵያም ስንዴ፣ ገብስና ሌሎችንም አዝርት ፈትጎ የመመገብ ዝንባሌ ይታያል። ይህም ጠቃሚ የምግብ ንጥረ ነገሮችን ባለመመገብ ምክንያት በተለያዩ በሽታዎች የመጠቃትና የመቀንጨር ችግሮች ይታያሉ። በቫይታሚንና ሚኒራሎች የበለፀጉ ምግቦችን ባለመመገብ ምክንያት ተማሪዎች በትምህርት ቤት ዝቅተኛ ውጤት ማምጣት፣ ካደጉ በኋላም ምርታማ ያለመሆንና ሌሎችም ተያያዥነት ያላቸው ችግሮች ይገጥሟቸዋል። ይህ ደግሞ በሀገር ኢኮኖሚያዊ እድገት ላይ በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ የራሱ ተፅእኖ ይኖረዋል።

ለዚህም ነው መንግስት በምግብና በስርዓት ምግብ ዙሪያ ትኩረት አድርጎ በመስራት ላይ ያለው። የምግብና የስርዓተ ምግብ ፖሊሲም ፀድቆ ወደ ስራ ከገባ ሰንበቷል። በርግጥ በምግብና በስርዓተ ምግብ ላይ ያለው ችግር አሁንም በግልፅ የሚታይ ቢሆንም አበረታች ጅምር ስራዎች በመንግስትና በምግብ ዙሪያ በሚሰሩ መንግስታዊ ያልሆኑ ተቋማት እየተከናወኑ ይገኛሉ።

ወይዘሮ ወገኔ ግርማ ‹‹ቴክኖ ሰርቭ›› በተሰኘና የገበሬዎችን አቅም በልዩ ልዩ መልኩ በመገንባት ጥራት ያለው የግብርና ምርቶችን እንዲያመርቱ በሚያደርግ ድርጅት ውስጥ ምክትል ካንትሪ ዳይሬክተር ሆነው ያገለግላሉ። እርሳቸው እንደሚሉት፣ ድርጅቱ ስራውን በኢትዮጵያ ከጀመረ አስራ አምስት ዓመታትን አስቆጥሯል። ስራውን የጀመረው በቡና አቅርቦት ሰንሰለት ላይ የነበረ ሲሆን የገበሬውን አቅም በማሳደግ ጥራት ያለው ቡና አምርተው ለተጠቃሚው እንዲያደርሱ አድርጓል። በመቀጠል ደግሞ ካለፉት አምስት ዓመታት ወዲህ በአትክልትና ፍራፍሬ ምርቶች ላይ ትኩረቱን አድርጎ ገበሬዎች ጥራት ያለው ምርት አምርተው ለተጠቃሚው እንዲያደርሱ የአቅም ማጎልበቻ ስራዎችን ሰርቷል።

በተጨማሪም በአዲስ አበባ የተለያዩ አካባቢዎች ደረቅ ቆሻሻዎችን ሰብስቦ ዳግም ጥቅም የሚሰጡበትን ፕሮግራም በማመቻቸት በተለይ ወጣቶችና ሴቶች ተጠቃሚ እንዲሆኑ አስችሏል። በፕሮግራሙ እስካሁን ከ5 ነጥብ 8 ሚሊዮን በላይ ሴቶችና ወጣቶች ተጠቃሚ መሆን ችለዋል። ድርጅቱ የአቅም ማጎልበት ስራውን የሚያከናውነውም ቡና፣ አትክልትና ፍራፍሬ አብቃይ በሆኑ በሁሉም ክልልች በሚገኙ አካባቢዎች ላይ ነው። አብዛኛዎቹ ድርጅቱ የሚያከናውነው ስራዎችም በዩ ኤስ ኤድ፣ ዩ ኤስ ዲ ኤና ሌሎችም ይደገፋታል።

በምግብ ማቀነባበር ሂደት ደግሞ ድርጅቱ ለአምራቾች የተለያዩ ቴክኒካዊ ድጋፍ ይሰጣል። አምራቾች ድጋፉ ተደርጎላቸው ምን ደረጃ ላይ እንደደረሱ ያለውን ሂደትም ይከታተላል። ይህም ጤናማ የምግብ አመራረት ሂደት እንዲኖርና ዜጎች በንጥረ ነገር የበለፀጉ ምግቦችን እንዲመገቡ ያስችላል። በተዘዋዋሪ ደግሞ እነዚህን ምግቦች በመመገብ ጤናቸውን ለመጠበቅ ያስችላቸዋል።

**በተመሳሳይ አርሶ አደሮችና የምግብ ፋብሪካ ባለቤቶች የፋይናንስ ተደራሽነት ኖሯቸው የምግብ ጥራትና ይዘት ላይ እንዲሰሩ ከመንግስት ጋር ሆኖ ይሰራል**

በቀጣይም ድርጅቱ ለምግብነት የሚውሉ ምርቶች ጥራታቸውን በጠበቀ መልኩ ተመርተው ወደተጠቃሚው እንዲደርሱ ከአርሶ አደሩ ጀምሮ ምግብ አቀነባባሪዎች ድረስ ዘላቂነት ያለው የአቅም ግንባታና የቴክኒክ ድጋፍ ያደርጋል፤ እያደረገም ይገኛል። በተመሳሳይ አርሶ አደሮችና የምግብ ፋብሪካ ባለቤቶች የፋይናንስ ተደራሽነት ኖሯቸው የምግብ ጥራትና ይዘት ላይ እንዲሰሩ ከመንግስት ጋር ሆኖ ይሰራል።

በዚሁ ድርጅት ውስጥ የኒውትሪሽን የኢትዮጵያ ፕሮግራም ማናጀር ሆነው እየሰሩ ያሉት አቶ እያቄም አምሳሉ እንደሚናገሩት፣ በዱቄትና በምግብ ዘይት ውስጥ ጠቃሚ ንጥረ ነገሮች እንዲገቡ ኢትዮጵያ ለፋብሪካዎች ያወጣቸው መስፈርት (ስታንዳርድ) አለ። በዚሁ ስታንዳርድ መሰረት ድርጅቱ ፕሮግራም ዘርግቶ ለፋብሪካዎቹ የቴክኒክ አቅም ግንባታ ድጋፍ ያደርጋል፤ ስልጠናዎችንም ይሰጣል። ምግቡ ከበለፀገ በኋላ ደግሞ ምን ያህል ጠቃሚና ደረጃውን ያሟላ እንደሆነ የላብራቶሪ ፍተሻ ድጋፍ ያደርጋል። በሀገር ውስጥ ያሉ ላብራቶሪዎች የበለፀገውን ምግብ እንዲፈትሹ የአቅም ግንባታ ድጋፍ ይደረግላቸዋል። ከዚህ ባሻገር ድርጅቱ ከመንግስት ባለድርሻ አካላትና ከዩኒቨርሲቲዎች ጋር በትብብር ይሰራል።

ለሰዎች ጠቃሚና በምግቦች ውስጥ የሚገኙ ቫይታሚንና ሚኒራሎች አሉ። እነዚህ ቫይታሚኖችና ሚኒራሎች ሰዎች ጤናማ ሕይወት እንዲኖሩ ያስችላሉ። ለልጆች ደግሞ ጤናማና የዳበረ ሰውነት እንዲኖራቸው ይረዳሉ። ይሁንና በአሁኑ ግዜ ምግቦች በደምብ ስላልበለፀጉና እነዚህን ቫይታሚኖችንና ሚኒራሎችን ያሟሉ ስላልሆኑ ሕብረተሰቡ ከነዚህ ምግቦች ላይ የሚያገኘው ጥቅም ዝቅተኛ ነው። ለአብነትም ስንዴ ሲፈጭ ከላይ ያለውና አብዛኛውን ምግብ የያዘው ክፍል ስለሚወገድ የሚፈለገው የምግብ ንጥረ ነገር ለሰዎች አይደርስም።

ይህን ለመተካት የቫይታሚንና ሚኒራል ድብልቆች በምግብ ውስጥ እንዲገቡ የሚያስገድድ ስታንዳንርድ በመንግስት በኩል ወጥቷል። እነዚህን የቫይታሚንና ሚኒራል ድብልቆች በምግብ ውስጥ ለማስገባት ደግሞ እውቀቱ ያስፈልጋል። ስለዚህ መንግስት ባስቀመጠው ስታንዳርድ መሰረት ድርጅቱ የቴክኒክ ድጋፍ ያደርጋል።

በመንግስት በኩል በርካታ ጥናቶችና ምዘናዎች ተካሂደው በምግብ ውስጥ የጎደሉ ንጥረ ነገሮች ምን እንደሆኑና ይህን ተከትሎ ለምን በሽታዎች እንደመጡ ለማየት ተሞክሯል። እነዚህ የምግብ ንጥረነገሮችን በምግብ ውስጥ ማስገባቱ ለሕብረተሰቡ ጤና ወሳኝ እንደሆኑም ተረጋግጧል። በስታንዳርዱ መሰረት በምግቦቹ ውስጥ እነዚህን ጠቃሚ ንጥረነገሮች ለማስገባት አስፈላጊ ግብአቶች አሉ። እነዚህ ግብአቶች በምን ደረጃ ጥራቱን የጠበቀ ምግብ ማምረት እንደሚችሉ በስታንዳርዱ መሰረት ይፈተሻሉ።



በንጥረ ነገር የበለፀገ ምግብ መመገብ ጤናማ ሕይወትን ይፈጥራል፤

ጠቃሚ የምግብ ንጥረ ነገሮች እጥረት እንደ ‹‹ስፓይና ቤፊዳ›› የተባሉና የአከርካሪ አጥንት የሚጎዱ በሽታዎችን እያስከተሉ ይገኛሉ። ይህ በሽታ ደግሞ በአብዛኛው እየጎዳ ያለው ሕፃናትን ነው። በተመሳሳይ መቀንጨርም የዚሁ የበለፀገ ምግብ እጥረት ውጤት ነው። እንደውም የበለፀጉ ምግቦችን አለመመገብ ወይም እጥረት መኖር ድብቁ ረሃብ ይሰኛል። ምክንያቱም ሰዎች ምግብ በልተው የጠገቡ ቢመስላቸውም የተመገቡት ምግብ በቂ ንጥረ ነገሮችን ባለመያዙ እንደተራቡ ስለሚቆጠር ነው። ስትንዳርዱ የወጣውና ይህ ምግብን የማበልፀግ ስራም የተጀመረው ይህን የድብቅ ረሃብ ችግር ለመቅረፍ ነው።

በመንግስት በተሰራ ጥናት ደግሞ በድብቅ ረሃብ ‹‹hidden hunger›› ምክንያት 4 ነጥብ 5 ቢሊዮን ዶላር በዓመት መንግስት ያጣል። ይህ ገንዘብ ለብዙ ነገር መጠቀም ይቻል ነበር። ስለዚህ መቀንጨርና ሌሎችም ከበለፀጉ ምግቦች እጥረት ጋር በተያያዘ የሚከሰቱ በሽታዎችን መከላከል የሚቻለው ምግቦችን በማበልፀግና ሰዎች ምግቦቹን በአግባቡ እንዲመገቡ በማድረግ ነው። ለዚህ ደግሞ የምግብ አመራረት ጥራቱና የማበልፀግ ሂደቱ በስታንዳርዱ መሰረት መሆኑን ማረጋገጥ ይገባል። ስታንዳርዱ ተግባራዊ መሆን የጀመረ ቢሆንም ሙሉ በሙሉ ግን ተግባራዊ መሆን ይጠበቅበታል። ድርጅቱ በዚህ ረገድ ያለውን ስራ እየሰራ የሚገኘውም ክፍተቱን ለመሙላት ነው።

የኢትዮጵያ ምግብና መጠጥ ኢንዱስትሪ ምርምርና ልማት ማእከል ዋና ስራ አስኪያጅ አቶ በቀለ መኩሪያ በበኩላቸው እንደሚሉት በኢትዮጵያ የተመጣጠነ ምግብ እጥረት ችግር በስፋት ይታያል። ከአምስት ዓመት በታች ያሉ ሕፃናት መቀንጨር በስፋት መታየት ደግሞ ለዚህ ችግር መኖር አንዱ ማሳያ ነው። የሕፃናት መቀንጨር በኢትዮጵያ 39 ከመቶ ደርሷል። ይህም በዋናነት የሚከሰተው በተመጣጠነ ምግብ እጥረት ችግር ነው።

ከመቀንጨር ባለፈ በተመጣጠነ ምግብ እጥረት ምክንያት የሚከሰቱ ሌሎች የጤና ችግሮችም አሉ። ለምሳሌ ኒውራል ቲዩብ ዲፌክት /የአከርካሪ አጥንት ጤና መታወክና የራስ ቅል መጠን መጨመር ችግር/ ገና በተወለዱ ሕፃናት ላይ በብዛት እየተከሰቱ መጥተዋል። ይህን ችግር ግን እናቶች በእርግዝና ወቅት ፎሊክ አሲድ በመውሰድ ማስወገድ ይችላሉ።

የተመጣጠነ ምግብ እጥረት ችግር በጤና ላይ ብቻ ሳይሆን በሀገሪቱ ኢኮኖሚ ላይም ከፍተኛ ተፅእኖ እያደረሰ ይገኛል። ከዚህ በፊት የተሰሩ ጥናቶች በተለይ ደግሞ cost of hunger በሚል የተሰራው ጥናት እንደሚጠቁመው ወደ 4 ነጥብ 5 ቢሊዮን ዶላር ሀገሪቱን በተመጣጠነ የምግብ እጥረት ምክንያት ያሳጣታል። የሀገሪቱን 16 ነጥብ 5 ከመቶ ዓመታዊ የተጣራ ገቢ/ጂ ዲ ፒ/ እንደሚያሳጣትም ነው ጥናቱ የሚያመለክተው። በዚህ የተመጣጠነ ምግብ እጥረት ምክንያት በኢንዱስትሪ አካባቢዎች ምርታማነት ዝቅተኛ እንደሆነም ጥናቱ ያሳያል።

የተመጣጠነ ምግብ እጥረት በጤናና በኢኮኖሚ መስክ የሚያደርሰው አሉታዊ ተፅእኖ እጅግ ከፍተኛ በመሆኑ በዚህ ላይ ሰፊ ስራ መስራት ያስፈልጋል። የተመጣጠነ ምግብ እጥረት በጤናና በኢኮኖሚ ላይ እያስከተለ ያለው ችግር ለመቅረፍ በመንግስት በኩል የተለያዩ ስራዎች እየተከናወኑ ይገኛሉ። አንደኛው የምግብ ማበልፅግ ፕሮግራም ሲሆን ይኸው ፕሮግራም ተቀርፆ ኢንዱስትሪ ሚኒስቴር አስተባባሪነትና በማእከሉ የቴክኒክ አስተባባሪነት እየተሰራበት ይገኛል።

ዋና ስራ አስኪያጁ እንደሚያስረዱት ይህ የምግብ ማበልፀግ ፕሮግራም በሶስት የምግብ ምርቶች ላይ በዋናነት እየተሰራበት ይገኛል። የመጀመሪያው የምግብ ጨው ሲሆን በጨው ውስጥ አዮዲን እንዲጨመር ይደረጋል። ይህም ሕፃናት በእንቅርት፣ በአእምሮ እድገት ውስንነት፣ በሴቶች ላይ ደግሞ በፅንስ ላይ የሚፈጠር ችግርን ለመከላከል ይረዳል። በኢትዮጵያ ጨውን አዮዳይዝ አድርገውና ሌሎች ቴክኖሎጂዎችን ተጠቅመው ለገበያ የሚያቀርቡ በርካታ ጨው አምራች ፋብሪካዎች አሉ። በነዚህ ፋብሪካዎች አማካኝነት በአብዛኛው አዮዲን ያለበት ጨው ገበያ ላይ እየገባ ነው።

ሁለተኛው ምርት የስንዴ ዱቄት ሲሆን የስንዴ ዱቄትን የሚያመርቱ ከ400 በላይ የሚሆኑ በርካታ ፋብሪካዎች በሀገር ውስጥ አሉ። ስንዴ ሲመረት በአብዛኛው ገለባው ተለይቶ ውስጡ ያለው ተፈጭቶ ለምግብነት የሚውለው። አብዛኛው ንጥረ ነገር የሚገኘው ደግሞ በገለባው ላይ ነው። ከዚህ አንፃር ከስንዴው ገለባ የጠፋውን የምግብ ንጥረ ነገር መልሶ በመጨመርና የስንዴውን ዱቄት በማበልፀግ ለተጠቃሚዎች እንዲደርስ ስራዎች እየተሰሩ ይገኛሉ። እንደ ሀገር አስገዳጅ ስታንዳርድ ፀድቆም ወደስራ ተገብቷል። በርካታ ስንዴ ዱቄት አምራች ኢንዱስትሪዎችም በተዘጋጀው ስታንዳርድ መሰረት ወደ ማበልፀግ ስራ እየገቡ ነው።

ሶስተኛው የምግብ ምርት ደግሞ ዘይት ነው። በኢትዮጵያ የምግብ ዘይት የሚያመርቱና ሙሉ ማጣሪያ ያላቸው ትላልቅ ኢንዱስትሪዎች 34 ደርሰዋል። እነዚህ ኢንዱስትሪዎች ዘይትን ቫይታሚን ‹‹ኤ›› እና ‹‹ዲ›› እያበለፀጉ ማምረት ጀምረዋል። ከ34ቱ ከዘጠኙ በላይ የሚሆኑት በተከታታይ እያመረቱ ይገኛሉ። በቅርቡ ደግሞ ሁሉም ቫይታሚን ‹‹ኤ›› እና ‹‹ዲ›› ያለው ዘይት ማምረት ይጀምራሉ።

ስለዚህ በዚህ የምግብ ማበልፀግ ፕሮግራም የገበታ ጨው፣ የስንዴ ዱቄትና የምግብ ዘይት ናቸው ተመርጠው ስራ እየተሰራባቸው ያለው። እነዚህ የምግብ ምርቶች ተመርጠው እየተሰራባቸው ያለው ካላቸው ተደራሽነትና የተጠቃሚያቸው ብዛት ከፍተኛ ከመሆኑ አኳያ ነው። በቀጣይ ደግሞ እነዚህ ምርቶች በማየት በሌሎች የምግብ ምርቶች ማለትም ስኳር፣ ወተት፣ የበቆሎ ዱቄትና በመሳሰሉት ላይ የምግብ ማበልፀግ ስራ የሚሰራ ይሆናል።

ለዚህ የምግብ ማበልፀግ ፕሮግራም የተለያዩ ፖሊሲዎች ተቀርፀዋል። ከነዚህም ውስጥ የምግብና ስርአተ ምግብ ፖሊሲ በዋናነት የሚጠቀስ ሲሆን ፖሊሲው ፀድቆ ስራ ላይ ውሏል። በተመሳሳይ የምግብ ስትራቴጂም ፀድቆ ስራ ላይ ውሏል። የአምስት ዓመቱ የምግብ ማበልፀግ ስትራቴጂም ተዘጋጅቶ ስራ ላይ ውሏል። እነዚህን ሁሉ በመጠቀም የግሉም ሆነ የመንግስት ሴክተር መስሪያ ቤት በጋራ ሆኖ አሁን የሚታየውን የተመጣጠነ ምግብ እጥረት ችግር መፍታትና ሕብረተሰቡ የተመጣጠነ ምግብ እንዲያገኝ ማድረግ ይጠበቅበታል።

ኢኮኖሚ

# መሠረተ ልማት

## የወሰን ማስከበር ችግርና የትራፊክ መጨናነቅ የፈተነው የመንገድ ግንባታ ፕሮጀክት

በኃይሉ አበራ

በአዲስ አበባ ከተማ በርካታ ሰፋፊ የመንገድ ፕሮጀክቶች ተገንብተዋል፡፡ መንገዶቹ ማሳለጫዎች፣ ትላልቅ ድልድዮች፣ ሰፋፊ የእግረኛ መንገዶች የተገነባላቸው መሆናቸው ለተሽከርካሪ የትራፊክ እንቅስቃሴም ሆነ ለእግረኞች ምቹ ሁኔታዎች ተፈጥረዋል፡፡ እንደዚህ አይነቶቹ የመንገድ ግንባታዎች አሁንም በኮርደር ልማቱና በሌሎች ፕሮጀክቶች ተጠናክረው ቀጥለዋል፡፡

ከተማዋ በሁሉም መውጫ በሮቿ በኩልም ተመሳሳይ ግንባታዎችን ስታካሂድ ቆይታለች፤ እያካሄደችም ትገኛለች፡፡ በከተማዋ መውጫ በሮች ከተገነቡት የመንገድ ፕሮጀክቶች መካከል የቃሊቲ ቱሉዲምቱ መንገድ ለእዚህ በአብነት ይጠቀሳል፡፡ ይህ መንገድ ምን ያህል የትራፊክ እንቅስቃሴውን እንዳሳለጠው ይታወቃል፡፡

ከተማ አስተዳደሩ አሁንም በከተማዋ መውጫ ላይ አንድ የመንገድ ፕሮጀክት መገንባት ጀምሯል፡፡ ይህ መንገድ ከፍተኛ የትራፊክ ፍሰት መጨናነቅ የሚታይበት ነው፡፡ የአካባቢው ነዋሪዎች እንደጠቆሙት፤ ይህ መንገድ ከፍተኛ የትራፊክ መጨናነቅ ይታይበታል፤ የእግረኛና የተሽከርካሪ መንገዶቹ በአግባቡ ፍሰቶቹን በሚመጥን መልኩ ያልተገነቡ በመሆናቸው ሁሌም አደጋዎች ይደርሳሉ፡፡ ይህን ተከትሎም የሰው ሕይወት ያልፋል፤ የንብረት ውድመት ይደርሳል፤ በትራፊክ መዘጋጋት ሳቢያም በሕዝብ የእለት ተእለት እንቅስቃሴ ላይ ከፍተኛ መስተጓጎል ሲደርስ ይስተዋላል፡፡

በተለምዶ የጅማ በር በመባል የሚታወቀው የዚህ አየር ጤና ወለቴ መንገድ ግንባታም ተጀምሯል፡፡ መንገድ መረጃዎች እንዳመለከቱት፤ በመንገዱ ሳቢያ የሚታዩ የትራፊክ መጨናነቅና የመሳሰሉትን ችግሮች ለማስቀረት የመንገዱ ግንባታ ሊካሄድ ውል ከተገባ ከዓመት በላይ ሆኖታል፡፡ ይሁንናም ወደ ግንባታ የተገባው በቅርቡ ነው። የአካባቢው ማኅበረሰብ በጉጉት የሚጠብቀው ይህ የመንገድ ፕሮጀክት አሁንም በሚፈለገው ፍጥነት እየሄደ እንዳልሆነ እየተጠቆመ ነው።

ለእዚህ መንገድ ግንባታ ፕሮጀክት መፋጠን የወሰን ማስከበር እንዲሁም የውኃ፣ የመብራት እና የመብራት ተቋማት ቅንጅታዊ ሥራ ወሳኝ መሆኑ ይታመናል፡፡ ይሁንና የአዲስ አበባ መንገዶች ባለሥልጣን ከአንድ ነጥብ ሶስት ቢሊዮን ብር በላይ ወጪ ይዞ እያስገነባ የሚገኘው የአየር ጤና፣ ካራ፣ ወለቴ አደባባይ የመንገድ ፕሮጀክት የግንባታ ሥራ በተለይ በወሰን ማስከበር እና ተያያዥ ምክንያቶች ዘግይቶ ነው የተጀመረው፡፡ አሁን የሚገኝበት የግንባታ ደረጃም ዝቅተኛ መሆኑ እየተጠቆመ ነው። ግንባታው በትራፊክ እንቅስቃሴው የተጨናነቀ መሆን፣ አማራጭ የትራንስፖርት መንገድ በአካባቢው ባለመኖሩ ምክንያት በሚፈለገው ፍጥነት እየተሠራ ላለመሆኑ ይገለጻል።

አቶ ለሜቻ ቶላ ተወልደው ያደጉት ከአየር ጤና ወደ ወለቴ በሚወስደው ቀደም ሲል ረጲ ጉለሌ አሁን ደግሞ ግራር በተባለው በዚሁ አካባቢ ነው። በዚሁ አካባቢም ለረጅም ጊዜ ኖረዋል፡፡ በአካባቢው በጣም አስከፊ አደጋዎችን መመልከታቸውን ጠቅሰው፣ በዚህ መንገድ ጥበት የተነሳ አባታቸውንና የአባታቸውን ወንድም በትራፊክ አደጋ ማጣታቸውን ገልጸዋል፡፡

እሳቸው እንዳሉት፤ እግረኛውና ተሽከርካሪው በመንገዱ እየተጋፋ ነው የሚሄዱት፡፡ የዚህ መንገድ ግንባታ ሥራ መጀመር መልካም ቢሆንም፣ ወደፊትም እንዳይጠብ ከዚህ በበለጠ ስፋት መሠራት አለበት ሲሉ ያስገነዝባሉ። መንገዱ ለእግረኛው ሰፋ ብሎ እግረኛውን ከተሽከርካሪው ራቅ በማድረግ መሠራት እንዳለበት ጠቁመዋል።

መንገድ አንድን አካባቢ ለመለወጥ ወሳኝ መሆኑን የሚናገሩት አቶ ለሜቻ፣ በጀሞ አካባቢ ጨፌ ፉሪ ሜዳ በሚባል አካባቢ እየሄዱ እግር ኳስ ይጫወቱ የነበረበት አካባቢ በአካባቢው የተሻለ መንገድ መገንባቱን ተከትሎ አካባቢው እድገት ማሳየቱን ተናግረዋል፤ የአየር ጤና ወለቴ መንገድ ሥራም በፍጥነት ተጠናቅቆ ለማየት ጉጉት እንዳደረባቸው አመላክተዋል።

አቶ ብሥራት ጥላሁን በአካባቢው ለረጅም ዓመታት ኖረዋል፤ ይህ ብቻም አይደለም፤ ለረጅም ዓመታትም በተለያዩ አካባቢዎች አሽከርካሪ ሆነው ሠርተዋል፡፡ አቶ ብሥራት መንገድ ለአንድ አካባቢ እድገት እና ኢኮኖሚያዊ



የአየር ጤና ወለቴ አደባባይ መንገድ ግንባታ

እንቅስቃሴ ወሳኝ ነው ይላሉ። የተሻለ መንገድ ሲኖር ርቀት ያለው አካባቢ ቢሆንም እንኳን በፍጥነት ማሽከርከር እና ካሰቡበት ደርሶ በፍጥነት መመለስ ይቻላል ሲሉ አብራርተው፣ ጅማ መንገድ ተብሎ የሚታወቀውና የከተማዋ መውጫ ከሆኑት አንዱ የሆነው ይህ የአየር ጤና ወለቴ መንገድ የትራፊክ መጨናነቅ በእጅጉ ሲያሳስባቸው መኖሩን ይናገራሉ፡፡

በዚህ መንገድ ከጊዜ ወደ ጊዜ የተሽከርካሪውና የነዋሪው ቁጥር እየበዛ ሲመጣ መንገዱ እየጠበበ መምጣቱን ይገልጻሉ፡፡ የትራፊክ ፍሰቱ በከፍተኛ ሁኔታ እየተጨናነቀ ያለበት ይህ መንገድ ቅድሚያ ተሰጥቶት ቀደም ብሎ ሊሠራ ይገባውም አንደነበር ተናግረዋል። የመንገዱ ሥራ ሲጠናቀቅ የትራፊክ መጨናነቁ መቅረቱ አንድ ነገር ሆኖ አካባቢውም የተሻለ እድገት እንዲኖረው እንደሚያስችል አመልክተዋል፡፡

ለመንገድ ግንባታው በተያዘለት ጊዜ መጠናቀቅ በተለይ የውሃ፣ የመብራት፣ እና የቴሌ ተቋማት ተቀናጅተው መሥራት እንደሚገባቸውም አስገንዝበዋል። የእነዚህ መሠረተ ልማቶች ባለቤቶች መንግሥታዊ ተቋማት መሆናቸውን ተናግረው.፣ ተቋማቱ ተቀናጅተው በወሰን ማስከበሩ እና ምሰሶዎችን ኬብሎችን፣ እና የመሳሰሉት ማንሳት እንዳለባቸው አመልክተዋል፡፡ እነዚህ ሥራዎች በፍጥነት እንዲፈጸሙም ጠበቅ ያለ መመሪያ መሰጠት እንዳለበት አስገንዝበዋል፡፡

የትራንስፖርት ችግር አንዱ የሚመጣው ከተሽከርካሪ ቁጥር ማነስ ብቻ ሳይሆን ከመንገድ ጥበት ነው ያሉት አስተያየት ሰጪው፣ ለምሳሌ ከካራ ተነስቶ ሜክሲኮ ለመድረስ ብዙ ጊዜ የሚወስደውና የሰዓት ብክነት የሚከሰተው በትራፊክ መጨናነቅ እና በመንገድ ጥበት ምክንያት መሆኑን አመልክተዋል፡፡ የከተማዋ መውጫ መግቢያ ጭምር የሆነው የዚህ መንገድ ግንባታ በፍጥነት ተጠናቅቆ ለኅብረተሰቡ ኢኮኖሚያዊ አገልግሎት እንዲሰጥ ማድረግ እንደሚገባም አሳስበዋል።

መንገዱ ሰፋ ካለ ፈጣን ምልልስ እንዲኖር ያስችላል፤ ለአካባቢው ኢኮኖሚያዊ አንቅስቃሴ ፋይዳው ከፍተኛ ነው፤ አካባቢው ውበት እንዲጎናጸፍ በማድረግ ተፈላጊ አንዲሆን ያደርገዋል ሲሉ አብራርተው፣ ግንባታው በፍጥነት ተጠናቅቆ ለአገልግሎት እንዲበቃ ማድረግ እንደሚገባ አስገንዝበዋል፡፡

በዚህ መንገድ ፕሮጀክት ሥራ ከወለቴ አካባቢ እየተሠራ ወደ አየር ጤና የሚደረገውን ጉዞ አድንቀው፣ ቱቦዎች ወዲያው አለመሸፈናቸው ጎርፍ በሚያመጣው ቆሻሻ እንዲደፈኑና ሌላ ችግር እንዲሰከት እንደሚያደርግ ጠቁመዋል፡፡ ከሁለት ወራት በሁዋላ ክረምት እንደሚገባም ጠቅሰው፣ በመንገዱ ላይ መጨናነቅ ከመፈጠሩ በፊት ግንባታውን ማፋጠን እንደሚገባ አስታውቀዋል፡፡

የወለቴ አየር ጤና መንገድ ግንባታ ፕሮጀክት ተቋራጭ ይርጋዓለም ኮንስትራክሽን ድርጅት የሳይት መሐንዲስ የሆነው ይዲዲያ ብርሃኑ እንዳለው፤ መንገዱ የስትራክቸራል እንቅስቃሴ እየተሠራ ሲሆን፣ የመሬት ላይ ሥራውን በሚፈለገው ፍጥነት ለመሥራት የትራፊክ እንቅስቃሴው ተግዳሮት እየሆነ ነው። አካባቢው ትራፊክ እንቅስቃሴ የሚበዛበት በመሆኑ እና አንዳንድ ጊዜም ሙሉ ሙሉ የሚዘጋጋ መሆኑ በፕሮጀክቱ ግንባታ ሥራ ላይ አሉታዊ ተፅዕኖ እያሳረፈ ይገኛል፡፡

መንገዱንም ለማስፋት የተፈለገበት አንዱ ዓላማ የትራፊክ ጭንቅንቁን ለመፍታት መሆኑን ተናግራል፡፡ መንገዱ የከተማዋ መውጫና መግቢያ መንገድ መሆኑን ጠቅሶ፣ ከትላልቅ እስከ አነስተኛ ተሽከርካሪዎች ድረስ በብዛት አንደሚንቀሳቀሱበት ገልጿል፡፡ በተለይ በሥራ መግቢያና መውጪያ ሰዓት የሚታየው የትራፊክ እንቅስቃሴ ከፍተኛ ተግዳሮት መሆኑን ተናግሯል።

የሳይት መሐንዲሱ እንዳለው፤ በዚህ ወር የተሻለ ሥራ እየተሠራ ይገኛል፡፡ በግራ በኩል ከአየር ጤና ካራ ድረስ የስትራክቸር ሥራው ተሠርቷል፤ ከከተማ ሲወጣ በቀኝ በኩል ደግሞ አብነት ከሚባል እስከ ወለቴ አንድ ኪሎሜትር ያህል ስትራክቸሩም የመሬት ላይ ሥራውም ተሠርቷል።

ቀጣይ ሥራዎችን ለማከናወንም የትራፊክ መጨናነቁ ማስተጓጎል ሊያደርስ እንደሚችል ስጋቱን ጠቅሶ፣ አሁን ላይ መንገዱን ከትራፊክ እንቅስቃሴ ዝግ አድርጎ ለመሥራት እንዳልተቻለም ነው ያመለከተው፡፡ ማሽኖችም ተሽከርካሪዎችም አብረው እየተንቀሳቀሱ ባለበት ሁኔታ ሥራው እየተሠራ መሆኑን ጠቁሟል።

መንገድ ሲዘጋጋ በግንባታ ሥራው የሚሳተፈው መኪናም ተደርቦ ለመቆም ይገደዳል ሲል ይዲዲያ ገልጸዋል፡፡ አካባቢው ተለዋጭ መንገድ የሌለው መሆኑን ተናግሮ፣ አሽከርካሪዎች አማራጭ መንገድ እንዲጠቀሙ ለማስገደድ አልተቻለም፤ የትራፊክ ኃይሉ ግን ከፍተኛ እገዛ እያደረገ ይገኛል ብሏል። ከአየር ጤና እስከ ካራ ድረስ የወሰን ማስከበር ሥራ ተሠርቶ ዝግጁ መደረጉንም ተናግሯል፡፡

የሳይት መሐንዲሱ የአየር ጤና ወለቴ መንገድ ፕሮጀክት እያከናወነ የሚገኘውና ሀገር በቀል የሆነው ይርጋዓለም ኮንስትራክሽን ረጅም ዓመት ልምድ ያለው መሆኑን ጠቅሶ፣ የራሱ ማሽነሪዎች ያሉት እና ከዚህ በፊትም በጅግጂጋና ሀዋሳ በመሳሰሉት በርካታ የመንገድ ሥራዎች ላይ መሥራቱን ጠቅሷል።

በአየር ጤና አካባቢ ባለው ሳይትም በቋሚነት ከኮንስትራክሽን ስራው ጋር የሚንቀሳቀሱ እና በቅንጅት የሚሠሩ ከውሃ እና ከቴሌ፣ እና ከመብራት ኃይል ተቋማት ባለሙያዎች ጋር እየተሠራ መሆኑን አስታውቋል። ለእያንዳንዱ ለሚያጋጥሙ ችግሮች ምላሽ እያገኘን ነው ሲል ነው የተናገረው።

የሳይት መሐንዲሱ፤ በግንባታው የ24 ሰዓት ሥራን ተግባራዊ ከማድረግ አንጻር አምሽቶ መሥራት በምሽት በፈረቃ የሚሠራባቸው ሁኔታዎች እንዳሉ ጠቅሶ፣ ይህ ሥራ ከትራፊክ መጨናነቁ አንፃር ሥራ ላይ እየዋለ መሆኑን አስታውቋል።

ግብዓት የማምጣት፣ ማሽነሪዎችን የማንቀሳቀስ ሥራዎች በምሽት እንደሚሠሩ ገልጸዋል፡፡ ዝናብ በሚጥልበት ወቅት የኮንስትራክሽን ሥራው በጣም እንደሚስተጓጎል ጠቁሞ፣ እርጥበቱንና ፍሳሾችን በማድረቅ የሚሠራበት ሁኔታ እንዳለም ተናግሯል።

እሱ እንዳብራራው፤ የኮንስትራክሽን ድርጅቱ ከበቂ በላይ ማሽነሪዎች አቅርቧል፡፡ በየቦታው የተከፋፈሉ ሳይቶች ሰፊ ስለሆኑ በተለያዩ ቦታዎች ላይ እንቅስቃሴዎች ባሉባቸው ቦታዎች ሁሉ ፎርማኖች፣ ጀነራል ፎርማኖች፣ ረዳት ፎርማን፣ የሰዓት ተቆጣጣሪዎች መኖራቸው እና ሌሎች ባለሙያዎች በተዋረድ የሥራ ክትትል እና ድጋፍ እያደረጉ ይገኛሉ።

አብዛኛዎቹ በፕሮጀክቱ ሥራ እየተሳተፉ የሚገኙ ባለሙያዎችም ልምድ ያላቸው መሆናቸውን ጠቅሶ፣ ሥራውን ለማፋጠን ተጨማሪ ባለሙያዎችን ወደ ሳይቱ የማምጣት ሥራ እየተሠራ መሆኑን የሳይት መሐንዲሱ ጨምሮ አብራርቷል።

የአዲስ አበባ መንገዶች ባለሥልጣን የሕዝብ ግንኙነት ኃላፊ አቶ እያሱ ሰለሞን እንዳስታወቁት፤ የዚህ መንገድ ግንባታ ፕሮጀክት አምስት ነጥብ 67 ኪ.ሜ ርዝመት ይሸፍናል፤ ከ30 እስከ 42 ሜትር የሚደርስ የጎን ስፋት ይኖረዋል። የመንገድ ፕሮጀክቱን ሥራም ይርጋዓለም ኮንስትራክሽን የተባለ ሀገር በቀል ድርጅት የሚያከናውነው ሲሆን፣ ተቋራጩ ግንባታውን በሁለት ዓመት ውስጥ አጠናቆ ለማስረከብ የኮንትራት ውል ፈርሞ ነው ወደ ሥራው የገባው፡፡ በአሁኑ ወቅትም የግንባታ ሥራውን እያከናወነ ይገኛል፡፡

የወሰን ማስከበር ችግሮች በወቅቱ ተጠናቀው ባለመነሳታቸው ግንባታው ከሚጀመርበት ጊዜ አንድ ዓመት ያህል ዘግይቶ መጀመሩን አቶ ኢያሱ ጠቅሰው፣ እስካሁንም ድረስ የመብራት፣ የቴሌ ምሰሶዎች አለመነሳታቸውን ተናግረዋል፡፡ በዚህ የተነሳም የግንባታ ሥራው በሚፈለገው ፍጥነት እየተከናወነ አለመሆኑን ጠቁመዋል።

እሳቸው እንዳብራሩት፤ ከፍተኛ የኃይል ተሸካሚ የሆኑ የኤሌክትሪክ መስመሮች፣ በመሬት ውስጥ የተቀበሩ የቴሌ ፋይበሮች እና የውሀ መስመሮች ባለመነሳታቸው የግንባታ ሥራውን በሙሉ አቅም ለማከናወን አዳጋች ሆኗል። ከእነዚህ ጋር የተያያዙ ሥራዎች አሁንም ገና መፍትሔ አላገኙም፤ በመሆኑም በሙሉ አቅም እና በሚፈለገው ደረጃ እና ፍጥነት ሥራዎችን ለመሥራት፣ የግንባታ ሥራዎቹንም ለማከናወን አልተቻለም።

አሁን የወሰን ማስከበሩ ሥራ በተከናወነበት በሁለት ነጥብ ሦስት ኪሎ ሜትር ውስጥ የድሬይኔጅ መስመር ዝርጋታ፣ የድጋፍ ግንብ ሥራዎች፣ የአፈር ቆረጣ፣ የገረጋንቲ አፈር ሙሌት እና መሰል ሥራዎች እየተሠሩ ይገኛሉ። አጠቃላይ አፈፃፀሙም አምስት ነጥብ 59 በመቶ ላይ ደርሷል።

መንገዱ የከተማዋ ምዕራብ አቅጣጫ መውጫ መሆኑን ጠቅሰው፣ ግንባታው ሲጠናቀቅ የትራፊክ ፍሰቱን በማሳለጥ ያለው ፋይዳ ከፍተኛ መሆኑን ገልጸዋል፡፡ ለግንባታው መፋጠን በወሰን ማስከበር ሥራዎች ላይ ያለው መተጋገዝ ተጠናክሮ መቀጠል እንዳለበት አስታውቀዋል፡፡ መሠረተ ልማቶቹ በፍጥነት ከተነሱ በተያዘው የጊዜ ገደብ ውስጥ የግንባታ ሥራዎቹን ለማከናወን እንደሚቻል ይናገራሉ።

አቶ እያሱ የአየር ጤና ወለቴ መንገድ ፕሮጀክት አጠቃላይ የአየር ጤና ወለቴ መንገድ አፈጻጸም ደረጃም አራት ነጥብ 73 በመቶ አካባቢ ላይ ብቻ መሆኑን ገልጸዋል።

በአካባቢው ተለዋጭ መስመር አለመኖሩና የግንባታው መጓተት በነዋሪዎች እና በአጠቃላይ የትራፊክ እንቅሰቃሴዎቹ ላይ ትልቅ ጫና መፍጠሩን አቶ እያሱ ጠቅሰው፣ ይሄንን ከግምት ውስጥ በማስገባት ባለድርሻ አካላት የሚጠበቅባቸውን የወሰን ማስከበር ሥራ በፍጥነት መፈፀም እንደሚጠበቅባቸው አስገንዝበዋል፡፡

# ርዕሰ አንቀፅ

## ዘመኑን የሚመጥን ጉዞ ለመጓዝ የተለወጠ ማኅበረሰባዊ ማንነት ያስፈልገናል!

ለአንድ ማኅበረሰብ ሁለንተናዊ ዕድገት የአስተሳሰብ ለውጥ ወሳኝ ነው። ባልተለወጠ ማኅበረሰባዊ ማንነት የተለወጠ ሀገር መፍጠር የሚታሰብ አይደለምና። መፍጠር ይቻላል ብሎ ማሰብም ያልተገባ ዋጋ በመክፈል በትናንቶች ላይ ከመዳከር ባለፈ ሊያመጣ የሚችለው አንዳች ነገር አይኖርም። በዚህ መልኩ ያደገ ሀገርና ሕዝብም የለም።

ዛሬ ላይ በዕድገት /ስልጣኔያቸው አንቱ የተባሉ ሀገራት እና ሕዝቦች ዛሬ ላይ ሆነው ለተገኙበት መሆን የደረሱት ትናንቶቻቸውን መሻገር ያስቻሉ አዳዲስ የለውጥ አስተሳሰቦችን መፍጠር እና እሱን ተቀብሎ የሚተገብር ትውልድ ማፍራት በመቻላቸው ነው። ይህንን የሚሸከም ሀገራዊ /ማኅበረሰባዊ ሥርዓት መፍጠራቸውም ዕድገታቸው ቀጣይ እንዲሆን አስችሎታል።

እኛ ኢትዮጵያውያን የረጅም ዘመን የሀገረ መንግሥት ታሪክ፤ በተለያዩ ወቅቶች የተፈጠሩ ስልጣኔዎች ባለቤት የመሆናችን እውነታ የአደባባይ ምስጢር ቢሆንም፤ እንደ ማኅበረሰብ የአስተሳሰብ ለውጥ ሊያመጡ የሚያስችሉ የታሪክ ምዕራፎችን መክፈት ባለመቻላችን ፤በትናንቶች እና ትናንቶች በሚያስከፍሉት ዋጋ ውስጥ ለመኖር ተገደናል።

እንደ አንድ ትልቅ ማኅበረሰብ በተለያዩ ወቅቶች ወደ ቀደመው የስልጣኔ ትርክታችን እና ብሔራዊ ክብራችን መመለስ የሚያስችሉ ሕዝባዊ መነቃቃቶች ውስጥ ብናልፍ፤ መነቃቃቶቻችን ባልተለወጡ ፖለቲካዊ ፣ ማህበራዊ እና ኢኮኖሚያዊ አስተሳሰቦቻችን ተሰናክለው ፤ መነቃቃቶቹ ሊፈጥሩ የሚችሉትን የስልጣኔ ጉዞ መጓዝ ሳይቻለን ቀርተናል። በዚህም ዛሬ ላይ ላለንበት ድህነት፣ ኋላቀርነት እና ጠባቂነት ተዳርገናል።

ይህ ብሔራዊ ክብራችንን እየተፈታተነ ያለ አሁናዊ ማንነታችን ፤በቀደመው ታሪካችን ሙሉ ሆነን አንገታችንን አቅንተን እንዳንጓዝ ተግዳሮት ሆኖብናል። ራሳችንን በአባቶቻችን የደመቁ የተጋድሎ እና የስልጣኔ ታሪኮች ውስጥ ደብቀን ዘመናትን እንድንቆጥር አድርገውናል።

በርግጥ እንደሀገር በየዘመኑ ወደ ስልጣን የመጡ መሪዎቻችን ሀገርን ወደ ቀደመ ሙሉ ክብሯ መመለስ የሚያስችሉ ጥረቶችን አድርገዋል። ሁሉም በብዙ ቁጭት ዘመናቸውን በሚመጥን የለውጥ እሳቤ ውስጥ ተመላልሰዋል። አንዳንዶችም የለውጥ እሳቤያቸው በፈጠረው ተቃውሞ ብዙ ዋጋ ለመክፈል ተገድደዋል።

ሕዝባችንም ቢሆን፤ የትናንት የትልቅነት ታሪኮቹ ጥለውለት ያለፉትን ዐሻራ እያየ እና ትርክቶቻቸውን እየሰማ፤ዛሬ ላይ ካለበት እሱን ከማይመጥን ማኅበረሰባዊ ማንነት ለመውጣት የተቻለውን ያህል ጥሯል። በየወቅቱ ለተፈጠሩ የለውጥ መነሳሳቶች ያለውን አጋርነት ብዙ ዋጋ በመክፈልም በተጨባጭ አሳይቷል።

ይህም ሆኖ ግን የመለወጥ መሻታችን ሁለንተናዊ የአስተሳሰብ ለውጥን መሠረት ያደረገ ባለመሆኑ፤ በመሪዎቹም ሆነ በመላው ሕዝባችን ስለ ለውጥ የተከፈሉ ዋጋዎች የሚጠበቀውን ያህል ትርጉም ያለው ሀገራዊ ለውጥ ማምጣት ሳይችሉ ቀርተዋል። ትውልዶችንም በየዘመኑ ያልተገባ ዋጋ ሲያስከፍሉ ቆይተዋል።

ይህንን ሀገራዊ እውነታ ኃላፊነት እንደሚሰማው እና የራሱ እና የመጪ ትውልዶች ዕጣ ፈንታ እንደሚያሳስበው ትውልድ ቆም ብሎ ማሰብ ያስፈልጋል። ይህንን ማድረግ ከሁሉም በላይ የቀደሙ ስህተቶችን ላለመድገም ማስተማመኛና አሁን ለጀመርነው የለውጥ ጉዞ ስኬት ትልቅ አቅም የሚፈጥር ነው።

ይህ እንደ ማኅበረሰብ አብሮን ዘመናትን የተሻገረው ለለውጥ እሳቤዎች ያለን ባይተዋርነት፣ከትናንት እና ትናንቶች ከፈጠሩት ማንነቶች ጋር ተዛምዶ የመጓዝ ረጅም የታሪክ ጉዞ አሁን ላይ መቋጫ ሊበጅለት ይገባል። ይህን ማድረግ ቀን ሊቆጠርለት የማይገባ የህልውና ጉዳይ ነው። ከዚህ በላይ ዋጋ ሊያስከፍለንም አይገባም።

እንደ ሀገር በትናንት ያልተለወጡ ማኅበረሰባዊ ማንነቶቻችን ከዚህ በላይ መጓዝ የምንችልበት አማራጭ የለንም፤ ያደሩም ሆኑ አሁናዊ ችግሮቻችን የዚህ እውነታ መገለጫ ናቸው። ችግሩን በመሻገር ሂደት ውስጥ ከሁሉም በላይ አሁን ያለው ትውልድ ኃላፊነት ከፍ ያለ ነው። ራሱ ተለውጦ ሀገር የመለወጥ ታሪካዊ ኃላፊነትም በእጁ ነው። ይህንን ኃላፊነቱን ለመወጣት የሰከነ ስብዕና መፍጠር ብሎም የለውጥ እሳቤዎች ለሚጠይቁት መስዋእትነት ራሱን ማዘጋጀት ይጠበቅበታል!


# አዲስ ዘመን

ኢፕድ

ግንቦት 30 ቀን 1933 ዓ.ም ተቋቋመ

**የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት ዋና ስራ አስፈጻሚ**

ስልክ ቁጥር - 011-126-42-22

ኢሜል ፡- epa@press.et

**ዋና አዘጋጅ**

አንተነህ ኃ/ብርሃን ወ/መድህን

**አድራሻ**

ንፋስ ስልክ ላፍቶ ክ/ከ

ወረዳ 06

የቤት ቁጥር 319

ኢሜይል - anteneh.hailebirhan@press.et

ስልክ ቁጥር - 011-1-26-42-40

**የገበያ ልማትና ፕሮሞሽን ዘርፍ**

ኢሜይል - etpresspromotion@gmail.com

ስልክ - 011-126-43-41

ፋክስ - 011-811-13-15

የዝግጅት ክፍል ፋክስ - 251-011-1-56-98-62

**የአዲስ ዘመን ማኔጂንግ ኤዲተር**

ወንድወሰን ሽመልስ ታደሰ

ስልክ፡- 011 126 4200

Email:- wendweson.shimelis@press.et

wendwesonshimelis@gmail.com

**የአዲስ ዘመን ምክትል ዋና አዘጋጆች**

- ወርቁ ማሩ
- ኃይሉ ሣህለድንግል
- እስማኤል አረቦ
- ቦጋለ አበበ

**የማስታወቂያ መቀበያ ክፍል**

ስልክ ቁጥር - 011-156-98-73

ፋክስ - 011-126-58-12

ቴሌግራም - 097- 608-47-07 - Press

**የማስታወቂያ ሽያጭ ማስተባበሪያ**

ስልክ - 011-1-26-43-39

**ማከፋፈያ** ፡- ስልክ ቁጥር - 011-157-02-70


# ነፃ ሃሳብ

ይህ አምድ በተለያዩ ፖለቲካዊ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ጉዳዮች ዙሪያ ዜጎች ነፃ ሀሳባቸውን የሚሰጡበት ነው፡፡በዓምዱ ላይ የሚወጡ ጽሁፎች የዝግጅት ክፍሉን አቋም አያመለክቱም፡፡

## መተባበርንና መቻቻልን የሚያጎለብቱ ተግባሮች ይጠናከሩ!

**ሰው መሆን**

ዘመናትን የተሻገረ ሀገረ መንግሥት አላት። አያሌ የብርሃንና የጨለማ ጊዜያት ተፈራርቀውባታል። ዛሬ ለመቆሟ ትናንት የተተከሉት ምሰሶዎች ምክንያት ናቸው። ለእዚህም ነው ወጀብ በመጣ ቁጥር መሠረቷ የማይነቃነቀው፤ ይልቁንም የጠበቀው።

ህብርና ኅብረት መገለጫዎቿ ናቸው። ሃይማኖት፣ ባህል፣ ማህበረሰብና ሌሎች እሴቶችን ልክ እንደ ልዩ ልዩ ህብረ ቀለማት አጣምራ ይዛለች። ይህቺ ሀገር ነብዩ መሐመድ እጃቸውን ወደ ምእራብ በመጠቆም «ሂዱ ወደ ምእራብ፤ በእዚያ አንድ የሀበሻ ንጉስ ታገኛላችሁ....የሚነካችሁ አንዳች ነገር የለም» ሲሉ ለተከታዮቻቸው ከስጋታቸው ነፃ ሆነው በነፃነትና በመቻቻል እንዲኖሩ የላኳቸው፤ እነርሱም ያለስጋት የመጡባት ሀገር ኢትዮጵያ ነች።

ከእዚያን ጊዜ አንስቶ በህብርና በፍቅር ሕዝቦች የሚኖሩባት ሀገር፣ በጊዜያዊ ውጣ ውረድ ሳትፈተን በአንድነት የሚኖርባት ሆና ፀንታለች። ኢትዮጵያ ህብረ ብሔራዊነቷንና ሃይማኖቶቿን እንደ ደካማ ጎን ቆጥረው ሊያፈርሷት የሞከሩ በርካታ ጠላቶቿ በማሴብት ጉድጓድ ሲወድቁና ሀገረ መንግሥቷ ሲቀጥል በተደጋጋሚ ታይቷል። ይህን ጥንካሬ ያገኘችውና ለጠላቶቿ እጅ ሳትሰጥ የቆየችው ለዘመናት ባዳበረችው የመቻቻልና የአብሮነት እሴት ምክንያት ነው።

«ሀገር የጋራ ነው። ሃይማኖት የግል ነው» በሚለው እሳቤ ማንኛውንም አይነት እምነት በነፃነት የሚያከብር እንዲሁም አንድ በሚያደርጉና የጋራ በሆኑ እሴቶች ላይ ደግሞ ጠንካራ ማህበረሰባዊ ትስስር ያለው ድንቅ ሕዝብ መፍጠር ተችሏል። ይህ ዛሬ መሽቶ ሲነጋ ያየነው ጉዳይ ሳይሆን ከጥንትም የነበረ በጠንካራ የመቻቻል መሠረት ላይ የተገነባ እሴት ነው።

ከላይ ለማንሳት እንደሞከርነው ኢትዮጵያና ኢትዮጵያዊነትን ለማዳከም ብዙዎች በተናጠልና በትብብር ሠርተዋል። ለዚህ እንደ ደካማ ጎን የተመለከቱት ደግሞ የኢትዮጵያን የብዝሃ ሃይማኖት አጀንዳ ነው። ይሁን እንጂ እነዚህ አካላት አንድ ያልተረዱት ጉዳይ ነበር። ለኢትዮጵያውያን ብዝሃ ሃይማኖት ጥንካሬ እንጂ የደካማ ጎን መገለጫ አለመሆኑን አልተረዱም። በዚህ ምክንያት ሃሳባቸው ዳር ሳይደርስ መና ሆኖ እንዲቀር፤ ለወደፊቱም ይህ እኩይ አላማቸው ቅዥት እንዲሆን አድርጎታል።

በኢትዮጵያ የሃይማኖት መከባበርና መቻቻል መገለጫ ከሆኑት መካከል ወሎ፣ ሐረር፣ ድሬዳዋ፣ አዲስ አበባ እና ሌሎችም እያልን...ብዙ ምሳሌ መጥቀስ እንችላለን። እነዚህን እንደ ምሳሌ አነሳን እንጂ በመላ ሀገሪቱ አንዱ የአንዱን ሃይማኖት አክብሮ፣ በዓላት ሲደርስ መልካም ምኞት ተገላልጦ በጋራ በደስታ የሚያሳልፍ መሆኑ ፀሐይ የሞቀው ሀቅ ነው።

ይህ ድንቅ እሴት እንዲቀጥል የማይፈልጉ አካላት በተለያየ ጊዜ እጅግ ዘግናኝ ድርጊቶችን ፈፅመዋል፤ ከንቱ ፕሮፓጋንዳ አሰራጭተዋል። ይህ የጥፋት ድርጊት ግን በማህበረሰቡ አርቆ አሳቢነት እንዲሁም ለዘመናት በገነባው ማህበራዊ ጉልበት ሊከሽፍ ችሏል።

ዛሬም በዓላት በመጡ ቁጥር፣ አጀንዳዎችን እየመዘዙ ማህበረሰቡ ውስጥ እኩይ ሃሳብ ለመጨመርና የመከፋፈል አጀንዳ ለማራመድ የሚቅበዘበዙ አይጠፉም። ሃቁ ግን ዛሬም እንደ ጥንቱ፤ ዛሬም እንደ ትናንቱ ኢትዮጵያውያን ለእነዚህ ትናንሽ አጀንዳዎች ልባቸውን ሳይከፍቱ ማህበራዊ መሠረታቸውን ይበልጥ የሚያጠናክሩ መልካም ጉዳዮች ላይ አተኩረው እያየናቸው ነው።

ለዚህ ጥሩ ምሳሌው የረመዳን ፆም ገብቶ እስኪፈታ ድረስ የሚታየው አብሮነትና መደጋገፍ ነው። ባለፈው አንድ ወራት ኢትዮጵያውያን የሃይማኖቱ ተከታዮችም ይሁኑ ከዚያ ውጪ የሆኑ ዜጎች ፆሙ በሰላም ተጀምሮ እንዲጠናቀቅና በዓሉም በድምቀት እንዲከበር ለማድረግ እርስ በእርስ ያሳዩት ፍቅርና መቻቻል በሌሎች የዓለማችን ክፍሎች ለሚኖሩ ሰዎች ሁሉ አስተማሪ ነው። ከ«መልካም ፆም» ምኞት መግለጫ ጀምሮ ለሃይማኖቱ ተከታዮች እስከ በተለያዩ ቦታዎች እስከተደረጉት አፍጥሮች ድረስ የታየው መደጋገፍ በአርአያነት ሊጠቀስ የሚገባው ደማቅ ተግባር ነው።

ይህ መቻቻል፣ መከባበር እና ራስን በሌሎች ቦታ አስቀምጦ መመልከት ሀገር በጠንካራ ምሰሶ ላይ ለመቆሟ ምሳሌ ነው። ኢትዮጵያ በዚህ መሰል ኅብረት የተገነባች ሌሎች ማህበራዊ ውጥንቅጦችንም በተመሳሳይ ቀና መንፈስ መፍታት እንደምትችል ያመላክታል።

ኢትዮጵያ «ተመስገን ረመዳን በሰላም ተከበረ የሚል ክርስቲያን፤ አሏህ አምዲሊላሂ ታቦቱ በሰላም ገባ የሚል ሙስሊም» ያለባት ነች። የእምነቶች ትክክለኛ መሠረት ሰላም ለመሆኑ ማሳያ እንደ ኢትዮጵያ ያለ ሀገር የትም ፈልጎ ማግኘት ይከብዳል።

ይህንን ፍፁም ሰላም፣ መከባበርና መቻቻል ለመናድ የሚጥሩ ደግሞ አይጠፉም። ለዚያ ነው ለግል ጥቅማቸው፤ ለፖለቲካ ፍላጎቶቻቸውና፣ ለስልጣናቸው ሲሉ ጠንካራውን መሠረት ለመሸርሸር የሚማስኑ የሴራ ቀማሪዎችን በየገዜው የምናየው። ለዚህም ነው «ማህበረሰቡ መሰል ድርጊቶችን በስከነ መንፈስና በጥንቃቄ ሊመለከተው ይገባል» የሚል መልእክት ለማስተላለፍ የምንወድደው።

የኢትዮጵያ ሕዝብ የትኛውንም አይነት የፖለቲካ ፍላጎት፣ ርዕዮተ ዓለም የሚያቀነቅኑ ፖለቲከኞች ሃይማኖትን ሕዝብን ለመከፋፈያ አጀንዳነት እንዳያውሉ በፅናት መቆምና መታገል ይኖርበታል። ሃይማኖት ሰላም ነው። ሃይማኖትን ተገን የሚያደርጉትን መገሰፅ ደግሞ የሰላም እርምጃ ሀሁ ሊሆን ይገባል። ለዚህ እርምጃ ምሳሌ የሚሆን ጉዳይ ለማግኘት ደግሞ ሩቅ መጓዝ አይጠበቅብንም። ጥንታዊ ዶሴዎቻችንን፣ ታሪካችንን ካገላበጥን አያት ቅድመ አያቶቻችን በብልሃት መሰል ሴራዎችን ሲያከሽፉ እንደኖሩ በሚገባ መረዳት እንችላለን። ከሁሉም በላይ ግን ትናንት የነበረን ፍቅር ዛሬም አብሮን ስለመኖሩ የሚያረጋግጡልንን ድርጊቶች ማቆም አይኖርብንም።

ለዚያ ነው መተባበርን እና መቻቻልን የሚያጎለብቱ ተግባሮች ለሁልጊዜም እንዲቀጥሉ ማሳሰብ የምንወድደው። ትንሽ መስለው የሚታዩ «አይዞህ፣ በርታ፣ ከጎንህ ነኝ» የሚሉ መልካም ምኞቶች፣ ከጎናችን ለሚኖረው ጎረቤታችን ከማፅናኛም ያለፈ ኅብረትና መተባበርን ምርጫው እንዲያደርግ የሚያስችለውን አቅም ይፈጥራሉ።

በሃይማኖት የማይመስሉን ወዳጆቻችን አብረውን እንዲዘልቁ የእኛ ቀና አመለካከት ልዩ ትርጉም ይኖረዋል። ከሁሉም በላይ ግን በሃይማኖቶች፣ በብሔሮች መካከል ሽንቁር ፈጥረው ስልጣናቸውን ለማስቀጠል የሚተጉ ኃይሎች፣ የፖለቲካ ቡድኖች ምንም አይነት ክፍተት እንዳያገኙ ያደርጋል።

በዚህ መሠረት ዛሬ ኢድ አል ፈጥርን (ረመዳን) ስናከብር ከሌሎች የሃይማኖት ተከታዮች ጋር ይበልጥ በሚያቀራርቡ በጎ ምግባሮች፣ መቻቻሎች፣ የአብሮነት እሴትን በሚያጠናክሩ ድርጊቶች ሊሆን ይገባል። ዛሬ የኢትዮጵያውያንን ታላላቅ መሠረቶች ለመናድ የሚያሰፈስፉ ቡድኖች ምንም ክፍተት እንደማያገኙ የሚያውቁበት ማስረጃ ማግኘት ይኖርባቸዋል።

በዋናነት ግን «ኢስላም ሰላም ፣ የሰብአዊነት እና የሰው ልጆች የፍቅር መንገድ መሆኑን የምናሳይበት በዓል ልናደርገው ይገባል» የሚለው የዛሬው ቁልፍ መልእክታችን ነው። መልካም ኢድ አል

ፈጥር (ረመዳን) ለመላው የእስልምና እምነት ተከታዮች ይሁን። ሰላም!!

ማህበራዊ

# እንዲህም ይኖራል

ሕይወት ፈርጀ ብዙ ገጽታዎች አሏት፤ መውጣት እንዳለ ሁሉ መውረድም ይኖራል። ከመውረድ ውስጥም በተጋት መውጣት ይቻላል። አግኝቶ ማጣት እንዳለ ሁሉ አጥቶም ይገኛል። ይህ የሕይወት እውነታ ነው፤ በጥቂቶች የህይወት መውጣትና መውረዶች ውስጥ ብዙዎች ይማራሉ። የህይወትን ፈተናዎችም ያውቃሉ። በከፍታ ውስጥ የሚገኙት ‹‹እንዲህም ይኖራል እንዴ?›› ብለው ራሳቸውን ይጠይቃሉ። ስተቸገሩት ያዝናሉ፤ ካሳቸው ቀንሰው የሴሎችን ችግር ይካፈላሉ፤ በተጨማሪም ችግር ብልሃትን ያስተምራል እንዲሉ ከችግር ጋር ተላምዶ ከመኖር ይልቅ ለመፍትሄ የሚታትሩትንም ያበረታታሉ። በመሆኑም ‹‹እንዲህም ይኖራል›› ብለን በከፈትነው አምዳችን ህይወትን በየፈርጁ ታስተውሉበት፤ ˆአስተውሳችሁም ትማሩበት ዘንድ ጋበዝናችሁ። ለአስተያየቶቻችሁ፤ ለመሰል ታሪኮች ጥቆማችሁ እንዲሁም ለድጋፋችሁ የዝግጅት ክፍላችን አድራሻ ትጠቀሙ ዘንድ ጋበዝናችሁ።

## መልካሚቱ እረኛ - ስለ አንዲቱ ግልገል ...

መልካምሥራ አፈወርቅ

### እንደ መነሻ ...

ሀድያ ዞን ‹‹እሙጨራ›› ቀበሌ መሬቱ ለምለምና አረንጓዴ ነው። ስፍራው ያሉ ነዋሪዎች እንሰትና ቡና ያመርታሉ። ከአብዛኞቹ ጎተራ በቆሎና ስንዴ ይታፈሳል። መሬቱ የሰጡትን አብቃይ ነውና ጠንካሮቹ አርሶአደሮች ዓመቱን ሙሉ ሥራ አይፈቱም።

ዓለሚቱ ሳሙኤል የብርቱ ገበሬ ልጅ ነች። እሷን ጨምሮ መላው ቤተሰብ መተዳደሪያው የግብርናው ፍሬ ነው። የቤቱ አባወራ ከእርሻው ጎን ጎን ጠንካራ ይሉት ነጋዴ ናቸው። የሰባቱ ልጆቻቸውን ዓለም ለማየት የመጀመሪያ ምርጫቸው ሁሉንም ማስተማር፣ ዕውቀትን ማስጨበጥ ሆኗል። ልጆቻቸውን በወግ አስተምረው ለቁምነገር ማድረስ ይሻሉ።

በነ ዓለሚቱ ቤት ከትምህርት ያልዋለ፣ ከቀለም ያልተዛመደ ልጅ የለም። ዛሬን ከገጠር ኑሮ አልፎ ነገን በተሻለ ለመራመድ ሁሉም ትምህርትን የሙጥኝ ብሏል። አባወራው ቤታቸውን አሸንፈው ልጆችን ለማሳደግ በብርታት ኖረዋል። ሰባቱም ልጆች የእናት አባታቸውን ቃል አክብረው በታዛዥነት ዘልቀዋል። መላው ቤተሰብ ተከባብሮ ፣ተዋዶ መኖርን ያውቃል።

### በድንገት...

ከቀናት በአንዱ በዚህ ቤተሰብ መሐል የደረሰው ኃዘን የሁሉንም ልብ ሰበረ። የአባወራው ድንገቴው ሞት የእማወራዋን አንገት አስደፋ። ነገን አርቀው የሚያዩ ልጆች በተስፋ መቁረጥ ቀናት ገፉ። ይህ ስሜት በጠንካራዋ እናት ሊመለስ አፍታ አልፈጀም። የባላቸውን ትከሻ የተኩት ወይዘሮ ጥርሳቸውን ነከሱ። ልጆቻቸው ከትምህርት እንዳይቀሩ፣ ከመንገድ እንዳይሰናከሉ በአባወራው መንገድ ተጓዙ ።

ጥረታቸው ከእርምጃ በላይ ሆነ። የሰበራቸውን ኃዘን እጁን ይዘው ሰበሩት። ተስፋ መቁረጥን ቀድመው አሸነፉት። ዓለሚቱና ስድስት እህት ወንድሞቿ የአባታቸው ምኞት በጠንካራዋ እናት ብርታት ከግቡ ደረሰ። ሁሉም ያለአንዳች ስንፍና ትምህርታቸውን አጠናቀቁ።

የቤቱ አራተኛ ልጅ ዓለሚቱ የእናቷን ልፋት፣ ድካም አትዘነጋም። ከአባታቸው ሞት በኋላ እማዋራዋ ስለልጆች የከፈሉት ዋጋ ቀላል አለመሆኑን ታውቃለች። ዛሬ ላይ ቆማ ትናንት የሆነውን ስታስብ ዓይኖቿ በዕንባ ይሞላሉ። ከዚህ ስሜት ባሻገር ስለእናቷ ያላት ፍቅርና ክብር ለየት ይላል።

ዓለሚቱ ትምህርቷን እንዳጠናቀቀች ከትውልድ ቀዬዋ ርቃ ሆሳዕና ላይ ከተመች። ሆሳዕና ትልቅ እህቷ አለችና እንግድነት አልተሰማትም። በዚህ ስፍራ ለመነገድ ራስን ለመቻል ያመቻል። ከእህቷ ዘንድ የጀመረችው የሱቅ ንግድ የአባቷ ሙያ ነው። በሥራው ልትቀጥል አልከበዳትም።

ወጣቷ በዚህ ውሎ ራሷን መቻሏ ከሌላ አጋጣሚ ጣላት። ሆሳዕና የእንጀራ ክፍሏ ብቻ አልሆነም። ከብቸኝነት የምርትቅበት፣ ቁምነገርን የምታስብበት ጭምር እንጂ። የትዳር አጋሯን ያገኘችው፣ በዚህ ከተማ ነበር። እሷን ያለው ሰው በቀረባት ግዜ አልገፋችውም። ስለእሱ በጎነት የተነገራት ሁሉ እውነት ሆኖ አገኘችው። ልቧ ከልብ ፈቀደው።

### ሶስት ጉልቻ...

ዓለሚቱ ሆሳዕና ላይ የጀመረችው የሱቅ ንግድ ከትዳሯ አገናኝቶ ጎጆ ቀልሳለች። በግብርና የሚኖረው ባለቤቷ ስለሚስቱ ክብር አለው። ሆሳዕና ላይ የጀመረው ሕይወት መልካም ሆኖለታል። ጥንዶቹ ስለነገ ብዙ ያልማሉ። ልጆች ወልዶ ለማሳደግ ፣ወግ አድርሶ ቁምነገር ለማየት ምኞታቸው ነው።

ውሎ አድሮ የባልና ሚስት ጎጆ በልጅ ፍሬ ተባረከ። የመጀመሪያውን ወንድ ልጅ አቅፈው ሳሙ። የሕጻኑ ጌዲዮን ለቅሶና ሳቅ ቤቱን በፍቅር ሞላው። የትዳራቸው መልካምነት በጥንዶቹ መተሳሰብ ተገለጠ። ጌዲዮን ጥቂት ከፍ እንዳለ ሁለተኛው ልጅ ተወለደ። ይኼኔ ደስታቸው በእጥፍ ጨመረ። ትንሹ ዳግም ወንድሙን ከብቸኝነት የሚታደግ ሕጻን ሆኖ የቤቱን በረከት አበዛ።

### ሦስተኛው ልጅ...

አሁን ደግሞ ሦስተኛው ልጅ ቤቱን በእንግድነት ተቀላቅሏል። ከዚህ ቀድሞ ሁለት ወንድ ልጆች ያገኘው አባወራ በሦስተኛው ሕጻን መምጣት የልቡ ሞልቷል። የውስጡ ምኞት ሴት ልጅን መታቀፍ ቢሆንም ከፈጣሪ ባገኘው ስጦታ አልተከፋም። ውስጡ ደስታን ሸምቷልና ስለሆነለት በረከት ዝም አላለም። ‹‹ልጅ ተጨመረልኝ፣ ሌላ ተካበልኝ›› ሲል ትንሹን እንግዳ ‹‹ተካበ›› ሲል ሰይሞታል። ተካበ ለእሱ ተጨማሪ ደስታ ነው። የቤቱ ሌላ በረከት ሆኖ ታክሏል።

ተካበ በሁለት ወንድሞቹ መሐል ደስተኛ ሆኖ ማደግ ጀመረ። መልካም ባሕሪ መገለጫው ነው። ከፊቱ ደማቅ ፈገግታ አይጠፋም። ገና ከልጅነቱ ትኩረቱ ልዩ ሆኗል። እንደወንድሞቹ ማንበብ መጻፍን ይፈልጋል። ዕድሜው ሲደርስ ትምህርት ቤት ሊገባ ግድ ሆነ። ትንሹ ተካበ የልቡ ምኞት ሞላ። እንደእኩዮቹ አፀደ ሕፃናት ገብቶ እንደ ምኞቱ መማር ጀመረ።

ተካበ የትምህርት ጅማሬው ማስደነቅ የያዘው ሳይውል ሳያድር ነበር። ከሌሎች ይበልጥ ጎበዝ መሆኑ ምስጉን አደረገው። በየግዜው በአድናቆት በሽልማት፣ ተንበሸበሸ። ቆይታውን አጠናቆ አንደኛ ክፍል ሲገባ ጉብዝናው አልራቀውም። በትምህርቱ ልቆ አንደኛነትን ተቀዳጀ።

### ከቀናት በአንዱ...

ትንሹ ተካበ የትምህርት ቤት ውሎው በጨዋታ የተሞላ ነው። ከእኩዮቹ ጋር መዝለል መጫወት ደስ ይለዋል። እንደልጅ ኳስ መጠለዝ፣ በአባሮሽ መዞር ይወዳል። ከቅርብ ግዜ ወዲህ ግን ፍላጎቱን የሚገታ ነገር ይሰማው ጀምሯል። ገና ሊራመድ ሲሞክር ጉልበቱን በሚይዘው ስሜት እየተረበሸ ነው። እንዲያም ሆኖ ከሩጫው አይቆምም። እያመመው ይቦርቃል፣ እየተሰማው ይፈነጥዛል።

አንድ ቀን ተካበ ኳስ እየተጫወተ በድንገት ወደቀ። ከወደቀበት ሲነሳ የተለየ ሕመም ተሰማው። ከትምህርት ሲመለስ ለእናቱ የሆነውን ሁሉ ነገራት። እናት እግሩን፣ ጉልበቱን እያሻሸች ችግሩን ልታውቅ ሞከረች። ተካበ ክፉኛ አሞታል። የእናቱ እጅ እንዳይነካው መጮህ፣ መከላከል ያዘ።

ውሎ ሲያድር ሕመሙ ባሰ። ትምህርት ቤት ለመሄድ፣ ቆሞ ለመራመድ ጭንቅ ሆነ። ቤተሰብ አብዝቶ ቢያስብ ቢጨነቅ ልጁን ከወጌሻ ዘንድ ወሰደው። ወጌሻው የጉልበቱን ችግር አስተዋለ፤ ለማሸት አልደፈረም፣ እጁን አላነሳም፣ ለማሰር ፈጥኖ አልወሰነም። እንደነበር መልሶ ለቤተሰቡ አስረከበ።

ትንሹ ተካበ ከሕመሙ አልዳነም። እንደልጅ መሮጥ መራመድ እያማረው ከቤት ዋለ። አንድ ቀን ደግሞ አንድ ጓደኛው አዝሎት ሲጫወት በጀርባው ወደቀ። ይህ አጋጣሚ ለትንሹ ተካበ የከፋ ስቃይ አስከተለ ።

ወራት ተቆጠሩ። እናት አባት ስለ መፍትሔው በየቦታው ሮጡ። ችግራቸውን ያዩ አንዳንዶች በመላ ምት አስጨነቋቸው። የልጁ ሕመም ክፉ መንፈስ ነው ያሉ፣ በራሳቸው ሀሳብ ብዙ አሏቸው። ዓለሚቱና ባለቤቷ ስለልጃቸው መዳን በየቦታው ዋተቱ። የተገኘ መፍትሔ አልነበረም።

### ከአንገቱ ስር ...

ውሎ አድሮ በተካበ አንገት ስር አንድ ምልክት ተስተዋለ። እናት በዓይኗ ያየችውን በእጆቿ ዳብሳ ልታውቅ ሞከረች። በቀላሉ የሚለይ ጠንካራ ዕብጠት ነበር። እሱን ተከትሎ የመጣው ቶንሲል ሌላ ስቃይ ሆነበት። ፈጥኖ ከሆስፒታል የደረሰው ሕጻን አስቸኳይ



ምርመራ ተደረገለት። ከሐኪሞች የተገኘው ውጤት የደም መርጋት መሆኑን አረጋገጠ።

የቀዩ ደም ሴል መውረዱን ተከትሎ ተካበ ለከፍተኛ ሕክምና ወደ አዲስ አበባ መላክ ነበረበት። ጎበዙ ተማሪ፣ ተስፋ የተጣለበት ለጋ ጅምር ትምህርቱን አቋርጦ ጥቁር አንበሳ ሆስፒታል ሊላክ ግድ ሆነ። እናት አባት የተጻፈላቸውን ማስረጃ ይዘው ከሆስፒታሉ ደረሱ።

በድንገተኛ ክፍል ሕክምናው ፈጥኖ ተጀመረ። እነሱ እንዳሰቡት ቆይታው በቀላሉ የሚጠናቀቅ አልሆነም። ጊዜው ቀናትን አስከትሎ ወራት ተቆጠሩ። የሆስፒታሉ ተከታታይ ሕክምና ሲጠናቀቅ ባልና ሚስት ልጃቸውን ይዘው መውጣት ግድ ይላቸዋል። አዲስ አበባ ‹‹የእኔ›› የሚሉት ማረፊያ ዘመድ የለም። በማያውቁት ስፍራ እንደልብ ወጥቶ መግባት ይቸግራል።

### ምስጢረኛው አባት...

የጥቁር አንበሳ የሕክምና ሂደት ለትንሹ ተካበ ቀላል አልነበረም። በልጅነት አቅሙ መድኃኒቶችን መጠቀም፣ ከአካሉ ወሳኝ ናሙናዎችን መውሰድ ፈታኝ የሚባል ስቃይ አለው። ዓለሚቱ ልጇ ሕመም ላይ መሆኑን እንጂ ምን እንደታመመ ያወቀችው የለም። አባት ከሐኪሞች የተነገረውን ውጤት በምስጢር ይዞ ብቻውን ይብሰለሰላል። የሰማውን ለሚስቱ አጋርቶ ችግሩን የእኩል ማድረግን አላጣውም። ይህ እንዳይሆን ስለሚስቱ ጤና ተጨነቀ። ስለ እርሷ ሠላም አሰበ። ውጤቱን ድንገት ብትሰማ የምትሆነውን አያውቅም። እናም በልጁ ሕመም ብቻውን ታመመ። በያዘው ምስጢር በውስጡ ጋየ።

### የሕክምናው ውጤት...

ትንሹ ልጅ ተካበ ሕመሙ የደም ካንሰር መሆኑ ተረጋግጧል። በአባትዬው ውስጠት ያለው ምስጢር የግሉ ብቻ አልሆነም። ከቀናት በኋላ እናት ዓለሚቱ እውነቱን ማወቋ ግድ ሆኗል። በወቅቱ ስለካንሰር የሚገልጹ የሙሉ መረጃ በራሪ ወረቀቶች በእጇ ይደርሷት ነበር። እንዲህ ሲሆን ነጋሪ አላሻትም፣ አሁን ስለ ልጇ ሕመም ድብቅ ምስጢር የለም። ፊቷ ካለው ሐቅ ጋር ልትጋፈጥ ጊዜው ደረሰ።

እናት ስለተካበ ሕመም ባወቀች ግዜ ውስጧ አምኖ ሊቀበል ቸገረው። ካንሰር በሕጻናት ላይ ስለመከሰቱ ለአንድም ግዜ ሰምታ አታውቅም። ለቀናት ራሷን ካረጋጋች በኋላ አባወራው ወደ ቤት ሊመለስ ተወሰነ። ባልና ሚስት ስለአንዱ ልጃቸው ጤና መላውን ቤተሰብ ትተው ከሀገር ከራቁ ሰንብተዋል። በቤታቸው ሁለቱ የተካበ ታላላቆችና ከእሱ ኋላ የተወለዱት ሁለት ሴት ሕጻናት በዘመድ እጅ ናቸው። አሁንም ሕክምናው ተጨማሪ ጊዜን ይፈልጋል።

ዓለሚቱ ተካበን ይዛ አዲስ አበባ ቀርታለች። አሁንም እግሮቹ በወጉ አይራመዱም። ራሱን ችሎ መቆምና መቀመጥ አይችልም። ጤናው ጨርሶ አልተመለሰም። በየግዜው የሚወስደው ሕክምና በእሱ አቅም የሚከብድ ነው። በዕድሜው ሰባተኛ ዓመቱን ደፍኗል። ቁመቱ መለሎና ረጅም በመሆኑ እንደ ልጅ አዝሎ ለመንቀሳቀስ ያዳግታል።

እናት በመጀመሪያዎቹ ቀናት የወሰዳቸው ሕክምናዎች አስጨናቂነት ዛሬም ድረስ ውል ይላታል። ለሰዓታት ራሱን ይስት ነበር። ከጀርባ አጥንቱ ላይ የመቅኔ ምርመራ ሲወሰድ ደግሞ በሕይወት አለመኖሩን እስኪታምን በተስፋ መቁረጥ ተመላልሳለች። የሀያ ስምንቱ ቀናት ኬሞ ቴራፒ በከባድ ሕመምና ስቃይ የተሞላ ነበር።

አንዳንዴ ዓለሚቱ ስለልጇ ክፉው ብቻ ይሰማታል። ድንገት የሚሞት የሚለያት ሲመስላት አምርራ ታለቅሳለች። አባወራው ግን ሁሌም ራሱን አጠንክሮ እሷን ያበረታል። ዘወትር ውስጡ የሚነግረው ልጁ በሕክምናው ዘልቆ ፈጽሞ እንደሚድን ነው።

ይህ ዕምነቱ ወደ ዓለሚቱ እንዲጋባ በፈጣሪ ያለውን መተማመን ይነግራታል። እናት ዓለሚቱ አሁን ባለቤቷን ወደ ቤቱ ሸኝታለች። ከእሱ የወሰደችው ጥንካሬ ግን ዛሬም ከእሷ ጋር ነው። ሕክምናው አሁንም ቀጥሏል። ባልና ሚስት አዲስ አበባ ላይ ሁነኛ ዘመድ የላቸውም። ይህ እውነት ለብዙ ችግሮች ይዳርጋል።

### የታበሰ ዕንባ...

አሁን በእነሱ አቅም የሆስፒታሉን ሕክምና በተመላላሽ መቀጠል የሚቻል አይደለም። ይህ የገባቸው ልበ መልካሞች ዓለሚቱ ልጇን ይዛ ወደምታርፍበት የማቲዎስ ወንዱ ካንሰር ሶሳይቲ አመላከቷት። በዚህ ቅጥር በርካቶች ከፍቷቸው መጥተው ዕንባቸውን አብሰው ተመልሰዋል። የታመሙ ድነው ቤታቸው ገብተዋል ።

ዓለሚቱ ልጇን ይዛ በመጣች ግዜ ቤቷ እስኪመስላት በእፎይታ ተንፍሳለች። አሁን ስለልጇ ሕክምና፣ አስፈላጊ መድኃኒትና ምግብ እንዳታስብ ጎዶሎዋ ሞልቷል። አራቱን ልጆቿን ትታ ከቤት ከወጣች ወራት ተቆጥረዋልና ብዙ ታስባለች።

እናት ሁሌም ናፍቆትና ትዝታ ይፈትኗታል። ልጆቿ በራቧት፣ በናፈቋት ግዜ በስልክ ታወራቸዋለች። በእጇ ያለው ፎቶግራፋቸው ደግሞ ዘወትር ከእርሷ ጋር ውሎ ያድራል። አንዳንዴ በትዝታ ርቃ በሀሳብ ታወጋቸዋለች። ይኼኔ እንደ እናት የሚታያት ደግ ደጉ ብቻ አይደለም። ከሳቃቸው ይልቅ ለቅሷቸው፣ ከደስታቸው ደግሞ ኃዘናቸው ልቆ ይሰማታል።

ሁለቱ የተካበ ታላቆች ትምህርት ቤት ይውላሉ። የእሱ ታናሽ ስድስት ዓመቷ ነው። ከእሷ ቀጥላ ያለችው ሕጻን ደግሞ በወጉ ጡት ያልጣለች ሁለት ዓመት ያልሞላት ጨቅላ ናት። በተለይ እሷ ከእናቷ ጉያ መውጣት፣ ከዓይኗም መራቅ የማይገባት ነበረች። ይህን ስታስብ ዓለሚቱ አንገቷን ትደፋለች። የልጆቿ ናፍቆት የትዳሯ ድምቀት በዓይኗ ጥግ ይዞራል።

አሁን ሕጻኑ ተካበ ጤንነቱ መልካም ሆኗል። ሕክምናው ባያበቃም። ቀና ብሎ እየሄደ ነው። እግሮቹ እርምጃቸው ተሻሽሏል። ባለቤቷ ከአይኗ ቢርቅም በሀሳብ ሁሌም ከጎኗ ነው። ስለልጇ ልጆቿን ትታ በደጅ ስላለችው ወይዘሮ አክብሮቱ ከፍቅር ጋር ነው።

### ስለአንዱ ሴሎቹን...

እናት ዓለሚቱ ስለአንድ ልጇ የከፈለችው ዋጋ ዘጠና ዘጠኙን በጎች በዱር ትቶ አንዲቱን ግልገል ፍለጋ እንደወጣው መልካም እረኛ ይመስላል። እሷ ተካበን አስታማ ለማዳን ከቤት ከቀዬዋ ርቃለች። ለአንድ ልጇ መኖር ስትልም አራት ልጆቿን ትታለች። ዛሬ ስለጤናው መድኃኒቱን አግኝታለችና ነገ ወደ ቀሪዎቹ ልጆቿ እንደምትመለስ ጥርጥር የላትም።

መዝናኛ

# ማረፊያ/ ትዝብት

## በአፍ ይጠፉ በለፈለፉ

**መልካምሥራ አፈወርቅ**

አንዳንዴ እንደዋዛ የምንጀምራቸው ጉዳዮች መጨረሻቸው ላያምር ይችላል፡፡ በተለይ አነሳሳችን ጤናማነት የጎደለው ከሆነ ፍጻሜው እንደ አጀማመሩ በጣፋጭነት መቋጨቱ ጥያቄ ውስጥ ይገባል፡፡

‹‹ውሃ ሲወስድ እያሳሳቀ ነው›› እንዲሉ አንድን የክፋት ድርጊት ሲጀምሩት ለውስጥ የሚያቀብለው ስሜት ለየት ይላል፡፡ ሃሳቡ በሳቅ ደስታ ተዋዝቶ ፣ ውስጥን በሀሴት የሚያረሰርስ እስኪመስልም ለጀመሩት ዓላማ ራስን አሳልፎ እስከመስጠት ያደርሳል ፡፡

ይህ አይነቱ እውነት ከራስ አልፎ የሰዎችን ክብርና ማንነት የሚነካ ከሆነ ደግሞ የክፋቱን ጫፍ ለማግኘት ይቸግራል፡፡ በየቀኑ በራስ ተነሳሺነት ተገፋፍተው የሚሄዱበት ርቀትም መጨረሻ ላይኖረው ይችላል፡፡ እንዲህ ያለው መንገድ ከወሰደበት አቅጣጫ በቀላሉ የሚመልስ አይሆንም፡፡ ጠፍተው የቀሩ እስኪመስል ከራስ ጋር ይለያያል፣ ያቆራርጣል፡፡

ተደጋግሞ እንደሚባለው ማህበራዊ ሚዲያን ለበጎ ዓላማ ከተጠቀምነው ሁሌም አትራፊዎች ነን፡፡ ከራሳችን አልፈን በርካቶችን ለመድረስ ድልድይ ይሆነናል፡፡ ከዚህ በተቃራኒ በክፋት ዓላማ ከተጓዝንበት ግን እንደ አወጣጣችን ልንመለስበት ችግር ነው፡፡

ይህ ማህበራዊ ሚዲያ ይሉት ጉዳይ እስከአሁን ብዙ አሳይቶናል፡፡ በጎ የሚባለውን በመልካም እንውሰደውና አንዳንዶች በሚዲያው ተጠቅመው እያደረጉት ያለውን ያልተገባ ድርጊት በመጠኑ እንቃኝ፡፡

በቅርቡ ነው፡፡ በዚሁ ሚዲያ የተለያዩ ገፆች ከሀገራችን ታዋቂ ሴት ተዋናዮች መካከል የአንዷ ስም እየተነሳ ይብጠለጠላል፡፡ ጉዳዩ ደግሞ በእሷ ህይወት ብቻ አልቆመም፡፡ ስለ ልጇቿና ባለቤቷ ጭምር የማይወሳ፣ የማይነገር የለም፡፡ በእርግጥ ስለ ታዋቂ ሰዎች ብዙ ቢባል አይገርም ይሆናል፡፡

የሰዎቹ የግል ታሪክ ፣ የቤተሰብ ሁኔታና ሌሎችም በየሰበቡ ሊወሱ ይችላሉ፡፡ የአንድን ሰው የመኖር መብት በመጋፋት ራስን እስከመጥላት የሚያዘልቅ አስነዋሪ ታሪክ መዝራት ግን ከነውርነት አልፎ ወንጀል እንደመስራት ይቆጠራል፡፡

አንዳንድ የማህበራዊ ሚዲያው ሱሰኞች ስለራሳቸው ህይወት የምትተርፍ ሽራፊ ሰከንድ ያላቸው አይመስሉም፡፡ ከዚህ ይልቅ ሌሎችን እንዴት እንደሚጎዱ፣ የከበረ ስማቸውን በምን መልኩ እንደሚያጠለሹ ሲጨነቁ ያድራሉ፡፡ ሌታቸው በነጋ ጊዜ በክፋት ያለሙትን ዓለም ዕውን ለማድረግ የሚቀድማቸው አይገኝም፡፡

እንዲህ አይነቶቹ የስም ጥላሸቶች አጉል ወሬን ይዘው ለመውጣት መረጃ ማስረጃ ስለሚባለው ጉዳይ አንዳች አይጨነቁም፡፡ ለእነሱ የሚዲያውን ገበያ ሊቆጣጠርላቸው የሚችል የአንድ ታዋቂ ሰው ስም ከነአባቱ መሸምደድ ብቻ በቂ ነው፡፡ የዚህን ሰው ክብርና ዝና ለማዋረድ ደግሞ ከየት እንደሚጀምሩ አሳምረው ያውቁታል፡፡

የሰዎች ሞራል እንደ እንጨት ተሰብሮ የሚወድቅበትን ስልት ለማግኘት ያዋጣል በሚሉት አቅጣጫ ሁሉ ይሮጣሉ፡፡ ስም ማጥፋታቸውን ያጠናክርልናል የሚሉትን መሰል ወሬ ካገኙም ዓይናቸውን አያሹም፡፡ በማንኛውም መልኩ የደረሰ ወሬ ለእነሱ ምቹና አስፈላጊ ነው፡፡

አሁን አሁን ደግሞ ይህ አይነቱ የስም ማጥፋት ሩጫ ከተራ የጽሁፍ ወሬ አልፎ በአካል ወጥቶ እስከመፋጠጥ የደረሰ ሆኗል፡፡ ‹‹የእከሊት ሚስት እከሌ ከሚባል ሰው ጋር ስትወሰልት ተያዘች፣ ባሏ ማንነቷን አውቆ ትዳሩን ፈታ፣ እሷ በአደባባይ ተጋለጠች፡፡›› የሚሉና አንገት የሚያስደፉ የስም ማጥፋት ዘመቻዎች ያለእፍረት ይራገባሉ፡፡

ሰዎቹ ስለሚነዙት ወሬ ታማኝ መሆናቸውን ለማሳየት በፊልምና ፎቶግራፍ የተደገፈ በቂ ማስረጃ በእጃቸው አንዳለ ሲናገሩ በተለየ መተማመንና እርግጠኝነት ነው፡፡ ጉዳዩ ‹‹ከአፍ ከወጣ አፋፍ›› ነውና እነሱን የሰሙ አንዳንዶች ጫፍ ይዘው ለማራገብ ሁሌም ተባባሪዎች ናቸው፡፡

በዚህ መነሻ የሚጀመረው ስም ማጥፋትም ነፍስ ዘርቶ ፣ በአካል ገዝፎ ውስጥን ለመስበር አፍታ አይቆይም፡፡ ብዙዎች ታዲያ የሰሙትን ወሬ እንደዋዛ አያልፉትም፡፡ ሁኔታውን ስለመውደዳቸው በምልክት ገልጸው፣ ያዩትን ለሌሎች አጋርተው፣ ከቻሉም በሌላ ልብ ሰባሪ ቃል ሃሳቡን አራግበው ጫፍ ያደርሱታል፡፡

በዚህ መቀባበል ከብዙኃን ጆሮ የሚዳረሰው አጉል ወሬ አቅም ለማግኘት ጉልበቱ አይዝልም፡፡እውነት ይሁን ሀሰት ባልተረጋገጠበት አፍታ በርካታው ታዳሚ የባለ ታሪኩን የስም ማጥፋት ዘመቻ በእኩል ይጋራዋል፡፡

በጣም አስገራሚው ነገር በጉዳዩ ላይ የአብዛኞች ሃሳብና አስተያየት መመሳሰሉ ነው፡፡ለዚህ ደግሞ የስም አጥፊዎቹ ኃይልና ተጽዕኖ ሰፊውን ድርሻ ይጫወታል፡፡ ‹‹ የወደቀ ዛፍ ምሳር ይበዛበታል›› እንዲሉ ነገሩን በወጉ ያልተረዱ ሁሉ ያሻቸውን ሃሳብ ለመሰንዘር ጽሑፍና ቃል የሚለማመዱበት አጋጣሚ ይሆናል፡፡

ሌላው ችግር ደግሞ ጉዳዩ ለሌሎች መነሳሳት በጎ ምሳሌ አለመሆኑ ነው፡፡ ትናንት ይህን ታሪክ ያዩ፣ የሰሙ አንዳንዶች ተከታዮቻቸውን ለማበራከት በጠማማው መንገድ ማለፋቸው አይቀርም፡፡ እነሱም ስም ለማጥፋት፣ በማያገባቸው ጠልቀው ለመዘላበድ የተጋሩት ተሞክሮ መነሻቸው ይሆናል፡፡ እንደሌሎቹ ሁሉ ያሻቸውን ነውርነት ለመሰንዘር አጋጣሚውን በመነሻነት ይጠቀማሉ፡፡

ለዚህ ሁሉ ክፉ ድርጊት መስፋት ዋንኛ ምክንያት ደግሞ በሀገራችን በዚህ ዘርፍ ላይ የሚስተዋለው የሕግ መላላት ተጠቃሽ ነው፡፡ብዙ ጊዜ ተበዳዮች በማስረጃ ከሳሾቻቸውን መልሰው ያለመክሰሳቸው እውነታና የሕጉ በወግ አለመተግበር ችግሩን አባብሶታል፡፡

የጥላቻ ንግግርና የሕጉ ዕውንነት በአግባቡ ሥራ ላይ የሚውልበት አጋጣሚ ቢተገበር ግን ማንም ነውርነትን ሕጋዊ ባላደረገ ነበር፡፡ ከዚሁ ጋር ተያይዞ ተበዳዮች ለሚሆንባቸው ክፉ ድርጊት መረጃን በማስረጃ አስደግፈው መብታቸውን ማስከበር ቢሞክሩ የሕጉን የበላይነት ማረጋገጥ ይቻላል፡፡

ደጋግመን እንዳስተዋልነው ባለቤቱ በራሱ ላይ ማዘዝ እስከማይችል ድረስ በፎቶግራፍ፣ ድምጽና ተንቀሳቃሽ ምስል ማንነቱን እያሰጡ፣መሳለቂያ ማድረግ ከወንጀልም በላይ ወንጀል ነው፡፡ በአንዱ ሃሳብ ላይ ተመርኩዞ ሌላው የሚሰነዝረው አስተያየትም ባብዛኛው ከዋናው ድርጊት የተለየ አይሆንምና በእኩል ሊጤን ይገባል፡፡

እስካሁን እንደተስተዋለው በጉዳዩ ላይ የሚሰጠው የመጀመሪያ አስተያየት ጠማማ ከሆነ እሱን ተከትለው የሚመጡ ሃሳቦችም ፍጹም የተቃኑ አይሆኑም፡፡ ይህን መረን የወጣ የማህበራዊ ሚዲያ ተሞክሮ እንዳደጉት ዓለማት ፈጥኖ መቆጣጠር ባይቻል እንኳን የራስን ሙከራ ማድረጉ አይከፋም፡፡

ለዚህ አባባሌ መነሻዬ ላይ ልጠቅሰው ወደሞከርኩት ሃሳብ ልመለስ፡፡ ስሟ በማህበራዊ ሚዲያ ሲብጠለጠል ስለከረመው አንዲት ሴት፡፡ ይች ሴት በሀገራችን ጥሩ እውቅና ካላቸው ሴት ተዋናዮች መሀል አንዷ ሆና ትጠቀሳለች፡፡ የማህበራዊ ሚዲያው እሾህማ ግርፋት ካገኛቸው መካከልም ግንባር ቀደሟ ናት፡፡ ማንነቷን መሠረት ባደረገውና ጊዜያትን ባስቆጠረው የስም ማጥፋት ዘመቻ እሷና ቤተሰቦቿ አንገት ሲደፉ ቆይተዋል፡፡

ባለቤቷንና ልጆቿን ጭምር ሲሸነቁጥ የኖረው ስም ማጥፋት ለጊዜያት ብቻ የቆየ አልነበረም፡፡ በስሟ በተከፈተ ማህበራዊ ገጽ ኑሮና ህይወትን፣ በሚሰረስር ክፋት ብዙ ጉዳዮችን እንዳዛባ ዘልቋል፡፡ በሙያዋና በግል ህይወቷ ከፍተኛ ተጽዕኖ ያሳደረው ይህ ጉዞ ‹‹ይሁነኝ›› ብለው ዓላማውን ለሚያራምዱ ግለሰቦች ደግሞ በረብጣ የተሞላ ትልቅ ሻንጣ ሆኖ ነበር፡፡

‹‹ትዕግስትም ልክ አለው›› እንዲሉ አሁን ላይ በተበዳይዋ ብርቱ ጥረት ይህን ክፉ ድርጊት የፈጸሙ ግለሰቦች በሕግ የሚጠየቁበት መፍትሔ መገኘቱ ተሰምቷል፡፡ በበቂ ማስረጃና መረጃ በሕግ ተጠያቂ እንደሆኑ የተነገረላቸው የስም ቀበኞች እነሆ! በቃችሁ ሊባሉ ጊዜው ደርሷል፡፡

ማንም ከሕግ አምልጦ የሚኖር የለምና ለግል ጥቅማቸው ሲሉ በርካቶችን አንገት የሚያስደፉ የክፋት ምሳሌዎች ከዚህ አጋጣሚ ይማራሉ ተብሎ ይታሰባል። እዚህ ላይ ‹‹በአፍ ይጠፉ በለፈለፉ›› ይሉት ብሂል ልኩን ያገኘ ይመስላል፡፡

# ዓለም አቀፍ

## የሩሲያ ጦር አሰልጣኞች ኒጀር ገቡ

**በጋዜጣው ሪፖርተር**

የሩሲያ ጦር አሰልጣኞች የኒጀር ብሄራዊ ጦርን ለማሰልጠን ኒሜይ መግባታቸው ተገለጸ።

የሩሲያ ጦር አሰልጣኞች ኒጀር መግባታቸው ሞስኮ በአስቸጋሪ ሁኔታ ውስጥ በሚገኘው የምዕራብ አፍሪካ የሳህል ቀጣና ተጽእኖዋን እያሳደገች ስለመምጣቷ ያመላክታል።

ባሳለፍነው ረቡዕ ወታደራዊ ስልጠና ለመስጠት የኒጀር ዋና ከተማ ኒሜይ የገቡት የሩሲያ ጦር ስፔሻሊስቶች የተለያዩ ጦር መሳሪያዎችን ከእቃ ጫኝ አውሮፕላን ሲያወርዱም ታይተዋል ነው የተባለው።

የሩሲያ ወታደራዊ አሰልጣኞች የአየር መከላከያ ሥርዓቶችን ይዘው ኒጀር መግባታቸውንም የሀገሪቱ ብሄራዊ ቴሌቪዥን ጣቢያ ባወጣው ዘገባ አመላክቷል።

ከሩሲያ ጦር አሰልጣኞች መካከል አንዱ ከኒጀር ብሄራዊ ቴሌቪዥን ጣቢያ ጋር ባደረገው ቆይታ፤ “እዚህ የተገኘነው የኒጀር ብሄራዊ ጦርን ለማሰልጠን እና በሁለቱ ሀገራት መካከል ያለውን ወታደራዊ ትብብር ለማሳደግ ነው” ብሏል።

አሰልጣኞቹ ኒጀር ኒሜይ የገቡት በሩሲያ እና በኒጀር ጁንታ መካከል በሰላምና ፀጥታ ዘርፍ በጋራ ለመስራት ስምምነት ላይ መድረሳቸውን ተከትሎ ነው።

የምዕራብ አፍሪካዊቷ ሀገር ኒጀር ጁንታ ባለፈው ዓመት በመፈንቅለ መንግስት ስልጣኑን ከተቆጣጠረ በኋላ ከሞስኮ ጋር ያለውን ግንኙነት እያጠናከረ መጥቷል።

ኒጀር ከፈረንሳይ ጋር የነበራትንና ረጅም ዓመታትን ያስቆጠረውን ወታደራዊና ዲፕሎማሲያዊ ግንኙነት ማቋረጧ ይታወቃል።



## የፀጥታው ምክር ቤት ፍልስጤም ባቀረበችው ጥያቄ ላይ ሳይስማማ ቀረ

**በጋዜጣው ሪፖርተር**

የፀጥታው ምክር ቤት ፍልስጤም ባቀረበችው ጥያቄ ላይ ሳይስማማ ቀረ።

የተባበሩት መንግሥታት ድርጅት (ተመድ) የፀጥታው ምክር ቤት አባላት የፍልስጤም አስተዳደር ባለስልጣን ባቀረበው ሙሉ የተመድ አባልነት ጥያቄ ላይ አልተስማሙም።

ጥያቄውን አዲስ አባል ለሚቀበለው የተመድ ኮሚቴ ያቀረቡት የሚያዝያ ወር የምክር ቤቱ ፕሬዚዳንት የማልታዋ አምባሳደር ቫኔሳ ፍራዚየር በተደረገው ዝግ ስብሰባ "ስምምነት የለም" ብለዋል።

አምባሳደሯ አክለውም እንዳሉት "ነገርግን አብዛኞቹ የአባልነት ጥያቄውን ደግፈውታል።"

አባል ሀገራቱ በጥያቄው አስፈላጊነት ላይ ተስማምተው ቢሆን ኖሮ ለምርጫ ወደ ምክር ቤቱ ይቀርብ ነበር።

በተመድ የፍልስጤም ተወካይ ርያድ መንሱር የፀጥታ ምክር ቤት የሙሉ አባልነት ጥያቄያችንን በመቀበል ዓለም አቀፍ መግባባት የተደረሰበትን የ'ቱ ስቴት ሶሉሽንን' ለመፈጸም ቁርጠኛ ይሆናል የሚል ተስፋ እንዳላቸው ተናግረው ነበር።

ፍልስጤም ከ12 ዓመታት በፊት በመተድ የታዛቢነት ቦታ ተሰጥቷታል።

የፍልስጤም አስተዳደር ሙሉ የተመድ አባል ለመሆን ለመጀመሪያ ጊዜ ጥያቄ ያቀረበው በ2011 ነበር።

በተመድ የእስራኤል አምባሳደር ጊላድ ኢርዳን ፍልስጤም ለእስራኤል የደህንነት ስጋት ነች ሲሉ ጥያቄውን አስቀድመው ተቃውመዋል።

አምባሳደሩ ለእስራኤል የሀገርነት እውቅና መስጠት የተመድን ቻርተር የሚጥስ እና በድርድር ዘላቂ መፍትሔ እንዳይመጣ የሚያደርግ ነው ሲሉ ተቃውመዋል።



የሚያዝያ ወር የምክር ቤቱ ፕሬዚዳንት የማልታዋ አምባሳደር ቫኔሳ ፍራዚየር በተደረገው ዝግ ስብሰባ "ስምምነት የለም" ብለዋል

የአረብ ሀገራት ከእስራኤል ጎን የፍልስጤም ሀገር ማቋቋም የሚያስችለው 'የቱ ስቴት ሶሉሽን' ተግባራዊ ካልሆነ በመካከለኛው ምሥራቅ ዘላቂ ሰላም አይመጣም የሚል አቋም ይዘዋል።

# ስፖርት





## ‹‹በማንዴላ ዋንጫ›› የቦክስ ፍልሚያ ለውጤት የሚያበቃ ዝግጅት ተደርጓል

**ዓስማሁ ግዛው**

በነፃነት ታጋዩና በቀድሞው የደቡብ አፍሪካ ፕሬዚዳንት ኔልሰን ማንዴላ መታሰቢያነት የሚካሄደው ‹‹የማንዴላ ዋንጫ›› የቦክስ ውድድር እአአ ከሚያዝያ 15-21 በደቡብ አፍሪካ ደርባን ከተማ ይካሄዳል። የኢትዮጵያ ቦክስ ብሔራዊ ቡድንም በዚህ ውድድር ተሳታፊ ነው። ብሔራዊ ቡድኑ ለዚህ ውድድር ተሰባስቦ ዝግጅት ከጀመረ 15 ቀን ሆኖታል። እያደረገ የሚገኘው ዝግጅትም ጠንካራና ለውጤት የሚያበቃ መሆኑን የቡድኑ አሰልጣኝና ቦክሰኞቹ ገልጸዋል።

የቦክስ ብሔራዊ ቡድኑ የሀገር ቤት ዝግጅቱን አጠናቆ ዛሬ ጉዞውን ወደ ውድድሩ ስፍራ ያደርጋል። ቡድኑ ከመጋቢት 24 ጀምሮ መቀመጫውን ቱሊፕ ሆቴል በማድረግ በጃንግል ቦንግ፣ በኢትዮጵያ ስፖርት አካዳሚ፣ በራስ ሀይሉ እና በፕላቲኒየም ጂምናዚየሞች የውድድሩን ስፍራ ባማከለ ሁኔታ በቀን ሁለቴ ልምምዱን ሲሰራ ቆይተል። ቡድኑ በአፍሪካ ጨዋታዎች ተሳትፎው ሜዳሊያ ያመጡ ቦክሰኞች እና በአንደኛው ዙር የቦክስ ቻምፒዮና ተጫውተው ውጤት ያስመዘገቡ የቡጢ ተፋላሚዎችን አካቶ ዝግጅቱን በማድረጉ በደርባኑ ውድድር ውጤት እንደሚጠብቁ ዋና አሰልጣኙ ዋና ኢንስፔክተር ቴዎድሮስ ጥላሁን ተናግረዋል።

አብዛኞቹ ቦክሰኞች ልምድ ባይኖራቸውም በክለቦቻቸው ጠንካራ ተፎካካሪዎች መሆናቸውን የገለጹት አሰልጣኙ፤ የቡድኑ የአካል ብቃት፣ ቴክኒክና የታክቲክ ስልጠናዎችን በማሳደግ ክፍተቶችን ተለይቶ መስራቱን አስረድቷል። በዚህም መሰረት አዳዲስ



**የቦክስ ብሔራዊ ቡድኑ ዝግጅቱን አጠናቆ ዛሬ ደርባን ይጓዛል፤**

የሆኑትን እና በዓለም አቀፉ ቦክስ ፌዴሬሽን አማካኝነት የሚወጡትን ሕጎች በመለየት ዝግጅቱ እንደተደረገ ገልጸዋል። ስፖርተኞቹ በታክቲክ፣ ቴክኒክና በአካል ብቃቱ ረገድ ጥሩ የሚባሉና ውጤት ማምጣት የሚችሉ ወጣቶች በመሆናቸው ውድድሮችን ለማሸነፍ ያላቸው ጉጉትም ከፍተኛ እንደሆነ አሰልጣኙ ተናግረዋል።

የቡድኑን የአሸናፊነት ስነልቦና ለመገንባት በባለሙያ እና ልምድ ባላቸው ስፖርተኞች እና አሰልጣኞች በመታገዝ ስልጠና አግኝተዋል። ዝግጅታቸውን በትልቅ ሞራልና ተነሳሽነት ማድረጋቸውንም አክለዋል። በዝግጅቱ ወቅት በሚደረገው ልምምድ ሴቶችና ወንዶች እኩል በሆነ ደረጃ በትጋት እየሰሩ ለውጤት የሚያበቃ ዝግጅትን እንዳደረጉም አስረድተዋል።

ስፖርቱ በአፍሪካ ጨዋታዎች ውጤት እንደሚመዘገብበት በተግባር ታይቷል። ባለሀብቱና መንግሥት ትኩረት ቢሰጡት ከዚህ የተሻለ ውጤት ማስመዝገብ ይችላል። ለሚደረገው ዝግጅት ፌዴሬሽኑ ጥሩ ድጋፍ እያደረገ ሲሆን፤ አመርቂ ውጤት ለማምጣት የሁሉም ድጋፍ አስፈላጊ መሆኑን አሰልጣኙ ጠቁመዋል።

የብሔራዊ ቡድን አምበል አብረሃም አለም፣ ቡድኑ ከጋናው ውድድር መልስ ዝግጅት እያደረገ እንደሆነና ሰፊ የመዘጋጃ ጊዜን እንዳገኘ ይናገራል። የቦክስ ስፖርት በመነቃቃት ላይ እንደሆነ የሚናገረው አብረሃም በጥሩ ሁኔታ እንደተዘጋጁና የተሻለ ውጤት እንደሚመጣም ተስፋ አድርጓል። አሰልጣኞቹ በቂ ልምድ ያላቸው በመሆኑ ለቡድኑ የሚያስፈልጉ ስልጠናዎችን እንደሰጡ እና ከስልጠና መልስ ስፖርተኞቹ የሚያገኙት አገልግሎትም ዝግጅቱን የሚመጥን እንደሆነ አስረድተዋል። ሀገርን በተለያዩ ውድድሮች በመወከል የብር ሜዳሊያ ማምጣት የቻለው ይህ ቦክሰኛ፤ ከዚህ በፊት በነበሩ ውድድሮች በጥቂት ስህተት ቢሸነፍም፣ ይሄንን በማረም ወርቅ ይዞ ለመምጣት ተዘጋጅቷል። የቡድን መንፈስ ላይ የተሰራው ሥራ ትልቅ መሆኑን የተናገረው አብረሃም፤ እሱና የቡድኑ አባላት 11 ወርቅ ሜዳሊያዎችን ለማምጣት እንዳሰቡም ገልጿል።

ሌላዋ የብሔራዊ ቡድኑ አባል ምክትል ሳጅን ሮማ አሰፋ በበኩሏ የተደረገው ዝግጅት በቡድን መንፈስ የመወዳደር ስሜትና ከሚሰጠው ስልጠና አኳያ ጥሩ መሆኑን ገልጻለች። ለውድድር የሚያበቃ ዝግጅት በመደረጉ ሜዳሊያውን በሙሉ የመውሰድ አቅም እንዳላቸውም ተስፋ አላት።

በዚህ ውድድር ኢትዮጵያን ጨምሮ ከ41 የአፍሪካ ሀገራት የተወጣጡ 360 ቦክሰኞች በ12 የሴቶችና በ13 የወንዶች ሚዛን ለአህጉሪቱ ክብር ይፋለማሉ።

የኢትዮጵያ ቡድን በአንድ ዋና እና ምክትል አሰ ልጣኝ ዝግጅቱ እየተመራ ውድድሩ የሚያካድ ሲሆን፤ በተለያዩ ኪሎ ግራሞች 4 ሴትና 7 ወንድ በድምሩ 11 ቦክሰኞችን በመያዝ ይፎካከራል። በወንዶች 51 ኪሎ ግራም ፍትሐዊ ጥሙይ፣ በ54 ኪሎ ግራም ሱራፌል አላዩ፣ በ57 ኪሎ ግራም አብዱሰላም አቡበከር፣ በ60 ኪሎ ግራም አቡበከር ሰፋን፣ በ63 ኪሎ ግራም አብረሃም አለም፣ በ67 ኪሎ ግራም ኤርሚያስ መስፍን እና በ75 ኪሎ ግራም ተመስገን ምትኩ ኢትዮጵያን ይወክላሉ። በሴቶች ደግሞ በ52 ኪሎ ግራም ቤቴልሔም ገዛኸኝ፣ በ54 ኪሎ ግራም ሮማን አሰፋ፣ በ60 ኪሎ ግራም ሚሊዮን ጨፌ እና በ66 ኪሎ ግራም ቤቴል ወልዴ ተካተዋል።